ብትል፣ 22. ነቢዩ በእግዚአብሔር (ያህዌ) ስም የተናገረው ካልተፈጸመ ወይም እውነት ሆኖ ካልተገኘ፣ መልእክቱ እግዚአብሔር (ያህዌ) የተናገረው አይደለም። ያ ነቢይ በድፍረት ተናግሮታልና እርሱን አትፍራው" (ዘዳ 18)።

"14 እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፤ "ነቢያቱ በስሜ የሐሰት ትንቢት ወይም ራእይ፣ (ከንቱ) ሟርት ይናገራሉ፤ እኔ አልላክኋቸውም፤ አላዘዝኋቸውም፤ አልተናገርኋቸውምም። የሐሰት ራእይ፣ ሟርት፣ ከንቱ ነገርንና የልባቸውን ሽንገላ ይተነብዩላችኋል። 15. ስለዚህ በስሜ የሐሰት ትንቢት ስለሚናገሩ ነቢያት እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ እኔ ሳልልካቸው፣ 'ሰይፍና ራብ በዚች ምድር ላይ አይመጣም' የሚሉ እነዚህ ነቢያት በሰይፍና በራብ ይጠፋሉ፤ 16. ትንቢቱ የተነገረለትም ሕዝብ ከሰይፍና ከራብ የተነሣ በኢየሩሳሌም አደባባዮች ይወድቃል፤ እነርሱንም ሆነ ሚስቶቻቸውን ወይም ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን የሚቀብራቸው አይገኝም። ለበደላቸው የሚገባውንም ቅጣት በላያቸው አወርዳለሁ" (ኤር. 14)።

ስለዚህ ነቢያት የመሳሳት ፈቃድ ሊሰጣቸው ይገባል የሚሉ አንዳንድ ተከራካሪዎች፣ በዚህ አግባብ መምጣታቸው ፍጹም ስሕተት ነው። ከአምላክ የተገኘ ነው በሚል በአምላክ ስም ስሚነገር፣ ነገር ግን ከአምላክ ላልሆነ ትንቢት ድጋፍ ስጥተዋልና አካሄዳቸው ውጉዝ ነው። ትንቢቱም ስሚያመጣው (ስሚያስከትለው) አሉታዊ ውጤት ተጠያቂዎች ናቸው።



# ክፍል ሰባት

## መርገም ከምዝላት፣ ከእንጅላት[1]...ይተላለፋልን?



### ከየት መጣሁ?
### ዴሬክ ፕሪንስ፣ ማርሊን ሄኪ፣ ጆን ኤክሃርት

"መርገም ከዘር ማንዘር ይተላለፋል፤ ይህም መርገም

[1] የአማርኛ ቋንቋ ዐዋቂዎች የዘር ሐረግ ቈጠራ፣ በዚህ መልክ እንደሚሄድ ያስረዳሉ:— አባት/እናት፣ አያት፣ ቅድመ አያት፣ ቅም አያት፣ ቅማንት፣ ሽማት፣ ምዝላት (መንዥላት)፣ እንጅላት (እንዥላት)፣ ፍናጅ፣ ቅናጅ፣ አስልጥ፣ አመለጥ፣ ማንትቤ፣ ደረባቴ። መርገም ይተላለፋል የሚሉ ሰዎች፣ ይተላለፋል የሚሉት እስከ ሦስተኛና አራተኛ ትውልድ ነው፤ ማለትም እስከ ቅድመ አያትና ቅም አያት ድረስ ነው። ምዝላትና እንጅላት ግን በትውልድ ሐረጉ ውስጥ ሰባተኛና ስምንተኛ አጸቅ ናቸው። እኔ "ምዝላት፣ እንጅላት" የሚለውን በርእስ የመረጥሁት፣ በዘር ሐረግ ቈጠራ ብዙ የተለመደ አነጋገር ስለመሰለኝ ነው። ስለዚህ በዚህ ጽሑፍ "ምዝላት እንጅላት" ማለት፣ "ዘርዐ ሐረግ" የሚለውን ትርጉም የሚወክል ብቻ እንደ ሆነ ልብ ይሏል።

በክርስቲያኖች ላይ እውናዊ ተጽእኖ አለው" የሚለውን ትምህርት የቀመሩት፣ ደርዝ ባለው መንገድ ያደራጁት እንዲሁም በጊዜ ሂደት እጐልብተው ለዓለም ያስተዋወቁት፣ እንግሊዛዊው ሰባኪ ዴሬክ ፕሪንስ እንደ ሆኑ ይነገርላቸዋል[2]። አስተምህሮው በኢትዮጵያ ውስጥ ስመግነት ግን፣ እርሳቸውን ጨምሮ በርካታ ሰዎች የመሪውን ድርሻ ሲወስዱ የሚችሉ ይመስለኛል—ማርሲን ሄኪና ጆን ኤክሃርት፣ ከፕሪንስ ባልተናነሰ መልኩ በዚህ ረገድ እሻራቸውን፣ በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የጣሉ ሰዎች ናቸው[3]።

---

[2] *አንዳንድ ጸሐፍያን የአስተምህሮው ጠንሳሽ ዴሬክ ፕሪንስ (Derek Prince) ናቸው ሲሉ ጽፈዋል። በተለይ ወደ አሜሪካን መጥተው፣ ከአሜሪካውያኑ Don Basham, Bob Mumford, Charles Simpson እንዲሁም Ern Baxter ጋር በነበራቸው ግንኙነት፣ አስተምህሮው ዳብሮ የአሁኑን መልክ እንዲይዝ ተደርጓል የሚሉ ጸሐፍያን አሉ። እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን ቀመር በ1970ዎቹ ላይ፣ እነዚህ ሰዎች "covenant relationship" የሚል "የኪዳን ጥምረት" መሥርተው፣ "New Wine" የሚል መጽሔት ማሳተም በጀመሩበት ጊዜ፣ አስተምህሮው በዓለም ዙሪያ የመስፋፋት ዕድል አገኘ። "Derek Prince Legacy Radio" የሚባለውም የሬዲዮ ፕሮግራም፣ ለአስተምህሮው ሥርጭት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው። ዴሬክ ፕሪንስ (Derek Prince 1915-2003) ከእንግሊዛውያን ቤተ ሰቦች በሕንድ አገር የተወለዱ ሲሆን፣ በእንግሊዝ የጦር ሰራዊት ውስጥ አገልግለዋል። የዕብራይስጥ፣ የግሪክ፣ የአረማይስጥና የላቲን ቋንቋዎችን እንደሚያውቁ ይነገርላቸዋል። ይህ ምን ያህል እውነት ነው እንዲሁም ዕውቀታቸው እስከ ምን ድረስ ይዘልቃል የሚለውን ጉዳይ፣ በነጻ ምንጭ አረጋግጦ ለዚህ ጽሑፍ ማድረስ አልተቻለም። ስለዚህ "Everybody presumed innocent until proven guilty beyond the reasonable doubt" በሚለው አካሄድ፣ ለጊዜውም ቢሆን ይህንኑ መረጃ ይዘን እንቆያለን።*

[3] *በኢትዮጵያ ውስጥ ይህን አስተምህሮ በማስተማር በስፋት የሚታወቁት፣ ከሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ወጥተው፣ "ዐርነት ቤተ ክርስቲያንን" የተከሉት፣ እነመጋቢ የማነብርሃን እንዳለ ናቸው። የእንቅስቃሴው ዕውቅ መምህር ግን፣ አቶ ጌታቸው መኩሪያ እንደ ነበሩ ብዙዎች ይስማማሉ። ከአቶ ጌታቸው መኩሪያ ጋር በነገረ መስኮት ዙሪያ የመጠያየት ዕድል ባላገኝም፣ ግለሰቡን በቅርበት የሚያውቋቸው ወዳጆቼ ግን፣ አቶ ጌታቸው እጅግ ትልቅ ዕውቀት እንዲሁም የማስተማር ክሂሎት ያላቸው ኢትዮጵያዊ ምሁር እንደ ሆኑ ይገልጻሉ። እንዲያውም ሁለት ወዳጆቼ፣*



እነዚህ ሦስት ሰዎች፣ በርእስ ጉዳዩ ላይ የጻፏቸው መጻሕፍት፣ በአማርኛ ቋንቋ ተተርጉመውና በብዙ ሺህ ቅጅ ተባዝተው፣ በአገሪቱ ውስጥ ተሠራጭተዋል። የዴሬክ ፕሪንስን መጻሕፍት በመተርጐምና አስተምህሮእቸውን በኢትዮጵያ ውስጥ በማስፋፋት የሚታወቁት የቀድሞው፣ "የዐርነት ቤተ ክርስቲያን" መጋቢ፣ መጋቢ የማነብርሃን እንዳለ ናቸው[4]።

---

*"በሳቸው መጠን ያለ ዐዋቂና አስተማሪ አይቼ ሰምቼ አላውቅም" ብለውኛል—የሚገርም ምስክርነት ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ዛሬ ያለችው የዐርነት ቤተ ክርስቲያን ይህ ዐይነት አቋም ይኑራት አይኑራት፣ እቅጩን ማወቅ አልተቻለም። ነገር ግን ከመጋቢ የማነብርሃን በኋላ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱን በመጋቢነት የሚመሩት፣ መጋቢ ዳርሰማ አስፋ፣ ነገረ መስኮትን በወጉ የተማሩ ሰው መሆናቸውን እንዲሁም ቤተ ክርስቲያኒቱ ይህን መሰል አስተምህሮ እንደማታምን አስታውቃ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን ኅብረት መቀላቀሏን በመጥቀስ፣ ቢያንስ በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ነባሩ አቋም እንደ ሌለ አንዳንዶች ይገልጻሉ። እንቅስቃሴው አብቦ በነበረበት በ1970ዎቹ መጨረሻ አካባቢ፣ እኔን መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት ያስተምረኝ የነበረን ወንድም ጨምሮ፣ አንጋፋ የአጥቢያችን (ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን) የሙሉ ጊዜ አገልጋይ፣ ወደ እንቅስቃሴው በደፋ ገብተዋል፤ ቤተ ክርስቲያኒቱንም ትተው ሄደዋል። የሚገርመው ግን በዚያን ወቅት በእንቅስቃሴው ውስጥ የነበሩ በርካታ ሰዎች፣ ዛሬ የእንቅስቃሴውን መሠረታውያን ትምህርቶች እንደማይቀበሉ በይፋ እየገለጹ ነው። አስተምህሮውን በንባብ የተቀበሉ ሰዎች በንባብ ተመልሰዋል። ነገር ግን በሰባኪውያን የማስተማር ክሂሎት ተደንቀው፣ በዕውቀታቸው ጥልቀት ተደመው ወደ እንቅስቃሴው የገቡ ሰዎች፣ ተጽእኖ ያስከተሉባቸው ሰዎች ስብእና በልባቸው እስኪደበዝዝ ድረስ፣ አስተምህሮውን መተው ሲከብዳቸው ይችላል።*

[4] *በእንግሊዝኛ፣ "Blessing or Curse You can Choose" በሚል ርእስ ዴሬክ ፕሪንስ የጻፉትን መጽሐፍ፣ በኢትዮጵያውያን የዘመን አቈጣጠር 1989 ዓ.ም ላይ፣ "በረከት ወይስ መርገም እንዱን ምረጥ" በሚል ወደ አማርኛ የመለሱት፣ ያሳተሙት እንዲሁም ያሠራጩት፣ መጋቢ የማነብርሃን እንዳለ ናቸው። በመጀመሪያው ዕትም፣ ዐሥር ሺህ ቅጅ ተባዝቶ እንደ ተሠራጨ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ተገልጾአል። የትርጉምና የኅትመት ወጪውን የሸፈነው፣ "Derek Prince Ministries International" የሚባለው የዴሬክ ፕሪንስ ድርጅት እንደ ሆነ፣ ውስጥ ዐዋቂ ምንጮች ያስረዳሉ።*

በርካታ የጆን ኤክሃርትን መጻሕፍት እየተረጐሙና እያተሙ የሚያሠራጩት ደግሞ ቀድሞ፣ "ክሩሴደር ቤተ ክርስቲያን" አሁን "የክርስቲያኖች መቅደስ ቤተ ክርስቲያን" የሚባለውን ቤተ እምነት በኢትዮጵያ ያቋቋሙት፣ መጋቢ ኢዮብ ማሞ ናቸው[5]።

---

መጋቢ የማነብርሃን እንዳለ፣ የፕሪንስን በርካታ መጻሕፍት ተርጕመው በማሠራጨት በስፋት ይታወቃሉ። እነዚህንም መጻሕፍት በማሳተምና የትርጕም ወጪያቸውን በመሸፈን፣ የተባበረው የፕሪንስ ድርጅት እንደ ሆነ ይነገራል። ግለሰቡም ሆነ እርሳቸው በመጋቢነት ያገለግሉባት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን፣ ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት የስያትን ይህንና ይህን መሰል ትምህርት ትቻስሁ፣ ተሳስቼ ነበር በማለት የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረትን እንደ ተቀሳቀሰች ይታወቃል። ነገር ግን ኅብረቱን ከተቀሳቀሰችም በኋላ (ቢያንስ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ የማነብርሃን እንዳለ) የፕሪንስን ትምህርት በማስተማርም ሆነ በማስፋፋት ቀዳሚውን ቦታ እንዳላቸው ይታወቃል። በአንጻሩ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በኅብረቱ አመራር ውስጥ ያገለግሉ እንደ ነበር ይታወቃል። እንግዲህ የአስተምህሮን በተመለከተ የኅብረቱ አንዱ ምፀት ይህ ነው። ኅብረቱ አባይ ነባዮችን አስመልክቶ በቅርቡ የጀመረው የአስተምህሮ ተቈርቋሪነት ብዙዎችን አስገርሟል፤ ተስፋም ሰጥቶአል። ይህ ጉዳይ ወደ ፊት ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም እናምናለን፤ እንጸልይማለን። ኅብረቱ በውስጡ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት መሠረተ እምነታቸው ሳይዛነፍ ይዘው መቀጠላቸውን፣ ዕለት ዕለት የመመርመር ኀላፊነት ያለበት ይመስለናል።

[5] "መርገምን መሻር" የሚለውን መጽሐፍ ጨምሮ፣ "ሐዋርያ ነኝ" የሚሉትን የአሜሪካዊውን የጆን ኤክሃርትን (John Eckhardt) መጻሕፍት ወደ አማርኛ ቋንቋ ተርጕመው፣ በአገሪቱ ውስጥ ያሠራጩት መጋቢ ኢዮብ ማሞ ናቸው። ምናልባትም በኢትዮጵያ የሚገኘውን ቀድሞ፣ "ክሩሴደር" አሁን "የክርስቲያኖች መቅደስ ቤተ ክርስቲያን"፣ የሚባለውን ቤተ እምነት በኢትዮጵያ እንዲቈረቈር የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉት፣ ጆን ኤክሃርት ሳይሆኑ አይቀርም። እስከ ቅርብ ጊዜም ድረስ የመጋቢ ኢዮብን ደመወዝ ይከፍሉ የነበሩት፣ እኚሁ አስተማሪ እንደ ነበሩ አንዳንድ ምንጮች ያስረዳሉ። ምናልባት የቤተ ክርስቲያኒቱ የስም ለውጥ፣ መጋቢ ኢዮብ ከግለሰቡ ጋር ከተጋጩ በኋላ፣ እውን የሆነ ነው የሚል አስተያየትም አለ። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ላይ ጥናት የሚያካሂዱ ወገኖች እንዲሁም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ለውጥ በንቃት የሚከታተሉ ሰዎች፣ ወደ ፊት በዚህ እንዲሁም በዚህ



ትልቁ ምፀት ግን አሜሪካዊቷ ሰባኪ፣ ማርሊን ሂኪ (Marilyn Hickey)፣ "የትውልድን መርገም መስበር" "Breaking Generational Curses" በሚል ርእስ የጻፉትን መጽሐፍ፣ ተርጕሞና ዐስትሞ ያሠራጨው የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት የመሆኑ ሐቅ ነው[6]። የመጽሐፉን የትርጕም ሥራ እንዲሁም የኅትመት ወጪ ሙሉ በሙሉ የሸፈነው፣ መቀመጫውን አሜሪካን አገር ያደረገው የማርሊን ሂኪ ድርጅት ነው[7]። በወቅቱ ማርሊን ሂኪን ወደ ኢትዮጵያ በመጋበዝ እንዲሁም መጽሐፋቸውን በመተርጐም፣ በማሳተምና በማሠራጨት የኅብረቱ ጽሕፈት ቤት ያደረገውን እድራጎት ብዙዎች ነቅፈዋል[8]።

ነገር ግን የቱንም ያህል ጥረት ቢደረግ፣ መጽሐፉ እንዳይሠራጭ ግለሰቧም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የጅማ ስብከት እንዳያካሂዱ ማስቆም አልተቻለም። ምናልባት በወቅቱ የነበረው ውትወታ የፈየደው ነገር ቢኖር፣ ግለሰቧ በአዲስ አበባ ከተማ የጅማ ስብከት እንዳያካሂዱ መደረግ ብቻ ነው። በናዝሬት የነበራቸው የጅማ ስብከት ግን፣ በተያዘለት መርሐ ግብር እንዲካሄድ ተደርጓል። መጽሐፉ በብዛት የተሠራጨው እንዲሁም ግለሰቧ በስፋት እንዲያስተምሩ የተፈቀደላቸው በናዝሬት ነበር።

የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ በወቅቱ የነበሩትን የኅብረቱን ዋና ጸሓፊ፣ ግለሰቧ የእምነት እንቅስቃሴ አስተምህሮ ("Word of Faith

---

መሰል ጉዳይ ላይ ሚዛናዊነትን የተላበሰ፣ ጥም ቈራጭ ጽሑፍ እንደሚያስነብቡን ተስፋ እናደርጋለን።

[6] በኢትዮጵያውያን የዘመን አቈጣጠር በ1994 ዓ.ም።

[7] *Marilyn Hickey Ministries*

[8] ግለሰቧ ወደ በጐርጐርሳውያኑ አቈጣጠር ሚያዝያ 2014 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ በመሄድ፣ በተለያዩ አካባቢዎች ስብከት እንዳካሄዱ ይታወቃል። ይህ መጽሐፍ የሚያወራው ግን በኢትዮጵያውያን ዘመን አቈጣጠር በ1994 ዓ.ም የተካሄደውን ታሪክ ነው።

*Movement"*) ለባሊ መሆናቸውን እንዲሁም ተተርጉሞ ለንባብ የቀረበው መጽሐፍ፣ ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሠረተ እምነት ጋር ከፉኛ የሚጋጭ መሆኑ ግለሰቧን ወደ ኢትዮጵያ የማስመጣቱን ግብዣ ስሕተት እንደሚያደርገው በቃልም ሆነ በጽሑፍ ለማስረዳት ሙከራ አድርጓል። ነገር ግን ጽሕፈት ቤቱ፣ ድርጊቱን ማስቆም አልቻልም ያለው፣ የሚከተሉትን ምክንያቶች በመዘርዘር ነው:— *(1)* ግለሰቧ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ግብዣ የቀረበው፣ ትምህርታቸው በውል በማይታወቅበት ጊዜ ነው፤ *(2)* ግለሰቧ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እንዲሰብኩና ጽሑፋቸውን እንዲያሠራጩ ሙሉውን ወጪ የሸፈነው ድርጅታቸው ነው፤ *(3)* ግለሰቧ የጀማ ስብከት የሚያካሂዱበት ስፍራ ተወስኗል፤ የማስታወቂያና የቦታ ክፍያ ተካሂዷል፣ *(4)* የግለሰቧ ድርጅት መጽሐፉን በማስተርጐምና በማሳተም ከፍተኛ ወጪ አድርጓል። ይህ ሁሉ እውን በሆነበት በመጨረሻው ሰዓት ላይ፣ "አታገለግሉም" እንዲሁም "መጽሐፉ አይሠራጭም" ማለት አግባብነት ይጐድለዋል። ከዚህ የተነሣም፣ ስሕተት ነው የተባለው መጽሐፍ እንዳይሠራጭ እንዲሁም ለግለሰቧ የተዘጋጀው የጀማ ስብከት እንዲቋረጥ ማድረግ አልተቻለም[9]። የግለሰቧ አስተምህሮ ስሕተት መሆኑ በውል ከታወቀ

[9] እዚህ ጋ ሁለት ሁነኛ ጥያቄ ማንሣት አግባብ ይሆናል፤ ይኸውም:— *(1)* ቀድሞውንስ ቢሆን፣ የግለሰቧ ትምህርት በውል ሳይታወቅ ግብዣው እንዴት ሊካሄድ ቻለ? *(2)* የመጽሐፉ አስፈላጊነትና ጤናማነት በውል ሳይመረመር የትርጕም ሥራው እንዲሠራ እንዴት ተወሰነ? ምናልባት ይህ ጉዳይ የኅብረቱን ጽሕፈት ቤት የሚመራው፣ "የአስተምህሮ አቋም ወይስ የንዋይ ልጓም?" የሚል ጥያቄ ይጭራል። ተሰፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፣ እያንዳንዱ ቤተ እምነት እንዲሁም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ ነገረ መለኮት መርማሪ ማዕከል ወይም የዐቅብተ እምነት አገልግሎት ዘርፍ ሊኖረው ይገባል የሚለው በዚህ መሰሉ ዐቢይ ምክንያት ነው። የቤተ ክርስቲያንን የአስተምህሮ ንጽሕና መጠበቅና ማስጠበቅ ከሚቻልባቸው ሁነኛ መንገዶች ወስጥ ይህ አንዱ ነውና።



በኋላ እንኳ፣ እንዳችም ዕርምት ወይም ማስተካከያ ያለመደረጉ፣ ከሥተቱ በብዙ ጐኑ እንዲተረጐም በር ይከፍታል[10]።

## "ክርስቲያን ከመርገም መጠበቅ አለበት!"

ክርስቲያን በትውልድ መርገም ውስጥ ሊወድቅ ይችላል የሚለው ትምህርት አስተምህሮውን የሚያስተዋውቀው በሚከተለው መንገድ ነው:—

> "ከንቱነትና የተስፋቢስነት ስሜት፣ ሕይወትህን ተጫጭኖት ይሆን? ሕይወትህ በእንቅፋትና በመጥፎ አጋጣሚስ የተሞላ ይሆን? በብዙ ዘመን የደከምህበት ልፋትህ ከንቱ ሆኖ ዐመድ አፋሽ ስትሆን፣ የእግዚአብሔር በረከት እንዳልጐበኘህ ይሰማህ ይሆን? እነዚህን እንቅፋቶች የበለጠ ከባድና አስጨናቂ የሚያደርጋቸው፣ *አንተ ክርስቲያንና ጌታን የምትወድ ሆነህ ሳለ ስለደረሰብህ ነው።* ስመሆኑ ዳግም የተወለደ እና መንፈስ ቅዱስን የተሞላ ክርስቲያን፣ ከእርግማን በታች ይኖር ዘንድ ይገባዋልን? እንዲህ ከሆነ *አንድ ክርስቲያን ከመርገም እንዴት ሊገላገል ይችላል? እንዴትስ ነጻ ወጥቶ በእግዚአብሔር ሙሉ በረከት ሊራመድና ሊኖር ይችላል?"*[11]

[10] "አለባበስው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ" ይላል የአገራችን ሰው። ይኸው፣ "ምንም አይደል"፣ "ለክፉ አይስጥም"፣ "እኔ ምንተዳዬ"...የተባሉ ጉዳዮች፣ እነሆ ዛሬ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን ህልውና በጥያቄ ላይ ከትዋል። ይህ በምንም መልኩ ለወቀሳ ወይም በዚያን ወቅት የነበሩ መሪዎችን ለማሳጣት የተደረገ ጥረት አይደለም። ነገር ግን ከዚህ ዐይነቱ ተሞክሮ፣ ብዙ የምንማረው ነገር እንዳለ ለማስታወስ እንጂ። "ከታሪክ የምንማረው ከታሪክ ያለመማራችንን" ቢሆንም።
[11] ይህ የማንንም ልብ የሚስብ ትልቅ ጥሪ ነው። ምክንያቱም ስኬትን የማይፈልገው የሰው ልጅ የቱ ነው? በተለያዩ የሕይወት ፈርጆች፣ በሕይወቱ ተደጋጋሚ ኪሳራ ያላጋጠመው ፍጡር የቱ ነው (ቢያንስ አፍሪካ በምትባለው ምድር ተወልዶ ያደገ)? ቢያንስ፣ "ለክፉ ለደጉ ፈጦ መድኅኒት ነው" በሚለው አካሄድ፣ ማንኛውም ሰው ለሙከራ ሊነሣሣ ይችላል፤ ከዚህም የተነሣ፣ አስተምህሮውን ሊቀበል ተግባራዊነቱን ሊከተል እንደሚችል አያጠራጥርም። በተሞክሮም ሆነ በዕንስ ሐሳብ ደረጃ፣ አስተምህሮው ስሑት እንደ ሆነ ግን እንመሰክራለን።

> በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እነኝህን ጥያቄዎች በተመለከተ…ማብራሪያ ሰጥተዋል"[12]።
>
> "ቅዱሳን ድነታቸውን ከተቀበሉም በኋላ በእርግማን ሊጠቁ ይችላሉ። በቅዱሳን ሕይወት ውስጥ እርግማኖች ተነጥለው ታውቀው መሰበር አለባቸው። የእርግማን መሰበር አጋንንት የሚገለገሉበትን መብትና ሥልጣን ይነጥቃል። የተደላደሉበትን መብት ከመንጠቅ በኋላ፣ አጋንንትን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መግለጥ፣ ማስወጣትም ቀላል ነው"[13]።

የአስተምህሮው ቀዳማይ አመንጪ እንደ ሆኑ የሚነገርላቸው ዴሬክ ፕሪንስ፣ እርግማን እንድም ከእግዚአብሔር፣ በሌላ መልኩ ከሰይጣን ሊመጣ እንደሚችል ይገልጻሉ፣ "ከእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ ሕጋዊ ሲሆን፣ ከሰይጣን የሆነው ሁሉ ግን ሕገ ወጥ ነው"[14] የሚል አስተያየት አላቸው። ክርስቲያን "ሕጋዊ" የሆነውም ሆነ "ሕገ ወጥ" የሆነው መርገም እንዳይመጣበት፣ መጠንቀቅና አስፈላጊውን ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልገው ያስጠነቅቃሉ[15]። እንቅስቃሴው "ክርስቲያን ማነው?" የሚለውን ጉዳይ የሚያብራራው "ጌታን የሚወድ"፣ "ዳግም የተወለደ"፣ "መንፈስ ቅዱስ የተሞላን" ሰው በማለት ነው[16]።

የዴሬክ ፕሪንስም ሆኑ ባልደረቦቻቸው፣ ትምህርታቸውን በሦስት መልክ ቢያዋቅሩትም፣ ትምህርቱ ግን በሁለት

---

[12] ጆን ኤክሃርት፣ *መርገምን መሻር፤* (የክርስቲያኖች መቅደስ ቤተ ክርስቲያን፤ 2001 ዓ.ም)፣ ገጽ 1፤ ኢትኮሮት የእኔ። ይህን መጽሐፍ በቀጥታ የጠቀስነው፣ በመጽሐፉ ላይ በጉልኅ ሚታዩትን የሆህያት፣ የሥርዐተ ነጥቦችና የሰዋሰው ስሕተቶች አርመን ነው።

[13] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 33።

[14] ዴሬክ ፕሪንስ፤ *በረከት ወይስ መርገም አንዱን ምረጥ—የጭንቀት ሕይወት ከመመራት የመገላገያው ዘዴ፤* (የማኅበርሃን እንዳለ፤ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፤ 1989 ዓ.ም)፣ ገጽ 50።

[15] ዝኒ ከማሁ።

[16] ጆን ኤክሃርት፣ *መርገምን መሻር፤* ገጽ 1።



መሠረታውያን ነጥቦች መጠቃለል የሚችል ይመስለኛል። ይኸውም:—

**ሀ. ክርስቲያን በመርገም ውስጥ እንዳለ እንዴት ማወቅ እንደሚችል ገለጻ ያቀርባል፣**

**ለ. ክርስቲያን ከመርገም ለመላቀቅ ምን ማድረግ እንደሚጠበቅበት ያስረዳል[17]፤**

በዚሁ ቅደም ተከተል የእንቅስቃሴውን ጽሑፍ በቀጥታ በመጥቀስ የአስተምህሮውን ክንቱነት እንመረምራለን። ኋላም አስተምህሮው ለንድፈ አሳቡ ማዕከል ያደረጋቸውን ዋንኛ ምንባባት በለፋት እንተነትናለን።

## ሀ. ክርስቲያን በመርገም ውስጥ እንዳለ እንዴት ማወቅ ይችላል?

በዚሁ ርእስ ጉዳይ ላይ የእንቅስቃሴው ዕውቅ መምህራን የሚሰጡትን ጽሑፍ በቀጥታ እንጥቀስ:—

> "'እርግማን' ሰው እግዚአብሔርን ሲያሳዝን፣ ክፋት ሲፈጽም፣ በደልን፣ ግፍን ሲሠራ፣ ከእግዚአብሔር አምላኩ የሚቀበለው የበደል ውጤት የሆነ ቅጣት ነው። ይህ ቅጣት በግለሰቡ፣ በቤተሰቡ ወይም ሁለትና ሦስት ትውልድ ከዚያም በላይ በመሄድ፣ አሰበሰዚያም አገርን ባካለለ መልክ ሊፈጸም ይችላል"[18]።

አንድ ሰው በእርግማን ውስጥ መውደቁን እንዴት ያውቃል የሚለውን ጉዳይ ጆን ኤክሃርት ራሳቸው በቀጥታ የጠቀሱት፣ ዴሬክ

---

[17] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 21። የዴሬክ ፕሪንስ መጽሐፍ አስተምህሮውን ያዋቀረው በሚከተሉት ሦስት መንገዶች ነው:— (1) በሕይወታችን ውስጥ መርገም ሚና በመጫወት ላይ ሳለ መሆኑ እንደምን ለማወቅ እንችላለን? (2) ከመርገም ለመላቀቅና ከሚያስከትለውም የከፋ ሕይወት ለማምለጥ ምን ልናደርግ ይገባናል? (3) የእግዚአብሔርን በረከት እንደምን መጋራት እንችላለን"

[18] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 4።

ፕሪንስን ነው[19]። እኛም ፕሪንስን በቀጥታ ጠቅሰን፣ የኤክሃርትን ጭማሪ እናስከትላለን፦

> "በግሌ ካካሄዱሁት የረጅም ጊዜ ጥናትና ከተለያዩ ሰዎች ካካበትሁት ግንዛቤ በመነሣት፣ የመርገምን ምልክቶች በሰባት የተለያዩ ገጽታዎች ለመከፋፈል ችያለሁ[20]። እነኚህን እኔ ያዘጋጀኋቸውን ዝርዝሮችና ሙሌ ያቀረባቸውን መግለጫዎች ሳወዳድራቸው እጅግ ተቀራራቢና ተመሳሳይ በመሆናቸው መደነቄ አልቀረም።"[21]

1. "የአእምሮ ወይም የስሜት መታወክ
2. በተደጋጋሚ ለበሽታ መጋለጥ (በተለይ በውርስ የተላለፈ ሲሆን)
3. መካንነት በተለይም ከውርጃና ከመሳሰለው ሁኔታ ጋር የተያያዘ ሲሆን፣
4. ያላቋረጠ የገንዘብ ዕጥረት፣
5. የጋብቻ መፍረስና የቤተሰብ መከፋፈል፣
6. ያላቋረጠ የገንዘብ ዕጥረት (ችግር)፣

19 ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 14። ነገር ግን እኛ ከተጠቀሰው ከምንጠቅስ ፕሪንስን በቀጥታ በመጥቀስ የኤክሃርትን ጭማሪ ደግሞ ከራሳቸው መጽሐፍ እንወስዳለን።

20 አንባቢያን ልብ ሊሉት የሚገባ ነጥብ፣ ይህ ጉዳይ የግለሰቡ የግል ተሞክሮ መሆኑን ነው። ክርስቲያን አስተምህሮውን በግለሰቦች ተሞክሮ ላይ ሲመሠርት እንዴት ይችላል? ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ የሚያስተምሩትን ትምህርት በተሞክሯችን ማዋዛት፣ ትክክለኝነቱን በግል ልምምዳችን ማድመቅ ተገቢ ነው። ነገር ግን የሰዎችን የግል ተሞክሮ የሕይወት መመሪያ ማድረግ፣ በዕንስ ሐሳብ ደረጃ ስሕተት ነው። መጽሐፍ ቅዱስም ይህ ዐይነቱን አካሄድ አይደግፍም።

21 የነገረ መለኮት ሰዎች፣ *"exegesis"* እንዲሁም *"eisegesis* የሚሏቸው ሙያዊ ቃላት አሏቸው። የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ፣ ትምህርቱን በትክክል በመፈከር/በመተንተን ወደ አንድ ድምዳሜ ላይ መድረስ ነው። ሁለተኛው ግን የራስን ሐሳብ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እየሸነቀሩ ማስገባት ነው። እስቲ ይህን አሳብ ዴሬክ ፕሪንስ እያሉ ካሉት ጋር ያነጻጽሩ።



7. ለአደጋ 'በተደጋጋሚ' የተጋለጡ መሆን፣ በቤተሰብ ውስጥ ተደጋግሞ የደረሰ ሕይወትን በገዛ እጅ የማጥፋት ታሪክ ወይም ያለ ዕድሜ መቀሠፍ"[22]

እነዚህን የዴሬክ ፕሪንስን ሰባት ነጥቦች፣ በጉዳዩ ላይ መጻሕፍት ያሳተሙ እንዲሁም በርእሰ ጉዳዩ ላይ ትምህርት የሚሰጡ ሰዎች ሁሉ አዘውትረው የሚጠቅሷቸው ነጥቦች ናቸው። ጆን ኤክሃርት ራሳቸው እነዚህን ሰባት ነጥቦች ከፕሪንስ በቀጥታ ከጠቀሱ በኋላ፣ የራሳቸውን ተሞክሮ በእማኝነት በመጥቀስ ሁለት ተጨማሪ ነጥቦችን ያክላሉ (ያስተዋውቃሉ)፦

> "እኔ ደግሞ በአገልግሎታችን ዘመን ካየሁት በመነሣት[23]፣ ተጨማሪ ሁለት ምልክቶችን ጨምሬአለሁ። እነዚህም፦

1. በሌሎች ሰዎች ፊት ሞገስ ማጣት፤ አእምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ወሲባዊ፣ ጉዳትና መወገድን ይጨምራል። ሞገስ አልባ መሆን፣ መጠላት፣ መገለል።
2. ተቅበዝባዥነት፣ መባከን፣ ዕረፍት የለሽ ሕይወት መኖር፣ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው፣ ከከተማ ከተማ፣ አንዱን ሥራ ለቆ ሌላውን፣ ከአንዱ ኅብረት ወደ ሌላው

22 ጸሐፊው፣ በቀጣዩቹ ተከታታይ ምዕራፎች እነዚህን ጉዳዮች በስፋት ይዘረዝራሉ። ፕሪንስ ከእነዚህ ውስጥ የትኛው ወይም ምን ያህሉ፣ በምን ያህል መጠን ተደጋግሞ ሲከሠት አንድ ክርስቲያን በመርገም ውስጥ ነው እንድንል ያደርገናል በሚለው ጉዳይ ላይ ቁርጥ ያለ መልስ ያልሰጡት። ነገር በእያንዳንዱ ሰው የግል አስተያየት ላይ የሚወድቅ አሻሚ ምላሽ እንዲህ ሲሉ ሰንዝረዋል፣ "ከእነዚህ የመርገም ምልክቶች አንዱ ወይም የሁለቱ በአንድ ሰው ላይ መታየት ያንን ሰው በመርገም ሥር እንዳለ አድርጎ ሊያስቈጥረው አይችልም። ዳሩ ግን አብዛኞቹ ምልክቶች ሲታዩ ወይም በተደጋጋሚ ሲደርሱ ስለዚያ ሰው ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ለመናገር እንችላለን። ሆኖም በእርግጠኛነት ለመናገር የምንችለው በመንፈስ ቅዱስ ስንመራ ብቻ ነው" ዴሬክ ፕሪንስ፤ *በረከት ወይስ መርገም*፤ ገጽ 34።

23 እነዚህ ሰዎች አስተምህሮ የሚያዋቅሩት፣ ከተሞክሯቸው በመነሣት እንደ ሆነ ልብ ይሏል።

ኅብረት መባከን፣ አዘወትሮ የዘላንነትና የተቅበዝባዥነት ሕይወት መኖር"[24]።

## አጭር ቀጭን ግምገማ

"ክርስቲያን በወላጆቹ መርገም ውስጥ ሊወድቅ ይችላል" የሚለውን አስተምህሮ ሙሉ ለሙሉ ብንቀበል እንኳ፣ እነዚህ ዴሬክ ፕሪንስ የዘረዘሯቸው ስባት ነጥቦች እንዲሁም ጆን ኤክሃርት ያከሉባቸው ሁለት ጭማሪዎች፣ "በርግጥ አንድ ሰው በመርገም ውስጥ ነው ብለን በቍርጥ መናገር የሚያስችሉን ናቸውን?" የሚለውን ጥያቄ በብርቱ እንድንጠይቅ የሚያስገድዱን ናቸው። በአፀደ ሥጋ የሚኖር የሰው ልጅ ሁሉ፣ ክርስቲያንም ሆነ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ፣ ኢአማኒም ሆነ ህልዎተ እግዚአብሔርን የሚጠራጠር ጠርጣሪ...ሊያጋጥሙት የሚችሉ የሕይወት ገጠመኞች ናቸው። አንድም ሰው ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ ጽዱ ነኝ። አንዳቸውም ገጥመውኝ አያውቁም ማለት የሚችል አይመስለኝም። ምናልባትም የእንቅስቃሴው አስተማሪዎች ራሳቸው ከዚህ ሐቅ እምልጠዋል ማለት እጅግ ሲበዛ አስቸጋሪ ነው። ሕይወታቸውን በቅርበት ባናውቅም እንኳ፣ ከሰው ልጅ ተሞክሮ ይህ ይሆናል ብሎ ለማሰብ ወፈር ያለ እውር እምነት ይፈልጋል።

ይህ አስተሳሰብ በዝርዝር ያላብራራንውን ነገር ግን ታሳቢ አድርገን ያሰፍንውን ሌላ የነገረ መለኮት ፅንሰ እሳብ መለስ ብለን እንድንመረምር የሚያስገድደን ነው። ይኸውም:— *(1)* በርግጥ ክርስቲያን ችግር የሌለበት ምድራዊ ሕይወት እንደሚኖር መጽሐፍ ቅዱስ ዋስትና ሰጥቶአልን? *(2)* በምድራዊው ኑሮ ክርስቲያን የገንዘብ ችግር እንዲሁም የበሽታ ጣጣ እንደማይጐበኘው መጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጫና ተስፋ ሰጥቶአልን? እነዚህ በወኑ መተንተን ያለባቸው መሠረታውያን የነገረ መለኮት ጭብጦች ናቸው። በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ፣ "አባሪ" በሚል ርእስ እነዚህን ሁነኛ ጥያቄዎች

[24] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 14-15።



እንነጋገርባቸዋለን። ለአሁኑ ግን ሁለት መሠረታውያን ነጥቦችን ጠቆም በማድረግ፣ እነዚህ ዘጠኝ ዝርዝር ሐተታዎች ስሕተት መሆናቸውን ልሞግት[25]:—

1. *መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ሊያልፉ እንደሚችሉ በግልጽ ይናገራል፤*

**በናሙናነት የተወሰኑ ክፍሎችን እንመልከት:—**

*"35. ሴቶች ሙታናቸው ተነሡላቸው። ሌሎቹ ደግሞ የተሻለውን ትንሣኤ ለማግኘት ሲሉ፣ መትረፍን ንቀው ለሞት ለሚዳርግ ሥቃይ ራሳቸውን ሰጡ፤ ከዚህም ነጻ ለመውጣት አልፈለጉም። 36. አንዳንዶቹ መዘባበቻ ሆኑ፤ ተገረፉ። ሌሎቹ ደግሞ ታስረው ወደ ወህኒ ተጣሉ፤ 37. በድንጋይ ተወገሩ፤ በመጋዝ ለሁለት ተሰነጠቁ፤ ድንጋይ ተወገሩ፤ ለፈተና አልፈው ተሰጡ፤ በሰይፍ ተወግተው ሞቱ፤ እየተጐሳቈሉ፣ እየተሰደዱና እየተንገላቱ የበግና የፍየል ቈዳ ለብሰው ዞሩ፤ 38. ዓለም ለእነርሱ አልተገባቻቸውምና። በየበረሓውና በየተራራው፣ በየዋሻውና በየጕድጓዱ ተንከራተቱ። 39. እነዚህ ሁሉ ስለ እምነታቸው የተመሰከረላቸው ቢሆኑም ከእነርሱ ማንም የተስፋውን ቃል የተቀበለ የለም። 40. እግዚአብሔር ለእኛ የሚበልጥ ነገር ስላዘጋጀ፣ ያለ እኛ ፍጹማን ሊሆኑ አልቻሉም" (ዕብ. 11)።*

*"21. እኛ ግን ለዚያ እጅግ ደካሞች መሆናችንን እያፈርሁ እናገራለሁ። ማንም በድፍረት በሚመካበት ነገር ሁሉ እኔም ደፍሬ*

[25] ልብ ልናደርጋቸው የሚገቡ ሁለት መሠረታውያን ነጥቦች ያሉ ይመስለኛል:— ***አንደኛው፤*** በዝርዝሩ ውስጥ የተካተቱት ነገሮች ሁሉ የመርገም ውጤት ናቸው ብለን ብንቀበል ***ሁለተኛ፤*** ክርስቲያን በመርገም ውስጥ ይሆናል የሚለውን አስተምህሮ ብናምን እንኳ፣ የግለሰቡ ትምህርት በፍጹም ትክክል ሊሆን አይችልም። ከዚህ በታች የዘረዘርኋቸው ትችቶች እነዚህ ሁለት ነጥቦች ትክክል ናቸው ብዬ ባለብ እንኳ የሚከተለውን ዝርክርክ ውጤት ነው።

መመካት እንደምችል እንደ ሞኝ እናገራለሁ። 22. እነርሱ ዕብራውያን ናቸውን? እኔም ነኝ፤ እስራኤላውያን ናቸውን? እኔም ነኝ፤ የአብርሃም ዘር ናቸውን? እኔም ነኝ። 23. የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸውን? እንደ አበደ ሰው ልናገርና እኔ እበልጣቸዋለሁ፤ ደግሞም ብዙ ጊዜ በሥራ ደከሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ ታስሬያለሁ፤ ብዙ ጊዜ ተገርፌአለሁ፤ ብዙ ጊዜ ለሞት ተቃርቤአለሁ። 24. አይሁድ ለአርባ ጅራፍ አንድ የቀረው አምስት ጊዜ ገርፈውኛል። 25. ሦስት ጊዜ በዱላ ተደብድቤአለሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግሬአለሁ፤ ሦስት ጊዜ የመርከብ አደጋ ደርሶብኛል፤ አንድ ሌሊትና ቀን በባሕር ላይ አድሬአለሁ፤ 26. ብዙ ጊዜ በጉዞ ተንከራትቻለሁ፤ ደግሞም ለወንዝሙላት አደጋ፣ ለወንበዴዎች አደጋ፣ ለገዛ ወገኖቼ አደጋ፣ ለአሕዛብ አደጋ፣ ለከተማ አደጋ፣ ለገጠር አደጋ፣ ለባሕር አደጋ እንዲሁም ለሐሰተኞች ወንድሞች አደጋ ተጋልጬ ነበር። 27. ብዙ ጥሬአለሁ፤ ብዙ ደክሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ እንቅልፍ አጥቻለሁ፤ ተርቤአለሁ፤ ተጠምቻለሁ፤ ብዙ ጊዜ ምግብ ሳልቀምስ ኖሬአለሁ፤ በብርድና በራቁትነት ተቈራምጃለሁ። 28. ሌላውን ነገር ሳልቈጥር፣ ዕለት ዕለት የሚያስጨንቀኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሐሳብ ነው። 29. ደካማ ማን ነው? እኔስ አብሬ አልደክምምን? በኃጢአት የሚሰናከል ማን ነው? እኔስ አልቈጭምን?" (2ቆሮ 11)።

"32. እነሆ፤ ሁላችሁም በየፊናችሁ የምትበታተኑበት ጊዜ ይመጣል፤ ያም ጊዜ አሁን ነው። እኔንም ብቻዬን ትተዉኛላችሁ፤ ይሁን እንጂ አባቴ ከእኔ ጋር ስለ ሆነ ብቻዬን አይደለሁም። 33. "በእኔ ሰላም እንዲኖራችሁ፣ ይህን ነግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ" (ዮሐ. 16)።



"18. "ዓለም ቢጠላችሁ፣ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ ዕወቁ" (ዮሐ. 15)።

"22. የደቀ መዛሙርቱንም ልብ በማበረታታትና በእምነታቸው ጸንተው እንዲኖሩ በመምከር፣ "ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት በብዙ መከራ ማለፍ አለብን" አሏቸው" (ሐሥ 14)።

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ክርስቲያን በችግር ውስጥ ሊያልፍ እንደሚችል የሚናገሩ ናቸው። እርግጥ ነው ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የተመቻቸ ሕይወት ውስጥ ሊኖር ይችላል፤ በአንጻሩ ደግሞ በችግር፣ በህማም፣ በሥቃይ፣ በዕጦት፣ በበሽታ ወዘተ ውስጥ ሊያልፍ ይችላል። ይህ መፍቀሬ ንዋይ ለሆነው የሰው ልጅ፣ በተለይ ደግሞ ለድኅረ ዘመናዊው ትውልድ የሚጣፍጥ አሳብ አይደለም። ቃለ እግዚአብሔር ግን፣ "ችግር የለም" ሳይሆን የሚለን፣ "ችግር አለ" "ነገር ግን፣ በችግር ውስጥ ትልቁ እግዚአብሔር አብሮን አለ"። "ከችግሮቹ ይልቅ ከእኛ ጋር ያለው ጌታ ብርቱ ነው"። "ክርስቲያን ችግርን የሚፈራ ሳይሆን፣ ችግርን በቍርጠኝነት የሚጋፈጥ ሰማዕት ነው"... የሚለውን አሳብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያን በመሆናችን ብቻ ከሌሎች ሰዎች የተሻለ ምድራዊ ስኬት እንደሚያጋጥመን አይናገርም፤ ዋስትናም አይሰጠንም። ባይሆን በምናልፍባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ፣ ልዑል እግዚአብሔር አብሮን እንደሚሆን፣ እንደሚያጽናናን፣ ከጊዜያዊ ችግር የሚያልፍ ደስታና ሐሴት በልባችን እንደሚያኖር ወዘተ ዋስትና አለን።

## 2. ከዝርዝሮቹ መኻል አንዳንዶቹ እንደ መርገም የሚታዩ ሳይሆኑ፣ እንደ በረከት የሚቈጠሩ ሊሆኑ ይችላሉ።

ለምሳሌ ጆን ኤክሃርት ሥራ መቀያየር፣ የመኖሪያ ቦታ መቀያየር፣ በሥራ መጠመድ ወዘተ እንደ መርገም ጠቅሷቸዋል፤ እነዚህ ነገሮች እንደ በረከት አይቈጠሩም ቢባል እንኳ፣ እንደ

መርገም ግን ሊታዩ የማይችሉባቸው ብዙ አጋጣሚዎች ይኖራሉ፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ሰዎች እነዚህን በተቃራኒው መልክ እንደ በረከት ሊቆጥሯቸው ይችላሉ፡፡ ስለዚህ አንድን ነገር መጥፎ ነው ወይስ ጥሩ ነው የሚለውን ጉዳይ ለመበየን፣ "በማን እይታ?" "በየትኛው መስፈርት?" የሚሉትን መሠረታውያን ጥያቄዎች ያስነሣሉ፡፡ እነዚህ ጉዳዮች፣ በብዙ መልኩ አንጻራዊ ምልከታዎች እንጂ ነባራዊ መሠረት ያላቸው አይደሉም፡፡ ስለዚህ ሥራ መቀያየር፣ ቤት መቀያየር፣ ሰፈር መቀያየር ወዘተ ለጆን ኤክሃርት መርገም ቢሆኑ ሌላው ደግሞ እንደ በረከት ሊቆጠሩ የሚችሉ ናቸው፡፡

**3. የቀረቡት ዝርዝሮች፣ መርገምን በቍርጥ ለመወሰን የሚያስችሉ መስፈርቶች አይደሉም፡፡**

እኛ እንደ "መርገም" ያየናቸውን ነገሮች፣ እንደ ኪሳራ የሰፈርናቸው ገጠመኞች...የትልቅ ስኬት፣ የትልቅ በረከት ምክንያት የሆኑባቸው እጅግ በርካታ ገጠመኞች አሉን፡፡ በአንድ ወቅት ያሰለቀሰን ጉዳይ፣ የኋላ ኋላ የትልቅ በረከት ምንጭ ሆኖ አይተናል፡፡ ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ በሕይወታችን የሚያልፉ ነገሮች ሁሉ፣ "ለበጎ" ዐላማ መጥተው የሚሄዱ ነገሮች እንደ ሆኑ አበክሮ የሚገልጸው፡፡ እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ መጠናቸውንና ዐይነታቸውን ሉዓላዊው ጌታ እንደሚቈጣጠራቸው ይገልጻል፡፡ ውጤቱም ሆነ ዐላማው እኛ ቢገባንም ሆነ ባይገባንም (የሚከተሉትን ምንባባት በናሙናነት ይመለከቷል—ሮሜ 8፥28:35-39፤ 2ቆሮ. 4፥15፤ ሮሜ 5፥34፤ ዘፍ. 50፥20፤ ዘዳ. 8፥2:3:16፤ መዝ. 46፥1-2፤ ኤር. 24፥5-7፤ 2ቆሮ. 5፥1፤ ፊልጵ. 1፥19-23፤ 2ተሰ. 1፥5-7፤ ዕብራ 12፥6-12፤ ያዕ. 1፥3-4፤ 1ጴጥ. 1፥7-8)፡፡



**4. በመስፈርቱ ውስጥ የተካተቱት እንዳንዶቹ ነጥቦች የሰውን ባሕርይ እንዲሁም የሰው ልጅ የሚኖረውን ሕይወት በትክክል ያገናዘቡ አይደሉም፡፡**

ማነው ሳይፈራ ሳይቸር የሚኖር? "የአእምሮና የስሜት መታወክ" ሳይገጥመው የሚችል ሰብአዊ ፍጡር የቱ ነው? በርግጥ ደህና ይህን መሰል ሁኔታዎች በሕይወታችን እውን የማይሆኑ ከሆነማ፣ ወገኖቼ ያለነው መንግሥተ ሰማይ ነው ማለት ነው፡፡ "እንባዎችን ሁሉ ከዐይናቸው ላይ ያብሳል" በተባለበት፣ ነገር ግን ይመጣል ብለን በምንጠብቀው መጻኢ ዓለም ላይ እየኖርን ነው ማለት ነው፡፡

ዴሬክ ፕሪንስ "በተደጋጋሚ ለበሽታ መጋለጥ (በተለይ በውርስ የተላለፈ)" መርገም ነው ብለውናል፡፡ ከወላጆቻችን የሚተላለፉ በሽታዎች መኖራቸው እሙን ነው፤ ነገር ግን የበሽታ ዕዳ ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ በረከቶችን ከቤተሰቦቻችን እንወርሳለን፤ ለምሳሌ አካላዊ ውበት፣ ሰል የሆነ ጭንቅላት ወዘተ፡፡ ስለዚህ መርገም ተላለፈ እንደ ተባለው ሁሉ በዚህ መልክ የሚመጣውንስ በረከት እንዴት ልናሰላው ይሆን? በርግጥ እነዚህን ነገሮች ቃለ እግዚአብሔር መርገም ይላቸዋል? የሚላቸው ከሆነ እነዚህን መርገም የሚላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የት ቦታ ነው የሚገኘው? ይህን ጉዳይ ኋላ ዘለግ አድርገን እንመለከተዋለን፡፡

**5. በዝርዝሩ ውስጥ ከተካተቱት መኻል አንዳንዶቹ በእኛ መልካምነት እውን የሚሆኑ ነገሮች ላይሆኑ ይችላሉ፡፡**

ለምሳሌ ትዳርን ያለማፍረስ፣ በእኛ መልካምነት ብቻ የሚወሰን ላይሆን ይችላል፡፡ ተጣማሪው ወገን አልፈልግም፣ አሻፈረኝ ብሎ ትዳር ሊያፈርስ ይችላል፡፡ አንዱ ወገን በወሰደው እሉታዊ አካሄድ ሌላው ወገን እኔ በመርገም ውስጥ ነኝ ማለት እንዴት ይችላል? በአንድ አገር ኋላቀርነት፣ ጦርነት፣ እድሎ፣ ሙስና ወዘተ ሊኖኝ የሚችለው፣ በእኛ መልካምነት ሳይሆን በአገር መሪ

ፖለቲከኞች እኩይ አስተዳደር ሊሆን ይችላል። አሜሪካን አገር የተወለደ ልጅ ኢትዮጵያ ውስጥ ከተወለደው ይልቅ ጥሩ ዕድል እንዳለው ይገመታል። ስለዚህ ኢትዮጵያውያን በመርገም ውስጥ ናቸው አሜሪካውያን በበረከት ውስጥ ናቸው ማለት እንዴት ይቻላል?

እንዲያውም እንደ ሳውዲ ዐረብያ ያሉ የዓለማችን ሀብታም አገሮች፣ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። እንደ ጃፓን በሀብትና በሥልጣኔ የናጠጡ አገሮች የሺንቶና የቡድሃ ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። በቅርቡ በወጣ አንድ መረጃ፣ 47 በመቶ የሚሆነው የቻይና ነዋሪ አምላክ አለ ብሎ እንኳ አያምንም። በተመሳሳይ መንገድ 31 በመቶ ጃፓናዊ በህልዎተ እግዚአብሔር አያምንም[26]። የቻይናውን እንኳ ብንተወው፣ ቢያንስ አንድ ጃፓናዊ ከመደበኛው ኢትዮጵያዊ፣ ዐሥራ ስድስት ዕጥፍ የተሻለ ሕይወት እንደሚኖር ስልካችንን በመጠቀም ማጣራት እንችላለን[27]። ጣዖት አምልኮ ወይም በእግዚአብሔር መኖር ያለማመን ለመርገም አንዱና ትልቁ መስፈርት ከሆነ፣ ይህን የዴሪክ ፕሪንስ አስተምህሮ፣ ከዓለማችን ነባራዊ እውነታ ጋር እንዴት ማደላደል ይቻል ይሆን?

በአጠቃላይ እነዚህን መስፈርቶች ተከትሎ አንድ ሰው በመርገም ውስጥ ነው ወይስ አይደለም፣ የሚለውን ጉዳይ ለመበየን እጅግ ሲበዛ አስቸጋሪ ነው። ለዚህም ሳይሆን አይቀርም ዴሬክ ፕሪንስ፣ አንድ ሰው በመርገም ውስጥ መሆኑን ወይም ያለመሆኑን "በእርግጠኛነት ለመናገር የምንችለው፣ በመንፈስ ቅዱስ ስንመራ ብቻ

[26] *The Washington Post May 23, 2013*
*https://www.washingtonpost.com/news/worldviews/wp/2013/05/23/a-surprising-map-of-where-the-worlds-atheists-live/?utm_term=.a2cfff4f80b0*

[27] *OECD Better Life Index* የአንደ ጃፓናዊ የዓመቱ አማካኝ ገቢ 28,641 ዶላር ሲሆን፣ እንደ *World Bank Open Data* በ2016 ዓ.ም የአንድ ኢትዮጵያዊ ዓመታዊ ገቢው በአማካኝ 1730 ዶላር ነው።

*https://data.worldbank.org/indicator/NY.GNP.PCAP.PP.CD*



ነው"[28] የሚል መሺለኪያ ያበጁት[29]። ይሻላቸዋል! መስፈርታቸው ነባራዊ ሊሆን በጭራሽ አይችልም።

በዝርዝሩ ውስጥ ያካተቷቸው ነገሮች ሁሉ፣ የመርገም ውጤት ናቸው ብለን ብናምን እንዲሁም ክርስቲያን በመርገም ውስጥ ይሆናል የሚለውን አስተምህሮ ትክክል ነው ብለን ብንቀበል እንኳ፣ እኔ ከዚህ በላይ የዘረዘርኳቸው አምስት ነጥቦች። መስፈርቱ ከብዙ አንጻር ቢሆን ስሕተት ባይሆን አንጻራዊ መሆኑን አመላካች ነው።

## ለ. ክርስቲያንን መርገም ውስጥ ይጥሉታል እንዲሁም ከመርገም ለመውጣት ማድረግ ያለበት የተባሉትን ነገሮች ደግሞ እንመልከት

በመርገም ውስጥ የሚጥሉን፣ "ጣዖትን ማምለክ"፣ መናፍቃዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መግባት[30]፣ "የግብረገብ ችግር" (ለምሳሌ ወላጆችን ያለማክበር እንዲሁም ከትዳር ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ)[31]፣ "ፀረ አይሁዳዊነት"[32]፣ "ሕግ አክራሪነት

[28] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 34።

[29] ነገሩን ምን ያህል አንጻራዊ/ጎሲናዊ ብያኔ እንዳደረጉት አንባቢ ልብ ይበል። አንባቢዎቹን የማበረታታው ሌላው ነገር፣ (1) በዝርዝሩ ውስጥ የተካተቱት ነገሮች ሁሉ የመርገም ውጤት ናቸው ብለን ብንቀበል (2) ክርስቲያን በመርገም ውስጥ ይሆናል የሚለውን አስተምህሮ ትክክል ነው ብለን ታሳቢ ብናደርግ እንኳ፣ የግለሰቦቹ ትምህርት በፍጹም የተሳከረ መሆኑን ለመረዳት እያንዳንዱን መስፈርት ቆም ብለው እንዲመረምሯቸው ነው።

[30] መርገም ውስጥ ይከታሉ የተባሉት መናፍቃዊ እንቅስቃሴዎች፣ የይሖዋ ምስክሮች፣ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንና የሞርሞን ሃይማኖት ይገኙበታል ገጽ 52።

[31] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 57 እስከ 61።

[32] ዝኒ ከማሁ፣ ከ62 እስከ 68። ይህ ጉዳይ ራሱን የቻለ ትልቅ ጥራዝ የሚያጸፍ ትችት ሊወጣው ይችላል።

ወይም ሥጋዊነት"[33]፣ "ስርቆት፣ አጭበርባሪነት፣ እግዚአብሔርን ማታለል"[34]፣ አሉታዊ ንግግር[35]።

ልብ እንበል፣ "ክርስቲያን በመርገም ውስጥ ሊወድቅ ይችላል" ተብሎ፣ "ጣዖትን ማምለክ" እንዲሁም "መናፍቃዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መግባት" የሚለው ገለጻ፣ በርካታ ጥያቄ ይጭራል። አንደኛ፣ ክርስቲያን እንዴትና በምን አግባብ ጣዖትን ሊያመልክ እንዲሁም መናፍቃዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ገብቶ "ክርስቲያን" ሊባል ይችላል? የእንቅስቃሴው መምህራን ራሳቸው "ክርስቲያን ማነው?" ለሚለው የሰጡት ገለጻ፣ "ጌታን የሚወድ"፣

[33] ስዚህ እንደ ምሳሌ ከቀረቡት ውስጥ፣ "ከእግዚአብሔር መገለጥ ምስጢር ይልቅ፣ ለሥነ መለኮት ትምህርት አክብሮት መስጠት...በእምነት ከመጓዝ ይልቅ በአእምሮ ምሪት መተማመን...ከፍቅር ይልቅ ለሕግ መገዛት" ዴሬክ ፕሪንስ፤ *በረከት ወይስ መርገም*፤ ከገጽ 69 እስከ 76። አእምሮን የአምላክ ባላንጣ አድርጎ ማቅረብ፣ የብዙ ስሕተት ትምህርቶች ዐይነተኛ መለያቸው ነው። መጽሐፍ ቅዱስን የሰጠን አምላክ ነው አእምሮንም የሰጠን። ከእንስሳ የለየን ትልቁ የአምላክ በረከት አእምሮ ነው። እነዚህ ሰዎች ግን ይህን ትልቅ በረከት በማሰጣል እንስሳ ኑሯ ሊቀላቀሉን ይፈልጋሉ። ሰው አእምሮውን ከጣለ ምን ሊተርፍለት ይችላል፣ እንስሳ ከመሆን በቀር።

[34] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 77 እስከ 80።

[35] ዝኒ ከማሁ፤ ከገጽ 90 እስከ 99። ለረጅም ጊዜ ዴሬክ ፕሪንስ፣ ከእምነት እንቅስቃሴ አስተምህሮ ጋር ንክኪ ያላቸው አይመስለኝም ነበር። ኋላ ግን በግልጽ የተገነዘብሁት፣ ከአስተምህሮውም ሆነ ከእንቅስቃሴው አንጋፋ መምህራን ጋር ወዳጅነት እንደ ነበራቸው ነው። ለምሳሌ በወርኀ ሐምሌ 1976 ዓ.ም ኬኔት ኮፕላንድና ዴሬክ ፕሪንስ በአሜሪካን አገር በጥምረት የጀማ ሉበከትና የትምህርት ዐውደ ጥናት አዘጋጅተው ነበር። ስለመርገም ትንታኔ ያቀረቡበት መጽሐፋቸው፣ ክርስቲያን ቴዷር መሆን አለበት እንዲሁም መታመም የለበትም የሚለውን አስተሳሰብ ታሳቢ ያደረገ ነው። ልክ እንደዚሁ ሁሉ፣ አዎንታዊ ንግግሮች አዎንታዊ ውጤት እንደሚያስከትሉ አሉታዊ ንግግሮችም አሉታዊ ውጤት እንደሚያመጡ በርካታ ቦታ ገልጸው እናነባለን። አጋንንትን ማስወጣት በተመለከተ ኬኔት ሃጊን ቃል ከተናገርሁ ይበቃል ባይ ሲሆኑ፣ ዴሬክ ፕሪንስ ግን በቂ ጊዜ ሰጥቶ መጸለይ...ያስፈልጋል ባይ ናቸው። ምናልባት ልዩነቱ ይህ ብቻ ሳይሆን ይቀራል?



"ዳግም የተወለደ"፣ "መንፈስ ቅዱስ የተሞላ"[36] ብለው ነው። ታዲያ በምን አግባብ ነው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነ፣ ጌታን የሚወድ...ሰው ጣዖትን የሚያመልከው። ሁለተኛ፣ ቤተሰቦቹ ጣዖትን በማምለካቸው ምክንያት፣ ግለሰቡ መርገም ውስጥ የሚወድቅበት አንዳችም ምክንያት የለም። ይህን ጉዳይ ኋላ በስፋት እንመረምረዋለን።

ኀጢአት ሁሉ በእምላክ ፊት ጸያፍ ተግባር ነው። ነገር ግን አማኝ በኀጢአት በወደቀበት ጊዜ ሁሉ በመርገም ውስጥ ይወድቃል ለማለት የሚያስችል፣ አንዳችም የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ የለም። በመሠረቱ የእንቅስቃሴው መምህራን ራሳቸው፣ "አጹብ ወቅዱስ" ነን ኀጢአት ዝር ብሎብን አያውቅም የሚሉ አይመስለኝም። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ኀጢአት የለብንም ብንል እግዚአብሔርን ሐሰተኛ እናደርገዋለን" ይላል (1ዮሐ. 1፥8-10፤ እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመልከቷል ኢዮ. 15፥14፤ 25፥4 ኤር. 2፥35፤ ዮሐ. 3፥33፤ 1ዮሐ. 5፥10)። ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ፣ የእንቅስቃሴው መምህራን ራሳቸው በየቀኑ በመርገም ውስጥ እየወደቁ፣ በየቀኑ ይነሣሉ ማለት ነው።

እነዚህ መርገሞች የሚሰበሩት በሚከተለው አምስት መልኩ እንደ ሆነ ዴሬክ ፕሪንስ ያስረዳሉ:—

1. "በክርስቶስ ስለ ማመንህና ስለ እንተም መሥዋዕት ሆኖ ስለ መሞቱ መስክር (ዐውጅ)"[37]፣
2. "ስለ ዐመፀኛነትህና ስለማንኛውም ኀጢአቶችህ ንስሓ ግባ"[38]፣
3. "ስለ ማንኛቸውም በደሎችህ ይቅርታን ጠይቅ"[39]፣
4. "የበደሉህን ሁሉ ይቅር በል"[40]፣

[36] ዴሬክ ፕሪንስ፤ *በረከት ወይስ መርገም አንዱን ምረጥ*፤ 1989 ዓ.ም፣ ገጽ 50።

[37] ዴሬክ ፕሪንስ፤ *በረከት ወይስ መርገም አንዱን ምረጥ*፤ ገጽ 141።

[38] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 142።

[39] ዝኒ ከማሁ።

5. “ከእስማትና ጥንቈላ ጋር ያለህን ግንኙነት ፈጽሞ እቋርጥ”[41]::

ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤን በመመስከር ሰዎች ወደ ድነት እንዲመጡ ማበረታታት እንዳለበት እሙን ነው:: ነገር ግን በሥራ መደራረብም ሆነ በሌላ የተለየ ምክንያት ይህን ባለማድረጉ መርገም ውስጥ ይወድቃል ብሎ ማስተማር፣ ሲበዛ እንግዳ ነው:: ታላቁ ተልእኮን ያለመከወኑ ኀጢአት ሊሆን ይችል ይሆናል፣ ነገር ግን ከዚያ ባለፈ ይህን ያለማድረግ መርገም ውስጥ ያጥላል ማለት ፍጹም ስሕተት ነው::

ክርስቲያን ስለማናቸውም ኀጢአት፣ ንስሓ መግባት እንዳለበት ሁላችንንም ያስማማል:: ነገር ግን ይህ እስከሚሆን ግለሰቡ በመርገም ውስጥ ይወድቃል ማለት ስሕተት ነው:: በተጨማሪ ዳግም የተወለደ ክርስቲያን አስማትና ጥንቈላን እንዴት ሊለማመድ ይችላል? ይህን የሚያደርግስ ክርስቲያን በምን መስፈርት ክርስቲያን ነው ማለት እንዴት ይቻላል?

በአጠቃላይ ክርስቲያንን በመርገም ውስጥ ይጥሉታል እንዲሁም አንድ ክርስቲያን በመርገም ውስጥ እንደ ወደቀ ምልክት ናቸው የተባሉት ዝርዝሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም:: እንዲያውም በሰዎች አንጻራዊ ምልከታ ላይ መሠረት ያደረጉ አስተሳሰቦች ናቸው:: ከዚህ ባለፈም ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ በማመኑ ባገኘው ትልቅ ዐርነት ላይ እንዳይኀደድ የሚያደርጉ ሰብአውያን ቀንበሮች ናቸው::

## መርገምና ከወላጅ የሚተላለፉ በሽታዎች

ይህን ርእስ ከላይ በስፋት እንደምንነጋገርበት ገልጸን ነበር፤ አሁን በቅርበት እንመርምረው::

---

[40] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 143::

[41] ዝኒ ከማሁ::



በቤት ለቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ፣ ፕሮግራም መሪው ከታዳሚው የጸሎት ርእስ መጠየቅ ጀመረ:: እንዲት እኅት፣ “ወገኖቼ መርገም እንዲሰበር ጸልዩልኝ” አለች:: ብዙዎቻችን በግብዣውያኑ መሚ እንደ ደረቀ እስከሬን ክው ብለን ቀረን:: “ምን ማለት ፈልገሽ ነው?” አለ መሪው፣ መገረምንና ግራ መጋባትን በቀላቀለ ፈገግታ:: “አባቴ ክፉኛ ይቈጣ ነበር” አለች እኅታችን ደልደል ብላ:: “ታዲያ ቍጣው የነደደ ጊዜ፣ እንኳን ሰው ተሰባሪ ዕቃ እንኳ በፊቱ የመቆም መብት የለውም፤ በቻይና ካራቴ እየተወናጨፈ እምሽክ ያደርጋቸዋል:: ሰውም ቢሆን ዕጣ ፈንታው ከዕቃዎቹ አይለይም:: ይህ የቍጣ መርገም በእኔም ሆነ በታላቅ እኅቴ ላይ ሰፍሮብናል:: ስንቈጣ የምንሆነውን ነገር፣ የሚያደርገንን ነገር በውል አናውቀውም፤ ምላጭ ከሚያስውጠው አልሃችን ጋር ተደምሮ ለምንም ነገር የምንመለስ ሰዎች አንሆንም”:: ፕሮግራም መሪው፣ “መቈጣት የሥጋ ሥራ እንደ ሆነ፣ በገላትያ 5÷16:20 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል:: ከዚህ ባለፈ ግን በመርገም ውስጥ ነኝ የሚለው አነጋገርሽ ግልጽ አይደለም” አላት:: የወንድማችን መልስ እኅታችንን ሊያረካት አልቻለም:: “ግድ የላችሁም እየሰበራችሁ ጸልዩልኝ! ከዘር ማንዘር ሊንከባለል የመጣ የቍጣ እርግማን እኔና እኅቴን እየተጫወተብን ነው”::

ይህ፣ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት የተዘራ ክፉ ዘር ነው:: አረሙ ለረጅም ጊዜ ሳይነቀል የመቆየቱም ምክንያት እንደ ርቱዕ ትምህርት እየታየ ነው:: እንዲያውም የዚህ ተቃራኒው ትምህርት እንደ ኑፋቄ እየታየ መምጣቱ ነው ብል ግነት አይሆንም::

ብዙ ሳይንሳዊ ጥናቶች፣ የወላጆች ተጽእኖ በልጆች ላይ ከፍተኛ እንደ ሆነ ያስረዳሉ—እምነታዊውም ሆነ እሱታዊው:: ወላጆች ቤታቸውን ገነት እንዲሁም ገሀነም የማድረግ ክሂሎታቸው እጅግ ትልቅ ነው:: ስለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ ወላጆች ልጆቻቸውን ሳያስልሱ እንዲመክሩ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያስተምሩ፣ የበጐ ምግባር ተምሳሌት እንዲሆኑ የሚያስገነዝበው (ዘዳ. 6÷7-9፤ ኤፌ. 6÷4)::

አባቶችን በተመለከተ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንዲህ ይላሉ:—

"ትክክለኛና ቀና የሆነውን በማድረግ የእግዚአብሔርን (ያህዌ) መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤተ ሰቦቹን እንዲያዝ መርጬዋለሁ፤ ይኸውም እግዚአብሔር (ያህዌ) ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ ሁሉ እንዲፈጸም ነው" (ዘፍ. 18÷19)።

"አባቱም፣ 'ለምን እንዲህ ታደርጋለህ?' ብሎ ገሥጾት አያውቅም ነበር፤ አዶንያስም እጅግ መልከ መልካምና የአቤሴሎም ታናሽ ወንድም ነበር" (1ነገ. 1÷6)።

"ንጉሡም እጅግ አዘነ፤ በቅጽር በሩ ዐናት ላይ ወዳለችው ቤት ወጥቶ አለቀሰ፤ ሲሄድም፣ "ልጄ አቤሴሎም ሆይ! ልጄ አቤሴሎም! በአንተ ፈንታ ምነው እኔ በሞትሁ ኖሮ! አቤሴሎም ሆይ፣ ልጄ፣ ጠየው ልጄ'ን!" ይል ነበር" (2ሳሙ. 18÷33)።

ሐዲስ ኪዳን የእናቶችን ተጽእኖ በተመለከተ እንዲህ ይላል:—

"ግብዝነት የሌለበት እምነትህን አስታውሳለሁ፤ ይህ እምነት ቀድሞ በአያትህ በሎይድ እንዲሁም በእናትህ በኤውንቄ ዘንድ ነበረ፤ አሁን ደግሞ በአንተ አንዳለ ተረድቻለሁ" (2ጢሞ. 1÷5)።

"ልጅቷም በእናቷ ተመክራ፣ 'የመጥምቁ ዮሐንስን ራስ በሳሕን ላይ አድርገህ አሁኑኑ ስጠኝ' አለችው...የተቈረጠውንም ራስ በሳሕን ላይ አድርገው ለልጅቱ ሰጧት፤ ልጅቱም ወስዳ ለእናቷ ሰጠች" (ማቴ. 14÷8;11)።

የወላጆች ብቻ ሳይሆን፣ የአካባቢና የባልንጀራም ተጽእኖ በልጆች ሕይወት ውስጥ እጅግ ከፍተኛ እንደ ሆነ ይታወቃል። ነገር ግን ዴሬክ ፕሪንስና ባልደረቦቻቸው፣ ከጓደኛ የሚወረስ መርገም ከአካባቢ የሚወረስ መርገም ባለማለታቸው እናመሰግናቸዋለን።

## ተጽእኖና እርግማን

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ "ከዘር ማንዘር የሚተላለፍ እርግማን" ("generation curse") የሚል ቃል እንደ ሌሎ ስንቶች እናውቅ ይሆን። ያን ዐይነት አሳብ የያዘ የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባብ



የለም። አንድ ወዳጄ፣ "'ከዘር ማንዘር የሚተላለፍ እርግማን' የሚለው ትምህርት ብዙ ተቀባይነት ያገኘው፣ ሰዎች ላደረሱት ጥፋት፣ ላስከተሉት በደልና ግፍ ሙሉ ኀላፊነት ላለመውሰድ በሚያደርጉት ትንቅንቅ፣ እንደ መሸፈኛ ስለሚያገለግላቸው ነው" የሚለው አባባሉ፣ በተወሰነ ደረጃም እንኳ ቢሆን እውነትነት ያለው ይመስለኛል። የሥነ ልቡና ምሁራን፣ "ማንኛውም ሰው የማኅበረሰቡ፣ የአካባቢው፣ የባልንጀሮቹ እንዲያው በአጠቃላይ የአስተዳደጉ ውጤት ነው" የሚለው አነጋገራቸው፣ በብዙ መልኩ እውነትነት አለው። እንዲያውም አንዳንዶች ይህን እውነት ቀመስ አባባል ያለልክ በመለጠጥ፣ "ኀጢአተኛ የሚባል ሰው የለም ኀጢአተኛ አስተዳደግ እንጂ" ይሉናል። ማንም ሊክደው በማይችል መንገድ አስተዳደጋችን በሕይወታችን ውስጥ ትልቅ ለውጥ አስከትሏል፤ ማንነታችንን ይቀርጻል—በጥሩም ሆነ በመጥፎ ጐኑ። ግን ይህን እውነት ይዞ፣ ወላጆቼ ላይ ይታይ የነበረ ሥነ ምግባራዊ እክል ነው መርገም ሆኖ እኔ ላይ የዘመተው ማለት በፍጹም ስሕተት ነው።

የዚህ አስተምህሮ ቀማርያን "መተላለፍ" ተብሎ በአማርኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች ላይ የተተረጐመውን ቃል፣ (በእንግሊዝኛው *iniquity*) "ከትውልድ የሚተላለፍ እርግማን" ተብሎ መተርጐም ይችላል ባይ ናቸው። ለምሳሌ ወይዘሮ ማርሊን ሄኪ፣ "ኀላፊ የማትሆንበት፣ ነገር ግን የወረስኸው እርግማን ሊኖርብህ ይችላል"[42] ይላሉ። እንዲያውም "ኀጢአት ተደጋግሞ ከተሠራ ኀጢአት ብቻ ሳይሆን መተላለፍ *'iniquity'* በመሆን በዘረ ሐረግ ደም ውስጥ ይዛመታል፤ የወላጆችህ መተላለፍም ወደ አንተ ደምም ዘልቆ ሊሄድ ይችላል"[43] የሚል አስተምህሮ አላቸው።

በርግጥ በአማርኛችን፣ "መተላለፍ" (በእንግሊዝኛው *"iniquity"*) ተብሎ የተተረጐመው የዕብራይስጥ ቃል፣ "ወይዘሮዋ

[42] *Break the generational Curse*, ገጽ 15።

[43] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 12 እና 50።

የሚሉትን ዐይነት ትርጉም አለውን?" የሚለውን ጉዳይ፣ ዘለግ አድርገን እነመርምር፡፡ በብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ኀጢአት የሚለውን ቃል ለመወከል ሦስት የዕብራይስጥ ቃላት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነርሱም፦ "ሀዎን/አቮን" (עָוֹן)፣ "ሀታ/ኻታ" (חָטָא) እንዲሁም "ፓሻ" (פֶּשַׁע) ናቸው፡ የመጀመሪያው ቃል ማለትም "አቮን" (עָוֹן) በእንግሊዝኛው በአማርኛ ትርጉሞች ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ፣ "መተላለፍ" ተብሎ ተተርጕሟል (ለምሳሌ የሚከተሉት የእንግሊዝኛ ትርጉሞች "አቮን" የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል "መተላለፍ" ማለትም *"iniquity"* ብለው ተርጕመውታል *KJV, ESV, NASV, WEB*)[44]፡፡ "ሀዎን" በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ 229 ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ ዐቢይ ትርጕሙም ስሕተት ማለት ነው፡፡ ተኳሽ ሊመታ ያሰበውን ዐላማ ሲስት፣ ጥይቱ ዐላማውን ስቶ/ተላልፎ ሲሄድ፣ እንደ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ መተላለፍ ማለት ዐላማን ከመሳት አንጻር እንጂ፣ ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው ሰው መሻገርን/መዛመትን በሚያሳይ መልኩ አይደለም የተጠቀሰው (ለምሳሌ የሚከተሉትን ምንባባት ይመለከቷል ዘፍ. 4÷13፤ 1ሳሙ. 20÷1፡8፤ 25÷24)፡፡

ሁለተኛው ቃል፣ "ኻታ" (חָטָא) ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን 595 ጊዜ ግልጋሎት ላይ የዋለ ሲሆን፣ የተጠበቀውን መስፈርት ያለማሟላት፤ ከመስፈርቱ ማጠር/ጉድሎ መገኘት ማለት ነው (ለምሳሌ የሚከተሉትን ምንባባት ይመለከቷል ኢዮ. 5÷24፤ 2ነገ. 18÷14፤ ዘፀ. 5÷16)[45]፡፡

[44] C. R. Cover, "Sin, Sinners (OT)", *The Anchor Bible Dictionary,* (Vol. 6 pp. 31-40, 1992), 31.

[45] ለበለጠ መረጃ የሚከተለውን መጽሐፍ ይመለከቷል— James Swanson, *Dictionary of Biblical Languages With Semantic Domains: Hebrew (Old Testament),* electronic ed. (Oak Harbor: Logos Research Systems, Inc., 1997).



ሦስተኛው ቃል፣ "ፓሻ" (פֶּשַׁע) ሲሆን፣ በብሉያት ቃሉ 135 ጊዜ ያህል ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ትርጕሙም ማመፅ፣ አሻፈረኝ ማለት፣ ሕግን ያለመታዘዝ ነው[46]፡፡

እነዚህ ቃላት ኀጢአት የተለያየ ባሕርይ እንዳለው የሚያሳዩን ቢሆኑም እንኳ፣ እንዳችም የትርጉም ልዩነት ሳይኖራቸው በተወራራሽነት ግልጋሎት ላይ የዋሉባቸው ቦታዎች ግን እጅግ ብዙ ናቸው (መዝ. 32÷5፤ ዕብ. 10÷17፤ ሉቃ. 13÷27)፡፡ የቃላትን አማራጭ ትርጉም ተከትለው የሚሄዱ የአስተምህሮ ቀመራዎች፣ እጅግ ብዙውን ጊዜ ስሕተት ሆነው የሚገኙት በዚህ ምክንያት ነው፡፡

በዘፀአት 20÷5 ላይ "አቮን" (עָוֹן) በአማርኛችን "መተላለፍ" ተብሎ የተተረጐመው ቃል፣ ግልጋሎት ላይ የዋለው፣ ሁለተኛውን ሕግ ያለመታዘዝ፣ ሕጉን ስቶ/አፍርሶ መሄድ በሚለው ትርጕሙ እንጂ ማርሲን ሄኪ እንደሚሉት፣ ከወላጅ ወደ ልጅ መዛመትን ለማመልከት አይደለም[47]፡፡

ዘፀአት 20÷5-6 በተመለከተ ልብ ልናደርገው የሚገቡን ቍም ነገሮች አሉ፤ ይኸውም 1. እርግማን የሚል ቃል በዚህ ቦታ ተጠቅሶ አናገኝም፡፡ ክፍሉ ከሦስት እስከ አራት ትውልድ ይተላለፋል የሚለው እርግማንን ሳይሆን፣ ጣዖትን በማምለክ እግዚአብሔርን መበደል ነው፡፡ 2. እግዚአብሔር አምላክ በአንክሮ የሚያስጠነቅቀው ጉዳይ፣ ጣዖትን ማምለክ በተከታታይ ትውልዶች ውስጥ ከፍተኛ ተጽእኖ እንደሚያስከትል ነው፡፡ 3. የጣዖት አምልኮው የሚቀጥል ከሆነ፣ የሚያስከትለውም መዘዝ በሦስትና በአራት ትውልድ የሚቆም አይሆንም፡፡ 4. ፍርዱ ይተላለፍባቸዋል የተባሉ ሰዎች፣ ጣዖትን በማምለክ ለአምላክ ያላቸውን ጥላቻ የሚገልጹ ሰዎችን ነው፡፡ 5. እስከ ሦስትና እስከ አራት ትውልድ ይተላለፋል በተባለበትም ዐውደ

[46] ዝኒ ከማሁ፡፡

[47] ማርሲን ሄኪን ጨምሮ ብዙዎቹ የእንቅስቃሴው መምህራን፣ ነገረ መለኮትን ኮሌጅ ገብተው በሥርዐቱ የተማሩ ሰዎች ያለመሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡

ምንባብ ውስጥ፣ የአምላክ ምሕረት እስከ ሺህ ትውልድ ይተላለፋል ተብሏል (ሮሜ 5÷20)።

በአዳምም ኀጢአት፣ የሰው ልጅ ሁሉ በኀጢአት እንደ ወደቀ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል (ኤፌ. 2÷3፤ ሮሜ 5÷12)። በዚህም አግባብ የሰው ልጅ ከውልደቱ ጀምሮ ኀጢአተኛ ነው (መዝ. 51÷5፤ ሮሜ 5÷13፤ 7÷9)። ኀጢአት በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ የገባው በአዳምና ሔዋን ኀጢአት በኩል፣ ብቻ እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል (ሮሜ 5÷17-19፤ 1ጢሞ 2÷14፤ 17÷26)። የአዳም ኀጢአት ወደ ሰው ሁሉ እንዳለፈ (1ቆሮ. 15:45)፣ በክርስቶስም ቤዛዊ/ወጂዊ ሥራ ቤተ ክርስቲያንም በክርስቶስ ደም ተገዝታለች፣ ታጥባለች፣ ጸድቃለችም (ሐሥ. 20÷28፤ ሮሜ 5÷9፤ 9÷22)።

## የመርገም ይተላለፋል አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግምገማ

ከዚህ በመቀጠል፣ "መርገም ከአናትህ፣ ከአባትህ … ይተላለፍብሃል" የሚሉ ሰዎች፣ አብዝተው የሚጠቅሷቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባት በቅርበት እንመረምራለን፤ ከፍሎቹ እነሆ:—

> "5. አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም፤ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ (ያህዌ ኤሎሂም) የሚጠሉኝን ልጆች ከአባቶቻቸው ኀጢአት የተነሣ፣ እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ድረስ የምቀጣ ቀናተኛ አምላክ (ኤሎሂም) ነኝ፤ 6. ነገር ግን ለሚወዱኝና ትእዛዛቴን ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ፍቅርን የማሳይ ነኝ" (ዘፀ. 20)።
>
> "9. ስለዚህም አምላክህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) አምላክ (ኤሎሂም) መሆኑን ዕወቅ፤ እርሱ ለሚወዱትና ትእዛዞቹን ለሚጠብቁት የፍቅሩን ኪዳን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ የሚጠብቅ ታማኝ አምላክ (ኤሎሂም) ነው። 10. ነገር ግን፣ የሚጠሉትን ዐይናቸው እያየ ይበቀላቸዋል፤ የሚጠሉትን ዐይናቸው እያየ ለመበቀል አይዘገይም" (ዘዳ. 7)።



ከሃምሳ ዓመት በፊት የተጻፉ የነገረ መለኮት መጻሕፍት[48]፣ እነዚህን ምንባባት በመጥቀስ መርገም ከቅድመ አያቶቻችን ይተላለፋል፣ ክርስቲያኖች ከዘር ለሚተላለፍ መርገም ሰለባ መሆን ይችላሉ የሚል ትምህርት አላስተማሩም። ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው የዚህ አስተምህሮ ቀዳማይ አመንጪ ዴሬክ ፕሪንስ ናቸው። ከሃምሳ ዓመት ወዲህ፣ "የትውልድን መርገም መሰበር" በሚል ርእስ በብዛት እየታተሙ የሚወጡ ጽሑፎች ግን፣ ክርስቲያን በወላጆቹ የዘር ሐረግ መርገም ሥር ሊወድቅ ይችላል ከማለትም ባሻገር፣ ይህን መርገም እንዴት መስበር እንደሚቻል በስፋት የሚያትት ሰፊ መድብል አቅርበዋል፤ ቀመር አበጅተዋል።

አስተምህሮዎች ሁሉ ከቅዱሳት መጻሕፍት አንጻር ይመሳከሩ እንዲሁም የትምህርቶቻችን ሁሉ ማዕከል ቅዱስ ቃሉ ብቻ መሆን አለበት የምንል ሰዎች፣ እነዚህን ስውር ምንባባት ለመተንተን አእምሮአዊ ስንፍናን ወግድ ማለት የግድ ይኖርብናል። አለያ ግን የሐሰት አስተምህሮ ማራገፊያ ከመሆን በጭራሽ አናመልጥም።

## የአበው ኀጢአት

ጣዖትን የማምለክ ኀጢአት፣ እስከ ሦስተኛውና አራተኛው ትውልድ ደረስ መዘዝ ሊኖረው ይችላል፣ የሚለው አሳብ በመጀመሪያ ተጠቅሶ የሚገኘው በዐሥርቱ ትእዛዛት ውስጥ ነው፣ "እኔ እግዚአብሔር አምላክህ (ያህዌ ኤሎሂም) የሚጠሉኝን ልጆች ከአባቶቻቸው ኀጢአት የተነሣ እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ድረስ የምቀጣ፣ ቀናተኛ አምላክ (ኤሎሂም) ነኝ" (ዘፀ. 20÷5)። ይህ ክፍል ከእግዚአብሔር ውጪ ያሉ ማናቸውም ዐይነት ጣዖታትን ማምለክ፣ የሚያስከትለው ቅጣት ምን እንደ ሆነ ይናገራል።

[48] ረዘም አድርጌ ገምቼ ነው።

እንዲያውም ከእስራኤላውያን ታሪክ በግልጽ የምንማረው፣ እስራኤል አምላኳ እግዚአብሔርን ትታ ፊቷን ወደ ጣዖት አምልኮ ስታዞር፣ አምላክ የተለያዩ ቅጣቶችን ያመጣባት እንደ ነበር፣ ከመላው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንማራለን። በዚህ ቦታ ልብ ልንላቸው የሚገቡ ሦስት መሠረታውያን ጉዳዮች አሉ። ይኸውም አንደኛ፣ እግዚአብሔር በርኅራኄው ታላቅ ስለሆነ ምሕረቱን እስከ ሺህ ትውልድ እንደሚያኖር፤ ሁለተኛ፣ ሲቈጣ ደግሞ ኀጢአትን/መተላለፍን (“አቮን” עָוֹן) እስከ አራት ትውልድ እንደሚቀጣ። ሦስተኛ፣ በዚህ ቦታ “መርገም” ይተላለፋል የሚል አንዳችም ቃል የለም። ከፍሉ ይተላለፋል የሚለው “ኀጢአትን” እንጂ መርገምን አይደለም። አራተኛ፣ ኀጢአት የሚያስከትለው ዳፋ/ውጤት ይከተላችኋል የተባሉት ደግሞ፣ ንስሓ ያልገቡ እንዲሁም ፊታቸውን ከእግዚአብሔር መልሰው ወደ ጣዖታት ዘወር ያደረጉትን ነው። አምላክን መሻትና ንስሓ መግባት የኀጢአት ሥርየት ቢሆንም፣ ይህን ሲያደርጉ ግን አይታይም።

በደብረ ሲና (በሲና ተራራ)፣ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ኪዳን አንደ ገባ እንመለከታለን። ከዚህም የተነሣ እስራኤል የእግዚአብሔር ሆነች። እስራኤል ይህን ኪዳን የመጠበቅ ሙሉ ኀላፊነት ነበረባት። ነገር ግን አምላኳን በመውደድም ሆነ በመታዘዝ ኪዳኗን መጠበቅ አልቻለችም። ጣዖታትን በማምለክ ኪዳኗን አፈረሰች። ይህ ደግሞ “መንፈሳዊ ዝሙት” በሚል ገለጻ ቀርቦ እንመለከታለን። ብዙ መዘዝ አንደሚያስከትልም በተደጋጋሚ ተነግሯል። ነገር ግን እስራኤል በተደጋጋሚ ስትወድቅ እንመለከታለን። ይህ ኀጢአት ድርጊቱን በፈጸሙት ሰዎች ላይ ብቻ የሚቆም ሳይሆን፣ ልጆቻቸውንም የሚነካ ብርቱ ጉዳይ እንደ ሆነ ተነግሯታል።

ይህ ኀጢአት፣ “እስከ ሦስትና አራት ትውልድ የሚተላለፍ” ነው ሲባል ምን ማለት ነው? እንዲያው በግልቡ ሲታይ አምላክ በአባቶች ኀጢአት ምክንያት፣ ልጆቹ ባላደረጉት ኀጢአት እንደሚጠይቃቸው፣ እንደሚቀጣቸው የሚናገር ይመስላል። ዘዳግም



24÷16 ይህን አማራጭ ትንታኔ ግን ይቃወማል፣ “አባቶች ስለ ልጆቻቸው፣ ልጆችም ስለ አባቶቻቸው አይገደሉ፤ እያንዳንዱ በራሱ ኀጢአት ይገደል”።

በርካታ የቅዱሳት መጻሕፍት ሊቃውንት፣ ልጆች ወደ እግዚአብሔር የሚመለሱ ከሆነ፣ ይህን መቅሠፍት ሙሉ ለሙሉ መቀልበስ ይችላሉ የሚል አቋም አላቸው። ምሳሌ ትልቁ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር ጆን ካልቪን፣ ዘፀአት 20÷5 በተመለከተ እንዲህ ይላል:—

> “እግዚአብሔር አምላክ የአባቶችን ኀጢአት ወደ ልጆች ጉያ አመልሳለሁ ሲል፣ ድርጊቱን ባልፈጸሙ ልጆች ላይ የአባቶችን ኀጢአት አመጣለሁ ማለቱ አይደለም። ምክንያቱም ልጆች ባላደረጉት ነገር ሊጠየቁ አይገባቸውምና። ነገር ግን እግዚአብሔር በአባቶቻቸውና ከእነርሱ በፊት በነበረው ትውልድ ኀጢአት የሚጠይቃቸው የእነርሱን መንገድ ከተከተሉ ነው”[49]

ልክ እንደ ጆን ካልቪን ሁሉ፣ አሜሪካዊ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሊቅ ዋልተር ካይዘር እንዲህ ይላሉ:—

> “ልጆች የአባቶቻቸውን ኀጢአት የሚደግሙ ከሆነ፣ እነርሱም እንደ ወላጆቻቸው በግል እግዚአብሔርን የመጥላታቸው ምልክት ነው”[50]

ስለዚህም ፕሮፌሰር ካይዘር፣ “የሚጠሉኝ” የሚለው ሐረግ አባቶችን ብቻ ሳይሆን ልጆችንም አመላካች ነው ባይ ናቸው።

ከዚህ ጋር ተመሳሳይ መልእክት ያለው በትንቢተ ኤርምያስ ላይ የሚገኝ ምንባብ እንዲህ ይላል:—

> 16. አባቶች ስለ ልጆቻቸው፣ ልጆችም ስለ አባቶቻቸው አይገደሉ፤ እያንዳንዱ በራሱ ኀጢአት ይገደል። 17. “አቤት፣ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ሰማያትንና ምድርን በታላቅ ኀይልህና በተዘረጋች ክንድህ ፈጥረሃል፤ የሚሳንህም አንዳች ነገር የለም።

[49] *John Calvin, Harmony of the Law, Vol. 2, “Exposition of the 2nd Commandment”*
[50] *Walter Kaiser, “Commentary on Exodus” in The Expositiors Bible Commentary, Vol. 2 (Zondervan: Grand Rapids, MI.: 1990), 423.*

> 18. ፍቅርና ቸርነትን ለአልፍ አእላፍ ታሳያለህ፤ ይሁን እንጂ የአባቶችን በደል ከእነርሱ በኋላ በሚነሡ ልጆቻቸው ጉያ ትመልሳለህ፤ ስምህ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሆነ፣ ታላቅና ኀያል አምላክ ሆይ፤ 19. ዕቅድህ ታላቅ፣ በሥራም ብርቱ ነህ፤ ዐይኖችህ የሰው ልጆችን መንገዶች ሁሉ ያያሉ፤ ለእያንዳንዱም እንደ መንገዱና እንደ ሥራው ትከፍለዋለህ"።

በአይሁድ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት የተዘጋጀ አንድ የትርጓሜ ሐተታ፣ "የአባቶችን በደል ከእነርሱ በኋላ በሚነሡ ልጆቻቸው ጉያ ትመልሳለህ" የሚለውን ክፍል በተመለከተ (ኤርምያስ 32÷17-19) እንዲህ ይላል:—

> "የአባቶች ኃጢአት ልጆችን ሊነካ የሚችለው፣ ልጆችም ልክ እንደ አባቶቻቸው በጣዖት እምልኮ ውስጥ ሲወድቁ ብቻ ነው። ምክንያቱም ቍጥር 16 ሁሉም በራሱ ኃጢአት ተጠያቂ መሆን እንዳለበት እንዲሁም ልጆች በአባቶቻቸው ኃጢአት መወቀስ እንደሌለባቸው ይገልጻል። ከዚህ በተጨማሪ ቍጥር 19፣ 'ለእያንዳንዱም እንደ መንገዱና እንደ ሥራው ትከፍለዋለህ' ማለቱ አባቶችንና ልጆችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ስለሆነ፣ በአባቶች ኃጢአት ልጆች መጠየቅ የለባቸውም"[51]።

የሚገርመው ደግሞ ከዚህ ምንባብ ጋር ተጓዳኝ ሐሳብ ባላቸው የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ላይ ሁሉ ትኵረት የተሰጠው የእግዚአብሔር ቍጣ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ይቅር ባይነት ነው (ዘኍ. 14÷17-20፤ ዘፀ. 34÷6-7 ፤ 20÷5-6፤ ዮና. 4÷1-2፤ ዘዳ. 7÷9-10፤ 5÷9-10፤ 6÷5)። ቍጣው ከሦስት እስከ አራት፣ ምሕረቱ ግን እስከ ሺህ ትውልድ ይዘልቃል።

> "1. ዮናስ ግን ፈጽሞ አልተደሰተም፤ ስለዚህም ተቈጣ። 2. ወደ እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ጸለየ፤ 'እግዚአብሔር ሆይ፤ በአገሬ ሳለሁ የተናገርሁትስ ይህን አልነበረምን? ፈጥኜ ወደ ተርሴስ

51 From— shamash.org/tanach/tanach/commentary/j_seminar/volume4/v4n22 Copyright ©1997 Sephardic Institute.



> ለመኰብለል የተነሣሁትም ለዚሁ ነበር፤ አንተ ቸርና ርኅሩኅ፤ ምሕረትህ የበዛ ከቍጣ የራቅህ አምላክ፣ ጥፋትንም ከማምጣት የምትመለስ እንደሆንህ ዐውቃለሁ" (ዮና 4)።

ምሕረቱ ኪዳኑን መሠረት ያደረገ በመሆኑ፣ ይቅርታ የሚገኘው ወደ ኪዳኑ በመግባት፣ መቅሠፍትም የሚመጣው ከኪዳኑ በመራቅ ነው። ከግብፅ የወጡት አይሁድ፣ በጣዖት አምልኳቸው ምክንያት በምድረ በዳ ሲቀሩ፣ ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው የተስፋውን ምድር የወረሱት በዚህ አግባብ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር በአባቶች ኃጢአት ልጆችን አይቀጣምና። የኃጢአት ክፍያ ኃጢአቱን ካደረጉ አባቶች ኀጢአቱን ወዳላደረጉ ልጆች ይተላለፋል ቢባል እንኳ፣ ይህ እውን የሚሆነው ከኪዳኑ ውጪ ባሉና ኪዳኑን ባፈረሱ እንጂ በኪዳኑ ውስጥ ባሉት ላይ በጭራሽ አይደለም[52]።

## አበው የበሉት ፍሬ የልጆችን ጥርስ አጠረሰ!

> 2. "ስለ እስራኤል ምድር፣ 'አባቶች ጐምዛዛ የወይን ፍሬ በሉ፤ የልጆችንም ጥርስ አጠረሰ' እያላችሁ የምትመስሉት ተምሳሌት ምን ለማለት ነው? 3. 'በሕያውነቴ እምላለሁ ይላል ልዑል እግዚአብሔር፤ ከእንግዲህ ይህን ምሳሌ በእስራኤል ምድር አትመስሉም። 4. እነሆ ነፍስ ሁሉ የእኔ ናት፤ የአባት ነፍስ የእኔ እንደ ሆነች ሁሉ የልጁም ነፍስ የእኔ ናት፤ ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርሷ ትሞታለች" (ሕዝ 18)።

በእስራኤል ታሪክ ውስጥ፣ እግዚአብሔር ፍትሓዊ ባልሆነ መልኩ በአባቶች ኃጢአት ልጆችን ይቀጣል፣ የሚለው አስተሳሰብ በብዙዎች ዘንድ እንደ ነበር እንመለከታለን። በሕዝቅኤል ዘመን የነበሩ ሰዎች ያን ዐይነት አስተያየት እንዲያደርጉባቸው ምክንያት የሆኑ ነገሮች አሉ። ይኸውም ይህ ትውልድ በባቢሎናውያን ምርኮ የተጋዘ ትውልድ ነው። ይህ ግዞት እንደሚሆን በተለያየ ጊዜ

52 ዝኒ ከማሁ።

የተለያዩ ነቢያት ተናግረዋል። ከዚህም የተነሣ ብዙ ትውልድ በጣዖት አምልኮ ውስጥ ኖሯል። "ከዚህም የተነሣ አዲሱ ትውልድ እኛ ይህ ዕጣ ፈንታ የደረሰብን፣ በአባቶቻችን ኀጢአት ነው የሚል አቋም ነበረው"[53]።

> ይህ ግን ስሕተት እንደ ሆነ ሕዝቅኤል በግልጽ ይናገራል:—
> "19. 'እናንተ ግን፣ 'ልጅ ስለ አባቱ ኀጢአት ለምን አይቀጣም?' ትላላችሁ። ልጁ ቀናና ትክክለኛውን ነገር ስላደረገ፣ ሥርዐቴንም ሁሉ በጥንቃቄ ስለ ጠበቀ በሕይወት ይኖራል። 20. መሞት የሚገባት ኀጢአት የሠራችው ነፍስ ናት። ልጅ በአባቱ ኀጢአት አይቀጣም፤ አባትም በልጁ ኀጢአት አይቀጣም። ጻድቁ የጽድቁን ፍሬ ያገኛል፤ ኀጢአተኛውም የኀጢአቱን ዋጋ ይቀበላል። 21. 'ኀጢአተኛ ከሠራው ኀጢአት ሁሉ ተመልሶ ሥርዐቴን ሁሉ ቢጠብቅ፣ ቀናና ትክክለኛውን ነገር ቢያደርግ ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል እንጂ አይሞትም። 22. በደሉ ሁሉ አይታሰብበትም፤ በጽድቅ መንገድ ሄዶአልና በሕይወት ይኖራል። 23. በውኑ ኀጢአተኛ ሲሞት ደስ ይለኛልን? ይላል ጌታ እግዚአብሔር። ይልቁን ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ሲኖር ደስ አይለኝምን?"
>
> *(ሕዝ 18)*።

ይህ የሕዝቅኤል ክፍል፣ ምንም እንኳ በአባቶቻቸው ኀጢአት ምክንያት ወደ ግዞት ቢወርዱም፣ በእውነተኛ ንስሓ የሚመለሱ ሰዎች በግዞት ምድር እንኳ፣ የአምላካቸው ቅሬታዎች/ትሩፋን መሆን እንደሚችሉ ይገልጻል።

በግዞት ምድር ለአምላካቸው ትሩፋን ከሆኑ ጻድቃን መኻል ዳንኤል አንዱ ምሳሌ ነው። ዳንኤል፣ "አባት የበላው ፍሬ የልጅ ጥርስ አጠረሰ" ከሚለው አስተሳሰብ ጋር የሚቃረን ሐሳብ እንደ ነበረው የሚከተሉትን ክፍሎች ይመሰክቷል:—

---

[53] *Ralph Alexander, "Commentary on Ezekiel" in The Expositors Bible Commentary, Vol. 6 (Zondervan: Grand Rapids, MI.: 1986), 823.*



"1. የሜዶናዊው የአርጤክስስ ልጅ ዳርዮስ በባቢሎን በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት፣ 2. በዘመነ መንግሥቱ በመጀመሪያው ዓመት፣ እኔ ዳንኤል ለነቢዩ ለኤርምያስ በተሰጠው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት፣ የኢየሩሳሌም መፈራረስ ሰባ ዓመት እንደሚቈይ ከቅዱሳት መጻሕፍት አስተዋልሁ። 3. በለዚህ ማቅ ለብሼ፣ በራሴም ላይ ዐመድ ነስንሼ፣ በጾምና በጸሎት፣ በምልጃም ፊቴን ወደ ጌታ አምላክ አቀናሁ። 4. ወደ አምላኬ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ብዬ ጸለይሁ፤ ተናዘዝሁም፤ 'ከሚወዱህና ትእዛዝህን ከሚፈጽሙ ሁሉ ጋር የፍቅር ቃል ኪዳንህን የምትጠብቅ፣ ታላቅና የተፈራህ አምላክ፤ ጌታ ሆይ፤ 5. እኛ ኀጢአት ሠርተናል፤ በድለናልም፤ ክፋትን አድርገናል፤ ዐምፀናልም፤ ከትእዛዝህና ከሕግህ ዘወር ብለናል። 6. ለንጉሦቻችን፣ ለልዑሎቻችንና ለአባቶቻችን እንዲሁም ለምድሪቱ ሕዝብ ሁሉ በአንተ ስም የተናገሩትን አገልጋዮችህን ነቢያትን አልሰማንም።

7. 'ጌታ ሆይ፤ አንተ ጻድቅ ነህ፤ ነገር ግን ለአንተ ታማኞች ባለመሆናችን እኛን በበተንህባቸው አገሮች ሁሉ የምንገኝ የይሁዳ ሰዎች፣ የኢየሩሳሌምና የመላው እስራኤል ሕዝብ፣ በሩቅም ሆነ በቅርብ ያለን በዚህ ቀን በኀፍረት ተከናንበናል። 8. እግዚአብሔር ሆይ፤ እኛና ንጉሦቻችን፣ ልዑሎቻችንና አባቶቻችን በአንተ ላይ ኀጢአት ስለ ሠራን በኀፍረት ተከናንበናል። 9. ምንም እንኳ በእርሱ ላይ ያመፅን ብንሆን፣ ጌታ አምላካችን ይቅር ባይና መሓሪ ነው። 10. እግዚአብሔር አምላካችንን አልታዘዝንውም፤ ደግሞም በአገልጋዮቹ በነቢያት በኩል የሰጠንን ሕግ አልጠበቅንም፤ 11. መላው እስራኤል አንተን ባለመታዘዝ ሕግህን ተላልፎአል፤ ዘወርም ብሎአል። 'በአንተ ላይ ኀጢአትን ስለ ሠራን፣ በእግዚአብሔር አገልጋይ በሙሴ ሕግ የተጻፈው መሐላና ርግማን ፈስሶብን። 12. ታላቅ ጥፋት በእኛ ላይ በማምጣት፣ በእኛና በገዦቻችን ላይ የተነገረውን ቃል ፈጸምህብን፤ በኢየሩሳሌም ላይ የተደረገውን የሚያህል ከሰማይ በታች ከቶ የለም።

> 13. በሙሴም ሕግ እንደ ተጻፈው፣ ይህ ሁሉ ጥፋት በእኛ ላይ ደረሰ፤ ሆኖም ከኀጢአታችን በመመለስና እውነትህን በመከተል ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ምሕረትን አልፈለግንም 14. አምላካችን እግዚአብሔር በሚያደርገው ሁሉ ጻድቅ ነውና፣ በእኛ ላይ እግዚአብሔር ጥፋት ከማምጣት አልተመለሰም፤ እኛም አልታዘዝነውም።
> 15. 'አሁንም ሕዝብህን ከግብፅ ምድር በብርቱ እጅ ያወጣህ፣ እስከዚህም ቀን ድረስ ስምህ እንዲታወቅ ያደረግህ፣ ጌታ አምላካችን ሆይ፤ እኛ ኀጢአትን ሠርተናል፤ እንተንም በድለናል። 16. ጌታ ሆይ፤ ቀድሞ እንዳደረግኸው የጽድቅ ሥራህ ሁሉ፣ ከከተማህ ከኢየሩሳሌም፣ ከቅዱስም ተራራህ ቍጣህን መልስ፤ በእኛ ኀጢአትና በአባቶቻችን በደል ምክንያት ኢየሩሳሌምና ሕዝብህ በዙሪያችን ባሉት ዘንድ መሣለቂያ ሆነዋል።
> 17. 'እሁንም አምላካችን ሆይ፤ የአገልጋይህን ጸሎትና ልመና ስማ። ጌታ ሆይ፤ ስለ ስምህ ስትል ፊትህን ወደ ፈረሰው መቅደስ መልስ። 18. አምላክ ሆይ፤ ጆሮህን አዘንብለህ ስማ፤ ዐይንህን ገልጠህ መጥፋታችንንና ስምህ የተጠራበትን ከተማ ተመልከት። ልመናችንን የምናቀርበው ስለ ጽድቃችን ሳይሆን፣ ስለ ታላቅ ምሕረትህ ነው። 19. ጌታ ሆይ፤ አድምጥ! ጌታ ሆይ፤ ይቅር በል! ጌታ ሆይ፤ ስማ! አድርግም፤ ስምህ በከተማህና በሕዝብህ ላይ ተጠርቶአልና አምላኬ ሆይ፤ ስለ ስምህ ስትል አትዘግይ"
>
> (ዳን. 9)።

ትንቢተ ዳንኤል ከአምላክ ጋር ሊኖረን ስለሚገባው ኪዳናዊ ግንኙነት፣ ትልልቅ ቍም ነገሮችን ይናገራል። እስራኤል ወደ ባቢሎን የመጋዟ ምስጢር፣ ለረጅም ዓመታት በጣዖት አምልኮና በዐመፅ ውስጥ የመኖሯ ውጤት ነው። ምንም እንኳ በአባቶቻቸው ኀጢአት በግዞት ቢወድቁም በግዞት በተወለዱበት ምድር እንኳ፣ ኪዳናቸውን ለሚጠብቁ ቅሬታዎች/ትሩፋኖች፣ እግዚአብሔር ቸር እንደ ነበር፣ ከነዳንኤል ሕይወት ማየት እንችላለን።



> "30. 'ልጆቹ ሕጌን ቢተዉ፣ ደንቤን ባይጠብቁ፣ 31. ሥርዐቴን ቢጥሱ፣ ትእዛዜንም ባያከብሩ፣ 32. ኀጢአታቸውን በበትር፣ በደላቸውን በጅራፍ እቀጣለሁ። 33. ምሕረቴን ግን ከእርሱ አላርቅም፤ ታማኝነቴንም አላጓድልበትም። 34. ኪዳኔን አላፈርስም፤ ከአፌ የወጣውንም አላጥፍም። 35. አንድ ጊዜ በቅድስናዬ ምያለሁና፣ ዳዊትን አልዋሽውም" (መዝ. 89)።

እግዚአብሔር ለዳዊት፣ አንዳች ቅድመ ሁኔታ የሌለባትን ኪዳን አቍሞአል። ይኸውም ከእርሱ ዘር ዘላለማዊ የሆነ ንግሥና እንደሚያቆም—ንጉሥ ከዘሩ እንደማይጠፋ (ለምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል— 2ሳሙ 7÷13-14፤ ኢሳ. 9÷7፤ ኤር. 33÷15-21)።

## ሐዲስ ኪዳን

የአባቶች ኀጢአት፣ "ሦስትና አራት ትውልድ" ይተላለፋል የሚለው ብሉይ ኪዳን ትምህርት የተነገረው፣ የእግዚአብሔር ምሕረት "ለአንድ ሺህ ትውልድ" ይዘልቃል በሚለው ዐውድ ውስጥ ነው። ይኸውም የአግዚአብሔር "አንድ ሺህ ትውልድ" ምሕረት፣ በኪዳኑ ውስጥ ታማኝ ሆኖ መኖርን እንዲሁም ኀጢአት አሉታዊ ውጤት እንደሚያስከትል፣ ቅድመ ሁኔታ ሆኖ በቀረበበት ዐውደ ምንባብ ውስጥ ነው። የአውነተኛ በረከት መሠረቱ፣ ከእግዚአብሔር ጋር በኪዳን መጋመድ/መጣመር ነው። እንደ ሐዲስ ኪዳን ትምህርት፣ ይህ እውን መሆን የሚችለው ደግሞ፣ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝ አድርጎ በመቀበል፣ በእርሱ ቤዛዊ/ወጂዊ ሥራ በፍጹም ልብ በማመን ነው።

ክርስቶስ ኢየሉስን እንደ ግል አዳኙ የተቀበለ ሰው፣ በምንም ዐይነት መልኩ፣ በወላጆቹ መርገም ሥር ሊወድቅ አይችልም።

> "6. እስቲ አብርሃምን አስቡ፤ 'እርሱ እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።' 7. እንግዲህ እነዚያ የሚያምኑት የአብርሃም ልጆች እንደሆኑ እስተውሉ። 8. መጽሐፍ፣ እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንደሚያጸድቅ አስቀድሞ በማየት፣ 'አሕዛብ ሁሉ በአንተ ይባረካሉ' በማለት ወንጌልን

ለአብርሃም አስቀድሞ አስታወቀው። 9. ስለዚህ በእምነት የሆኑት፣ የእምነት ሰው ከሆነው ከአብርሃም ጋር ቡሩካን ናቸው" (ገላ. 3)።

እሕዛብ፣ በአብርሃም ዘላለማዊ ኪዳኑ ውስጥ መግባት የቻሉት በክርስቶስ ቤዛዊ ሥራ በማመናቸው እንደ ሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ብሉያትን ጠቅሶ ይሞግታል:—

"13. 'በዕንጨት ላይ የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው' ተብሎ ስለ ተጻፈ፣ ክርስቶስ ስለ እኛ ርግማን ሆኖ ከሕግ ርግማን ዋጅቶናል፤ 14. ለአብርሃም የተሰጠው በረከት፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ለአሕዛብ እንዲደርስ ዋጅቶናል፤ ይኸውም በእምነት የመንፈስን ተስፋ እንድንቀበል ነው" (ገላ. 3)።

"3. የሚባርኩህን እባርካለሁ፤ የሚረግሙህን እረግማለሁ፤ በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች፣ በአንተ አማካይነት ይባረካሉ'" (ዘፍ. 12)።

እንዲያውም ሐዲስ ኪዳን በረከት፣ በዘር ሳይሆን በእምነት በማቆም ኪዳን እንደሚገኝ በግልጽ ያስረዳል:—

"9. 'አብርሃም አባት አለን' በማለት ራሳችሁን አታታሉ፤ እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣ ይችላል እላችኋለሁና" (ማቴ. 3 እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል— ገላ. 3÷22፤ 4÷20÷ ዘፍ. 18÷18፤ 22÷18፤ 26÷4፤ ኤር. 4÷2፤ ሮሜ 3÷28-30፤ 9÷17፤ የሐ. 7÷38-42፤ 19÷37)።

የትውልዳችሁ መርገም በክርስቲያኖች ላይ እውን መሆን ይችላል የሚሉ ሰዎች፣ መርገምን ለመስበር በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ማመን ብቻ በቂ አይደለም ማለታቸው እንደ ሆነ ልብ ልናደርገው ይገባል። በገላትያና በቈላስይስ አብያተ ክርስቲያናት ታይቶ የነበረው ኑፋቄ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ማመን በጣም ጥሩ ነገር ነው፤ ነገር ግን ብቻውን በቂ አይደለም የሚል ነበር። ልዩ የሆነ ዕውቀት ወይም ደግሞ ሃይማኖታዊ ልምምድ ካልታከለበት (ካልተጨመረበት) በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ማመን ብቻ ፋይዳ የለውም ወይም ሙሉውን የድነት በረከት አያስገኝም ባዮች ነበሩ።

ዘፀአት 20÷4-5 በመጥቀስ፣ "ከትውልዳችሁ መርገም ሥር ናችሁ" የሚሉን ሰዎች በሌላ መንገድ በክርስቶስ ቤዛዊ/ወጇዊ ሥራ



ማመናችሁ ብቻ በቂ እይደለም እያሉን ነው[54]። እንዲያው ጌታ ያልሰበረውን መርገም የትኛው የሰብእውያን ቀመር ወይም የትኛው ጀግና ሊሰብረው ይችላል? እንሰበርላችሁ የሚሉስ ሰዎች፣ የእኛን እነርሱ ይሰብሩልናል ግን የእነርሱን መርገም የሰበረላቸው ማን ይሆን?

የዚህ ትምህርት አስተማሪዎች መርገምን የሚያመጣው ሰይጣን ነው ባዮች ናቸው[55]። ነገር ግን ዘፀአት 20÷4-5 ላይ ያለው እንዲሁም ተዛማጅ ምንባባት መርገም የሚያመጣው ከሰይጣን ነው አይሉም። በምንባባቱም ዐውድ ውስጥ፣ ሰይጣንም ሆነ አጋንንት በስም አልተጠቀሱም። ኪዳናቸውን የሚያፈርሱትን ሰዎች የሚቀጣው ራሱ እግዚአብሔር ነው። ምክንያቱም የሕጉ እጋጊም (ደንጋጊም) ሆነ የሕጉ አስጠባቂ ራሱ እግዚአብሔር ነውና (ሕጉን የሚያስከብር የሕጉ ባለቤት ነው)።

በተጨማሪም ክርስቶስን በማመናችን ከሥልጣናት፣ ከኀይላት፣ ከገዢዎች ወዘተ ቍጥጥር ውጪ እንደሆንን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል።

"10. እናንተም የገዥነትና የሥልጣን ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ሙሉ ሆናችኋል" (ቈላ. 2)።

እንደ ማርሊን ሄኪ ያሉ የእንቅስቃሴው መምህራን፣ ዐሥራት ያለመስጠት ራሱ መርገም እንደሚያመጣ ይገልጻሉ፤ ለዚህ አሳብ ማስደገፊያ አድርገው የሚጠቅሱት ሚልክያስ 3÷9 ነው። በአሮጌው ኪዳን፣ የአምልኮ ሕግ ብመባል የሚታወቁትን እነዚህን ትእዛዛት መተላለፍ መርገም የሚያስከትል ከሆነ፣ በአምልኮ ሥርዐተ

---

[54] ዴሬክ ፕሪንስ፤ *በረከት ወይስ መርገም አንዱን ምረጥ—የጭንቀት ሕይወት ከመመራት የመገላገያው ዘዴ*፤ (የማነብርሃን እንዳለ፤ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፤ 1989 ዓ.ም)። *Neil T. Anderson, The Bondage Breaker, (Harvest House: Eugene, Or.: 1990).*
[55] ዴሬክ ፕሪንስ፤ *በረከት ወይስ መርገም አንዱን ምረጥ—የጭንቀት ሕይወት ከመመራት የመገላገያው ዘዴ*፤ (የማነብርሃን እንዳለ፤ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፤ 1989 ዓ.ም)፣ ገጽ 61-63።. *Marilyn Hickey, Break the Generation Curse, (Denver: Marilyn Hickey Ministries, 1988).*

ሕግ የተዘረዘሩትን 613 ሕጎች ያስማክበራችንም በመርገም ውስጥ ይከተናል ማለት ነው፤ ምክንያቱም ዐሥራት ከእነዚህ 613 ሕግጋት አንዱ ሕግ ነውና[56]።

ልጆች የወላጆቻቸውን መጥፎ ጠባይ ሊወርሱ እንደሚችሉ ይታወቃል። በአንጻሩ ልጆች ከወላጆቻቸው የተለያዩ ዐይነት በሽታዎች ሊተላለፉባቸው እንደሚችሉ ግልጽ ነው (ለምሳሌ:— የስኳር በሽታ፣ ኤች.አይ.ቪ.)። በአንጻሩ ደግሞ ወላጆች ልጆች ከወላጆቻቸው ጥሩ ጠባይም ሆነ ውብ ተክለ ሰውነት ይወርሳሉ። ይህን ጉዳይ መርገም ይተላለፋል ከሚለው ጋር ስማመሳሰል ምንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ አናገኝም[57]።

## ማጠቃለያ

ማጅራት መቺዎችና ኪስ አውላቂዎች፣ ዐላማቸውን ከዳር ስማድረስ ተገን የሚያደርጉት አሳቻ ቦታዎችን፣ ግራ አጋቢ ሁኔታዎችንና ሰዎች በቀላሉ የሚዘናጉባቸውን ወቅቶች ነው። የአባይ ነባዮችም ሆነ የመናፍቃን አካሄድ የዚህ ግጣም ነው—አንዳችም ልዩነት የለውም።

ሕዝበ ክርስቲያኑ ቅዱሳት መጻሕፍት የአምላክ አፊምተ ቃል ናቸው፤ የአስተምህሮአችንም ሆነ የሥነ ምግባራችን መለኪያ ናቸው የሚል እምነት አለው—በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ያለው አቋም በደምሳሳው የሚታይ ቢሆንም። ከዚህም የተነሣ ትምህርቶችንም ሆነ አካሄዶችን፣ በቅዱስ ቃሉ መመዘን አማራጭ የሌለው አካሄድ ነው የሚል መግባባት፣ በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ዘንድ አለ። ይህ ቋሚና ነባር አካሄድ፣ ለመናፍቃኑም ሆነ ለአባይ ነባዮቹ እንብዛም አክል አይፈጥርባቸውም። ለዚህ ማነቄ ሁነኛ የመሿለኪያ ብልኀት

56 የተለያዩ ድረ ገጾች የእነዚህን 613 ሕጎች ዝርዝር ይገልጻሉ፤ ይመለከቷቸው።

57 ከላይ፣ መርገምና ከወላጅ የሚተላለፉ በሽታዎች በሚል ርእስ ያነሣናቸውን ነጥቦች ይመለከቷል።



አበጅተውለታልና፤ በዚህም ጥበባቸው ብዙ ባይተዋር ትምህርቶችን አስርገው ማስገባት ችለዋልና። እነዚህ የማሿለኪያ አካሄዶች የሚከተሉት ናቸው:—

- ቅዱሳት መጻሕፍት ከእኛ ትምህርት አንጻር እየተገናዘቡ ይተርጐሙ፣
- ቅዱሳት መጻሕፍት በእኛ የሥነ ትርጓሜ መርሖ አንጻር ይተንተኑ፣
- እጅግ ስውርና ለመተርጐም አስቸጋሪ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትን የአስተምህሮአችን መሠረት አድርገን እንገስገልባቸዋለን።

አባይ ነባዮችም ሆኑ መናፍቃን፣ እነዚህን ሦስት አካሄዶች እንደ አስፈላጊነቱና እንደ አዋጭነቱ እቀላቅለው ይጠቀሙባቸዋል። ቅዱሳት መጻሕፍትን ከእናት ቋንቋቸው ማለትም ከበኩረ ጽሑፉ በቀጥታ ተርጕመን ነገር ግን ከእኛ አስተምህሮ ጋር አስማምተን/አዋድደን እናቀርብላችሁ የሚለው አካሄድ ጠንካራ የገንዘብ ዐቅም ይፈልጋል። ገንዘብ ያስፈለገው፣ የትርጕሙን ሥራ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለመከወን ሳይሆን፣ መጽሐፍ ቅዱስን ከራሳቸው አስተምህሮ አንጻር እያደላደሉ ስመተርጐም እንዲሁም ትርጕማቸው በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ማስቻል ብዙ ድካም የሚፈልግ ነው። ዐቅማቸው የፈቀደላቸው ግን ይህን ማድረግ ችለዋል። ለምሳሌ፣ "የይሖዋ ምስክሮች" መጽሐፍ ቅዱስን ከራሳቸው አስተምህሮ ጋር እንዲታረቅ አድርገው ተርጕመውታል[58]—በአማርኛ ቋንቋ ያዘጋጁት መጽሐፍ፣ "የአዲስ

58 እንዲያውም አሁን እንደ *NIV* ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጕሞች "ለይጣናዊ ናቸው"፣ "ግብረ ሰዶማውያን የዘጋጁቸው ናቸው"፣ "የነ.ው ኤጅ ተከታዮች የተሳተፉባቸው ናቸው" ወዘተ የሚል አሉባልታ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ተከታዮች መኻል እየናፈሱ ነው። ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ግን ይህን በውል ሳይረዳ፣ አሉባልታውን በማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን ላይ እየነዛው ይገኛል። የሚገርመው ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የትርጕም ዝግጅት ታሪክ፣ እንደ *NIV* ከመቶ ያላነሱ ሊቃውንት የተካፈሉበት እንዲሁም እጅግ ስመ ጥር ምሁራን የተካተቱበት የትርጕም መጽሐፍ

ዓለም ትርጉም" በመባል ይታወቃል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት እየተሠራጨ ይገኛል፡፡ ሁለተኛውና ሦስተኛው አካሄድ ግን፣ ብልጣብልጥነትን እንጂ፣ የገንዘብ ዐቅም አይፈልግም፡፡

የተሳሳተ የሥነ ትርጓሜ አካሄድ መከተል፣ በሁሉም አባይ ነባዮችና መናፍቃን ላይ የሚታይ ቋሚ ችግር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ አስተምህሮአቸውን ግልጽ ባልሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ላይ ማስደገፍ ተመራጭ አቀራረባቸው ነው፡፡ ይህ ምዕራፍ ትኩረት ያደረገበት ርእስ፣ ለመረዳት አዳጋች የሆኑና በርካታ የትርጓሜ አማራጭ ያላቸውን ክፍሎች በመጠቀም፣ ሰዎች ባይተዋር ትምህርታቸውን እንዴት አድርገው በሕዝቡ ልብ እንደሚያሠርጹ የሚያሳይ ነው፡፡

የእምነት እንቅስቃሴንና አንዳንድ "የዐርነት" አገልግሎት እናገለግላለን የሚሉ ሰዎች፣ ስውር ምንባባትን አብዝቶ የመጠቀም ልማድ አላቸው፡፡ በተለይ አሻሚ ከመሆናቸው የተነሣ በርካታ የትርጓሜ አማራጭ የሚቀርብላቸው ክፍሎች፣ በዚህ ረገድ አጅግ ተወዳጅ ሆነውላቸዋል[59]፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ምንባባት፣ አስተምህሮአቸው እርቃኑ እንዳይታይ፣ ኀፍረት መሸፈኛ ሆነውላቸዋልና፣ ሥነ ምግባራቸው እንዳይጋለጥ ይጋርዱላቸዋልና፡፡ ማንም ተነሥቶ፣ "ትምህርታችሁም ሆነ አኗኗራችሁ እንደ ቃሉ አይደለም" የሚለውን ክስ ቢያቀርብ፣ "ካቃሉ አልራቅንም እንዲያውም ቃሉን በጥልቀት ያመሳከረ ሕይወት አለን" የሚሉት፣

---

እንደ ሌሎ በአካዳሚ ጆርናሎች ላይ እየተነገረ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ የአንዳንድ አስባልታዎችን ምንጭ ምን እንደ ሆነ መመርመር፣ የቤተ ክርስቲያን አስተማሪዎችን መጠየቅ፣ እንዲሁም የሚባለው አስባልታ ምን ያህል እውነት ነው የሚለውን ጉዳይ በቅርበት መመርመርን ወይም ማስመርመርን መልመድ እንዳለበት መግለጽ እወዳለሁ፡፡

[59] ይህን ስል ግን አንዳንድ ሰዎች በዚህ ዐይነቱ ትምህርት ውስጥ የገቡት ሆን ብለው ሳይሆን፣ እነርሱ ራሳቸው ተሳስተው እንደ ሆነ መግለጽ እፈልጋለሁ—በዚህ ረገድ እኔ ራሴ የማውቃቸው በርካታ ገጠመኞች አሉኝና፡፡



እነዚህን ስውር ምንባባት፣ ከወዲህ ከወዲያ እያጠናበሩ በመጥቀስ ነው፡፡

በርካታ ሰዎች እነዚህን የጉፋቂ ማራገፊያ ክፍሎች በጥልቀት ስለማይመረምሩ፣ ስሕተቱን ፊት ለፊት የመቃወም ኀይል አይኖራቸውም፡፡ ከበረታም እነርሱ ራሳቸው ጉፋቂውን ታቅፈው ይኖራሉ፡፡

እባክዎን የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት በጥሙና ያንብቧቸው:—

> "16. ስለዚህ ከአሁን ጀምሮ ማንንም በውጫዊ ነገር አንመዝንም፤ ከዚህ ቀደም ክርስቶስን በዚህ መልክ መዝነነው ነበር፤ ከእንግዲህ ግን እንደዚህ አናደርግም። 17. ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፣ አዲስ ሆኖአል። 18. ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ እርሱ በክርስቶስ አማካይነት ከራሱ ጋር አስታረቀን፤ የማስታረቅንም አገልግሎት ሰጠን፤ 19. እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር ሲያስታርቅ የሰዎችን በደል አይቈጥርባቸውም ነበር፤ ለእኛም ደግሞ የማስታረቅ ቃል ሰጠን" (2ቆሮ 5)።
>
> "1. ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም፤ 2. ምክንያቱም የሕይወት መንፈስ ሕግ በክርስቶስ ኢየሱስ ከኀጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ አውጥቶአችኋል" (ሮሜ 8)።
>
> "13. ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን"
>
> (ገላ. 2)
>
> "15. ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን አይደለም፤ በአንድ ሰው መተላለፍ ብዙዎቹ ከሞቱ፣ የእግዚአብሔር ጸጋና በአንዱ ሰው፣ ይኸውም በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የመጣው ስጦታ ለብዙዎች እንዴት አብልጦ ይትረፈረፍ! 16. ደግሞም የእግዚአብሔር ስጦታ እንደ አንዱ ሰው የኀጢአት ውጤት አይደለም፤ ምክንያቱም ፍርዱ የአንድን ሰው ኀጢአት ተከትሎ ኵነኔን አመጣ፤ ስጦታው ግን አያሌ መተላለፍን ተከትሎ ጽድቅን አመጣ (ሮሜ 5)።

9. እናንተ ግን፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ የሚኖር ከሆነ፣ በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ናችሁ። ማንም የክርስቶስ መንፈስ ከሌለው፣ እርሱ የክርስቶስ አይደለም። 10. ነገር ግን ክርስቶስ በውስጣችሁ ካለ፣ ሰውነታችሁ ከኀጢአት የተነሣ የሞተ ቢሆንም፣ መንፈሳችሁ ከጽድቅ የተነሣ ሕያው ነው። 11. ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ የሚኖር ከሆነ፣ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣው፣ በውስጣችሁ በሚኖረው በመንፈሱ ሟች ስሆነው ሰውነታችሁ ሕይወትን ይሰጣል" (ሮሜ 8)።

"31. ታዲያ ለዚህ ምን እንመልሳለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ማን ሊቃወመን ይችላል? 32. ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት፣ ነገር ግን ለሁላችንም አሳልፎ የሰጠው እርሱ፣ ሁሉንስ ነገር ከእርሱ ጋር እንደ ምን በልግስና አይሰጠን? 33. እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚከስ ማን ነው? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤ 34. ታዲያ የሚኰንን ማን ነው? የሞተው፣ እንዲሁም ከሞት የተነሣው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ ኢየሱስ፣ ስለ እኛ ይማልዳል። 35. ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማን ነው? ችግር ነው ወይስ ሥቃይ፣ ወይስ ስደት፣ ወይስ ረሀብ፣ ወይስ ዕራቍትነት፣ ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ?" (ሮሜ 8)።

"30. በክርስቶስ ኢየሱስ ለመሆን የበቃችሁት ከእርሱ የተነሣ ነው፤ እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበባችን፣ ጽድቃችንና ቅድስናችን፣ ቤዛችንም ሆኖአል። 31. እንግዲህ፣ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው፤ "የሚመካ በጌታ ይመካ"" (1ቆሮ 1)።



# አባሪ

## ክርስትና ለጤንነትና ለሀብት ዋስትና አልሰጠም!

ከጌታ ጋር ለረጅም ዓመት የኖረች እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በትጋት አምላኳን የምታገለግል ክርስቲያን እኅት፣ "ክርስቲያን ቱጃር መሆን አለበት" የሚለውን ስብከት ከመጥገቧ የተነሣ፣ "የሚሸተን ዶሮ ወጥ ነው፤ ሽሮ እንኳ በወጉ እያገኘን ግን አይደለም" የሚለው ንግግሯ ትዝ ይለኛል።

ዶሮ ወጥ ያሸተቱን የዘመኑ የዶሮ ወጥ ሰባኪዎች እንጂ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት አይደሉም። መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ምድር ዐልጋ በዐልጋ የሆነ ሕይወት ይገጥማችኋል የሚል ዋስትና አልሰጠንም። ባይሆን አምላካችን እግዚአብሔር፣ "ለሽሮ" በማይመጥን ሕይወት ውስጥ፣ "ዶሮ ወጥ" ከሚሰጠን ደስታና ፍሥሓ የተሻለ ሐሴት በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጐናጽፈን፣ ለሳማችን የተትረፈረፈ እንደሚሆን ቃል ኪዳን ሰጥቶናል።

በተመሳሳይ መንገድ፣ አንድ ወዳጄ ማቴዎስ 4÷23፤ 9÷35 ጠቅሶ ሁሉም "ይፈወሱ ነበር"፣ "ክርስትና በሽታ ሁሉ እንደሚፈወስ ዋስትና ሰጥቷል" የሚል ሙግት በፌስቡክ ሊገጥመኝ ሞከረ። እባክህ ተው መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ዐይነቱን ዋስትና አልሰጠም ብለው ሊሰማኝ በፍጹም አልቻለም።

ይህ አስተሳሰብ ወደ ኢትዮጵያ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የገባው፣ "በእምነት እንቅስቃሴ" መምህራን አማካይነት ነው። ግለሰቡ የዚህ ትምህርት ሰለባ መሆኑን በትክክል የሚያውቀው አይመስለኝም (ማለቱን እንጂ የሚለው ነገር ከየት እንደ መጣ በትክክል አልተረዳውም)።

"የታመመ ሁሉ መፈወስ አለበት" የሚለው የእንቅስቃሴው ትምህርት አስተምህሮውን የሚያጸናበት ሁለት የአካሄድ አቅጣጫዎች አሉት። "በክርስቶስ ወጂዊ ሥራ ውስጥ አካላዊ ፈውስ ምላሽ ስላገኘ፣ ሰዎች ሁሉ መፈወስ አለባቸው" የሚለው አንደኛው አካሄድ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ "በወንጌላውያኑ ትረካ ውስጥ የታመሙ ሁሉ ተፈውሰዋል" የሚለው ነው።

የሁለተኛው አካሄድ የመረጃ ማሳከር ብቻ ሳይሆን፣ ትልቅ የሆነ የሥነ ትርጓሜ ችግር አለበት። ይኸውም በአንድ ታሪካዊ አጋጣሚ አንድ

ነገር እውነ ሆነ ማለት፣ ሁል ጊዜ ነገሩ እውን ይሆናል ማለት አይደለም። ከትምህርታዊ ምንባባት ተነሥተን ታሪክን አጣቅሰን አስተምህሮ እንመሠርታለን እንጂ፣ በተገላቢጦሹ ምንጨታዊ ምንባባት አንዳችም አስተያየት ባልሰጡበት ጉዳይ፣ ከትረካዎች ተነሥተን አስተምህሮ አናዋቅርም። ለምሳሌ ጌታ ተራራ ላይ ወይም በታንኳ ላይ ተቀምጦ በየብስ ላሉ ሰዎች ትምህርት ሰጥቶአል ማለት፣ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በሚያስተምሩበት ጊዜ ተራራ ላይ ይውጡ ወይም ታንኳ ላይ ይቀመጡ ማለት አይደለም። ዘማሪው፣ "ጻድቅ ሲራብ ዘሩም አህል ሲለምን አላየሁም" (መዝ. 37÷25) ብሏልና እኛም አናይም ማለት ትክክል አይደለም፤ ቢያንስ ይህ አስተምህሮ በሐዲስ ኪዳን ነገረ መለኮት ውስጥ ትክክል አይደለም።

የሚገርመው ግን በወንጌላት የፈውስ ትረካ ውስጥ ወደ ጌታ የመጡ ሰዎች ሁሉ ሲፈወሱ ወይም ስፈውሳቸው እምነት ወይም ሌላ ጉዳይ በቅድመ ሁኔታ ሲጠየቅ አንመለከትም። ከስዚህ አንድ ክፍል ጠቅሶ መሳው የሐዲስ ኪዳን አስተምህሮ በዚህ መልክ ይሰፈርልኝ ማለት ትክክል አይደለም።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ፣ "የእምነት ወይስ የክህደት እንቅስቃሴ" በሚለው የእኔና የወንድም ምኒልክ አስፋው መጽሐፍ (ገጽ 57-70) ሰፊ ማብራሪያ የቀረበበት ቢሆንም፣ የምዕራፉን እጥርጥር እንዲሁም ከመጽሐፉ አጠቃላይ ሙግት አንጻር የሚከተለውን ወደዚህ አምጥቻለሁ።

## ሀ. ክርስትና ስጤንነት ዋስትና አልሰጠም!

1. በአራቱ ወንጌላት ውስጥ 48 የፈውስ ታሪኮች ተዘግበው እናገኛለን። ነገር ግን የተጓዳኝ ምንባባቱን ድግግሞሽ ስናቀናንስ፣ በወንጌላት ውስጥ 26 የፈውስ ታሪኮችን እናገኛለን።
2. ኢየሱስ ወደዚህች ምድር የመጣው የሰው ልጆችን ሁለንተና ማለትም ነፍሳቸውን ሥጋቸውን ስመፈወስ ነው። ጌታ ይህን ማድረጉ ሁለት ዐቢይ ምክንያትን አለው፤ አንደኛው እርሱ እንደ አባቱ ሁሉን የማድረግ ችሎታና ሥልጣን እንዳለው ለማሳየት/ለማሳወቅ (ዮሐ. 5÷17-22)። ሁለተኛ፣ በክርስቶስ እውን የሚሆነው መንግሥት ምን ዐይነት መገለጫ እንዳለው ለማሳሰብ/ለማስገንዘብ ነው (ማቴ. 4÷23-25)። ይህ መንግሥት የጽድቅ፣ የሰላም፣ የዕረፍት፣ በጥቅሉ የበረከት ዘመን መንግሥት ነው።
3. በክርስቶስ ኢየሱስ የፈውስ አገልግሎት ውስጥ፣ ተፈዋሹ ስው እምነት ያለው መሆኑ በቅድመ ሁኔታ ውስጥ ገብቶ እንምለከትም። ከ26ቱ የፈውስ ታሪኮች ውስጥ፣ 4ቱ ብቻ የፈውሱ ምክንያት ምን እንደ ሆነ አልተገለጸልንም። በተቀሩት በ22ቱ የፈውስ ታሪኮች ውስጥ ግን የፈውሱን ጥያቄ ያቀረበው ወይም ፈውሱ እውን ይሆናል ብሎ እምነት የነበረው ማን እንደ ነበር ተገልጾአል። ከዚህ መረጃ የምናየው በሕመምተኞቹ ጠያቂነት ያውም ጥያቄውን ያቀረቡት እምነት ኖሯቸው ነው ብንል እንኳ ከ22 ውስጥ እምነት የተጠየቀው በ12ቱ ብቻ ነው። ይኸውም:—

| ወንጌላት | በኢየሱስ ጠያቂነት | በደቀ መዛሙርቱ ጠያቂነት | በሕመምተኞቹ ጠያቂነት | በዘመዶቹ ጠያቂነት | በሕመምተኞቹ ወዳጆች ጠያቂነት | በኢየሱስ ተቃዋሚዎች ጠያቂነት | ባልታወቁ ሰዎች ጠያቂነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ማቴዎስ | — | — | 1 | — | 1 | — | 2 |
| ማርቆስ | — | 1 | 4 | 3 | 1 | — | 2 |
| ሉቃስ | 3 | — | 2 | — | — | 2 | — |
| ዮሐንስ | 1 | 1 | — | 2 | — | — | — |

4. ጌታ ኢየሱስ ሁሉን ማድረግ ቢችልም፣ የታመሙትን ሁሉ ግን ያልፈወስም (ዮሐ. 5÷3-5)፤ የተጠየቀውን ሁሉ ያላደረገበት ትእይንቶች ነበሩ፣ ለምሳሌ ምልክት እንዲያሳያቸው ስለመኑት ሁሉ ምልክት አላደረገም (ማቴ. 12÷38-40)። ስዚህ ደግሞ ምክንያቱ ኢየሱስ ሰዎችን የሚፈውሰው (ምልክት፣ ድንቅንና

ተአምራትን የሚያደርገው) ስማያዊ ዐላማውን በሰዎች ልብ ለማድረስ ብቻ እንደ ነበር የሚያስገነዝበን ነው። እርግጥ ነው ሰዎች ከሥጋዊ እስራታቸው ሲፈቱ ደስ ይሰዋል። ይህ ግን ወሳኝ ጉዳይ ሆኖ አልቀረበም። ወሳኙ ጉዳይ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ መሆኑን አምነው፤ አርሱን አንደ ግል አዳኛቸው መቀበላቸው ነው። ስለዚህ ጌታ ሁሉን ማደረግ መቻሉ እሙን ቢሆንም ሁሉን ሲያደርግ ግን አንመለከትም። ስለዚህ ችሎታውን ከሉዓላዊ ፍላጎቱ/ዕቅዱ ጋር መቀየጥ የለብንም።

5. ኢየሱስ ዘንድ የመጡ ሰዎች የተፈወሱት፤ ኢየሱስ አርሱ ሁሉን ቻይ፤ ለሰዎች ግድ የሚለው…አምላክ መሆኑን ለማሳየት ነው። በዚህም መንፈስ የተራቡ ሰዎችን መግቧል (ማቴ 15÷32፤ ማር. 8÷2)፤ መሪ ያላላቸውን (ማቴ. 9÷36፤ ማር. 6÷34)፤ ተጨንቀው የነበሩትን (ሉቃ. 7÷13)፤ በደዌ የተመቱትን (ማር. 9÷22) ሰዎች አይቶ አዝኗል። የግለሰቦቹ እምነት ሳይሆን፤ የእርሱ ርኅራኄ ለፈውሱ ምክንያት ሆኖ የቀረበባቸው አራት የፈውስ ታሪኮች አሉ (የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ማቴዎስ 20÷34፤ 14÷14፤ ማርቆስ 1÷41፤ ሉቃስ 7÷13)።

6. "የዳዊት ልጅ ሆይ ማረን" በማለት ለዕርዳታ የጮኹትን ሰዎች ፈውሷል (ማቴዎስ 9÷27፤ 15÷22፤ 17÷15፤ 20÷30፤ ሉቃስ 17÷13)። እንዲሁም እምነታቸውን አይቶ የፈወሳቸው አሉ (ማቴ. 8÷10፤ 9÷28-29፤ 15÷28፤ ማር. 2÷5፤ 5÷34፤ 9÷24፤ ሉቃ. 17÷19፤ 18÷42)። ቅዱሳት መጻሕፍት እምነት በኀጢአት የወደቀው የሰው ልጅ ከልቡ የሚያመነጨው ጉዳይ ሳይሆን፤ የአምላክ ነጻ ስጦታ እንደ ሆነ ይናገራሉ (ለምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ኤፌ. 2÷8፤ ዮሐ. 6÷28-29፡44-45፤ ሮሜ 12÷3፤ ሐሥ. 12÷3፤ 3÷16፤ ፊልጵ. 1÷29፤ 2ጴጥ. 1÷1)። ስለዚህ እምነት የፈውስ ወይም የድነት ቅድመ ሁኔታ ነው ማለት አስቸጋሪ ነው።



7. ኢየሱስ ሰዎችን ይፈውስ የነበረው ክብሩን ለመግለጥ ነው (ዮሐ. 1÷14፤ 2÷11÷4፤ 17÷5፡22፡24)። የእርሱን ማንነት አስመልክቶ ውዝግብ ሲነሣ ምግባሩን አይተው ማንነቱን እንዲለዩ ጥሪ ያቀርብላቸው ነበር (ዮሐ. 5÷36፤ 10÷25፤ 14÷11፤ 15÷24)። እርሱ የመጣው ሰዎችን ለማስገረምና ለማስደነቅ አይደለም (ዮሐ. 4÷48)፤ ነገር ግን በሚያደርጋቸው ምልክቶች (ግሪክ ሴሚያ) ሰዎች የእርሱን ማንነትና ተልእኮ እንዲያውቁ ማድረግ ነው። በሉቃስ ወንጌል፤ ኢየሱስ የፈወሳቸው ሰዎች እግዚአብሔርን ሲያከብሩና ሲያመሰግኑ እንመለከታለን (ሉቃ. 5÷25፤ 13÷13፤ 17÷15፤ 18÷43)። ሰዎቹ በተኣምራቱ ብቻ ሳይሆን የተገረሙት፤ ተኣምራቱ በሚያስተላልፈው ወሳኝ መልእክት እንጂ—ይኸውም አምላክ ያራራልናል፤ ቸርነቱ ከእኛ ጋር ነው በሚለው ብርቱ መልእክት እንጂ።

ኢየሱስ ሰዎችን የፈወሰው ትንቢትን ለመፈጸም ነበር። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ኢየሱስን በተመለከተ ከ300 በላይ ትንቢቶችን ተናግረዋል። ኢየሱስ ያ የሚጠበቀውና ነቢያት የተናገሩለት መሲሕ መሆኑን ለማስረገጥ ተኣምራትን አድርጓል። በሉቃስ ወንጌል ላይ ኢየሱስ በነቢዩ ኢሳይያስ የተነገረውን ትንቢት ካነበበ በኋላ፤ "ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ" አለ (4÷21)። ስለዚህ ፈውስ ክርስትና የትንቢት ፍጻሜ እንደ ሆነ አመላካች ነው። ኢየሱስ እጁ የሰለለችውን ሰው ከፈወሰ በኋላ፤ በነቢዩ ኢሳይያስ የተጻፈው ይፈጸም ዘንድ መሆኑን ወንጌላዊው ማቴዎስ ነግሮናል (12÷17-21)። ኢየሱስ የምድራዊ አገልግሎቱ መሲሑ ሲመጣ የሚከውነው ነገር እንደ ሆነ ተናግሯል (ሉቃ. 7÷21-23)።

ከእነዚህ መሠረታውያን ነጥቦች የምንማረው ቍም ነገር የተኣምራት ቀዳማይ ዐላማ እግዚአብሔርን ማክበር እንደ ሆነ። እንዲሁም ክርስትና ለምች ሁሉ ከእማማቸው ይፈወሳሉ የሚል ጥቅል ዋስትና አልሰጠም።

## ሰ. ክርስትና ለሀብት ዋስትና አልሰጠም!

መጽሐፍ ቅዱስ ምድራዊውን ብልጽግና ሳይሆን፣ ሰማያዊውን ብልጽግና አጥብቀን እንድንሻ ያሳስበናል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ምድራዊ ንዋይ እንዴት ይሰበስባሉ የሚለውን ጉዳይ አያስተምርም። ባንጻሩም ግል ለድኾች የተለየ አምላካዊ ትኩረት ተሰጥቶ እናነባለን። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ቀን እጦትም ሆነ አጥረት የማይኖሩበት ዘመን እንደሚመጣ በግልጽ ይናገራል። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር አዲስ በሚያደርግበት ጊዜ ሁሉም ነገር የእኛ ይሆናል—ቢያንስ የሚያስፈልገን ነገር ሁሉ በሚያስፈልገን መጠን ይኖረናል። ይህን ደግሞ እግዚአብሔር ራሱ፣ በራሱ የጊዜ ሰሌዳ እውን ያደርገዋል። እስከዚያ ቀን ድረስ መስጠት (ብድራት ሳይጠብቁ መስጠት) የእግዚአብሔር ዘይቤ እንደ ሆነ ሁሉ፣ የእኛም ዘይቤ መሆን አለበት። መስጠት የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው። እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ሰጭ ነው። እኛም በዚህ ባሕርይ ልንወረስ ይገባል። ገንዘብና ምድራዊ ሀብት ከእኛ ጋር ለዘላለም አይኖሩም፤ የገንዘብም ሆነ የምድራዊ ሀብት ፋይዳው ውሱን ነው። በመሆኑም ገንዘብና ምድራዊ ሀብት እየተጐዱ በመስጠት ለሚልቀው ፋይዳ እንዴት ሲውል ይችላል ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል።

በዘመኑ ብልጽግና እንደ ወንጌል ቢቈጠርም በእውነተኛው ወንጌል ግን አይደለም። የብልጽግና ወንጌል የሰዎችን ሁሉ ችግር አይፈታም። የብልጽግና ወንጌል ባለጠጎች ዘንድ ሲደርስ ይሸመደመዳል፤ ምክንያቱም ምኑን ያበለጽጋቸዋል፤ እነርሱ ራሳቸው



ገና ድሮ ባለጠጎች ናቸው። የብልጽግና ወንጌል ባለጠጎችን አያጓጓም። የብልጽግና ወንጌል የሚያጓጓው ምስኪን ድኾችን ብቻ ነው[60]።

በመሠረቱ የሰዎች ትልቁ ችግር ማግኘትና ማጣት አይደለም፤ ወይም ሀብትና ድኽነት አይደለም። የሰዎች ትልቁ ችግር ኀጢአትና መዘዙ ነው። በዚህ ረገድ ሰዎች ሁሉ—ሀብታምም ሆኑ ድኾ—እኩል ናቸው። ሀብታሞችም ሆኑ ድኾች ኀጢአተኞች ናቸው፤ እናም ለድኾች ኢየሱስ እንደሚያስፈልግ ሁሉ ለሀብታሞችም ኢየሱስ ያስፈልጋቸዋል። ሰዎች ሁሉ ኀጢአተኞች ከሆኑ ኢየሱስ የማያስፈልገው ምድራዊ ፍጡር በጭራሽ ሊኖር አይችልም። ጳውሎስ "ሰዎች ሁሉ ከኀጢአት በታች" መሆናቸውን ሲናገር "ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉም ተሳስተዋል፤ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል" ይላል (ሮሜ 3፥9-11)። ጳውሎስ ችግራችን ምን እንደ ሆነ ከነገረን በኋላ መፍትሔውንም ነግሮናል። "አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጧል፤ እርሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው ጽድቅ ነው" (ሮሜ 3፥21-22)።

ምንም ተባለ ምን ክርስቲያኖች ከክርስቶስ የተነሣ ባለጠጋ ናቸው። እግዚአብሔር እንዲመረምረን መፈለግ ትልቅ ነገር ነው። ነቢዩ እንዲህ ብሎ ይጠይቃል፤ "ምን ይዤ ወደ እግዚአብሔር ፊት ልምጣና በልዑል አምላክ ፊት ልስገድ? የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የአንዱን ዓመት ጥጃ ይዤ በፊቱ ልምጣን? እግዚአብሔርስ በሺህ አውራ በጎች ወይስ በእልፍ የዘይት ፈሳሾች ደስ ይለዋልን? ወይስ

---

60 *Bradley A. Koch, The Prosperity Gospel and Economic Prosperity: Race, Class, Giving, and Voting* (Indiana University: PhD Diss, 2009) 14-21.

የበኵር ልጄን ስለ በደሌ የኾዴንም ፍሬ ስለ ነፍሴ ኀጢአት እሰጣለሁን? ሰው ሆይ፤ መልካሙን ነግሮሃል፤ እግዚአብሔር ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? ፍርድን ታደርግ ዘንድ፤ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፤ ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን?" (ሚል 6÷6-8)።

አንደ ሉዓላዊ ፈቃዱ አምላካችን እግዚአብሔር ቱጃር ሊያደርገን ቢችልም ክርስትና ግን አማኞች ሁሉ ባለጸጋ ይሆናሉ የሚል ዋስትና አልሰጠም። መጽሐፍ ቅዱስ የዕለት እንጀራችንን መጠየቅ እንደምንችል ነግሮናል፤ በመጠን በመኖር ክርስቶስን የሕይወታችንና የኑሮአችን ማዕከል አንድናደርግ መመሪያ ተሰጥቶናል። በምናልፍባቸው ማናቸውም ዐይነት ጉዳናዎች፣ እርሱን በማክበርና በመፍራት የእርሱ አንደ ራሴ ሆነን እንድንኖር ተጠይቀናል። አምላክ በሰጠን ዕውቀት፣ ገንዘብ፣ ጤንነት፣ ጊዜ፣ ክኂሎት ወዘተ ክርስቶስን መሰበክና ቅዱሳንን ማገልገል ይጠበቅብናል። ክብር ሁሉ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ይሁን።



# ክፍል ስምንት

## ክርስቲያን አጋንንት ይገቡበታልን?



እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፣ "ክርስቲያን አጋንንት ይገባበታል" የሚለው አስተሳሰብም ሆነ አስተምህሮ፣ እንደ ትልቅ ኑፋቄ ይታይ ነበር። የቤተ ክርስቲያናችን አንጋፋ ወንጌላዊ፣ ይህን ትምህርት በድብቅ ተቀብለው፣ የተማሩትን በስውር ሲያስተምሩ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ እጅ ከፈንጅ[1] ያዘቻቸው።

[1] ትምህርቱ እንደ "ፈንጅ" ይታይ ነበር።

በወቅቱ የነበሩት የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች፣ ነገረ መስኮት ቀመስ (አንዳንዶቹም ጠገብ) ነበሩና፣ ግለሰቡ የማርከሻ ትምህርት ስተከታታይ ወራት እንዲማሩ፣ በማኅበረ ምዕመናኑ ፊት ቆመው የነገረ መስኮት ንስሓ እንዲገቡ፣ ለተወሰኑ ወራትም ከማናቸውም አገልግሎት ታግደው፣ በጾምና በጸሎት ራሳቸውን እንዲመረምሩ ቍርጥ ብያኔ ተላለፈባቸው።

ምክንያቱም ክርስቲያን አጋንንት ይገቡበታል የሚለው ትምህርት፣ ስወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሠረተ እምነት፣ ሲበዛ እንግዳ እንዲሁም ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ነው። በተገላቢጦሹ ዛሬ፣ "ክርስቲያን አጋንንት አይገባበትም" የሚል ሰው ቢገኝ፣ ከቤተ ክርስቲያን አባልነት ባይሰረዝ እንኳ፣ እንደ ትንግርት እንደሚታይ አያጠያይቅም—ቢያንስ በአብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት። እንዲያውም ይህን አግድም ዐደግ ትምህርት ስሕተት ነው የሚሉ ሰዎች ወየውላቸው—"የአእምሮ ሰው"፣ "አውቃለሁ ባይ"፣ "የመንፈስ ቅዱስ ተቃዋሚ"፣ "መንፈሳዊ ነገር የማይገባው ሥጋዊ ክርስቲያን"፣ "የመንፈስ አሠራር የማይረዳ"...የሚል መታወቂያ ይሰጠዋል (ይወጣስታል)።

መቼም አሮጌ አስተምህሮ ሁሉ ትክክል ነው፣ አዲስ ትምህርት ሁሉ ስሕተት ነው የምል ሞኛሞኝ ሰው አይደለሁም። "አሮጌ" እንዲሁም "አዲስ" የሚለው፣ ዕድሜን ብቻ እንጂ ይዘትን ታሳቢ ያላደረገ ገስጻ እንደ ሆነ እረዳለሁ። ስለዚህ "አሮጌም" ሆነ "አዲስ" ትምህርት፣ አይነቀስም አይገሠሥም ብለን በተቀበልነው በቃስ እግዚአብሔር መመዘን፣ መገናዘብ፣ መመሳከር...ይኖርበታል።

ክርስቲያን አጋንንት ይገባበታል የሚለው ትምህርት፣ ስወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትም ሆነ፣ ለፕሮቴስታንቱ መሠረተ እምነት አዲስ ነው። "መርገም ከምንዝላት፣ ከእንጀላት ይተላለፋል"



እንደሚለው ትምህርት፣ "ክርስቲያን አጋንንት ይገቡበታል" የሚለውም ዘመን አመጣሽ ትምህርት ነው። ካልተሳሳትሁ በቀር፣ የሁለቱም ትምህርቶች ቀዳማይ አመንጪና አስተዋዋቂ ዴሬክ ፕሪንስ ናቸው። እነዚህም ሁለት ጣምራ ትምህርቶች አስተማሪዎቻቸው፣ "የዐርነት አገልግሎት" በማለት ይጠሯቸዋል። ክርስቲያኑን ማኅበረሰብ፣ "ከዘር ከሚመጣ መርገም ነጻ ማድረግ" እንዲሁም "ከአጋንንት ቍጥጥር ዐርነት ማውጣት"።

እንደ አሜሪካዊው ፒተር ዋግነር *(Charles Peter Wagner)* ያሉ ሰዎች ደግሞ፣ በዚሁ እስተምህሮ ላይ፣ "የግዛት መናፍስት" *("Territorial Spirits")* የሚለውን ትምህርት አክለውበት ብቅ አሉ (ለግዛት መናፍስት የሚጠቀሱት ጥቅሶች እነሆ:— ዳን. 10፤ ዮሐ. 12÷31፤ 14÷30፤ 16÷11፤ ማር. 5÷10፤ ኤፌ. 6÷12)[2]። ከዚያም በየአብያተ ክርስቲያናቱ ሁሉ፣ የሰንበት አምልኮ ከመጀመሩ በፊት፣ "በዐየር ላይ ያሉትን እርኩስ የግዛት መናፍስት እየተቃወምን እንጸልይ!" መባል ተጀመረ። "ስም ... ስም ... ልቀቅ ... በሰሜን ... በደቡብ ..."። ቤተ ክርስቲያን የሥርዐት ሳይሆን፣ የሁከት ማዕከል ሆነች። የአልቃይዳ አጥፍቶ ጠፊ የገባበት አዳራሽ መሰለች[3]። ሐዋርያው ጳውሎስ ያላመኑ ሰዎች ወደ ጉባኤያችሁ

[2] ይህ አስተምህሮ በአንዳንድ አካባቢ መንፈስ ቅዱስ እንዳይወርድ፣ ጸሎታችን ምላሽ እንዳያገኝ የሚገዳደሩ እንዲያውም የሚከሰክሱ የተግዳሮት መናፍስት አሉ። አንዳንድ አካባቢ ደግሞ እግዜር፣ ሳይጠራ ከተፍ ይላል። ምክንያቱም ዐየሩ ነጻ ነውና። የሚል ትምህርት ነው።

[3] በዚህ ውጥንቅጥ መሀከ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባው የሄድሁት የእኅቴ ልጅ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባየው ሁከት ምክንያት መንፈሱ እጅግ ታወከ፣ ኅሊናው ተበጠበጠ፤ "ይህ ነገር ምንድን?" ነው ሲል ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ በስሆሳስ ደጋግሞ ጠየቀኝ። "አይዞህ ሰጥቂት ደቂቃ ነው ይቆማል" አልሁት። ነገሩ ከመቆም ይልቅ እየተባባሰ ቀጠለ። እንዲያውም አንዳንዶች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው፣ በልሳን መናገር ጀመሩ። አንዳንዶቹ እየተንዘፈዘፉ ወደቁ። "እባክህ አልተመቸኝም" አለኝ፣

ቢገቡ "ዐበዳችሁ አይሉምን?" የሚለው ትምህርት በሙላት ተፈጸመብን። ሃይ ባይ ባጡ እንግዳ ደራሽ ትምህርቶች፣ ቤተ

---

በሚያሳዝን ድምፀት፣ በተማጽኖ መንፈስ። እንዴት ላረጋጋው እንደምችል ማሰብ ጀመርሁ፤ አንዳችም መላ ሊመጣልኝ አልቻለም፤ ምን ዐይነት መላ ሊገኝ ይችላል? እንኪን በዚያ ቅጽበት እስከ ዛሬ መፍትሔ ልናገኝለት መቼ ቻልንና? "ኋላ ይህ የመንቀጥቀጥና የማጓራት ነገር ወደ እኛ ሊመጣ ይችላል፤ እኔ ይህን በፍጹም አልፈልግም" አለ። እጅግ በጣም ደነገጠ። "ከቤተ ክርስቲያኒቱ አስወጣኝ" ሲል ደጋግሞ ተማጸነኝ—በእኔ ሃይ ባይነት ካልሆነ በስተቀር መናፍስቱ ዘለው የሚሰፍሩበት መሰለው። "እኔ አይዞህ ይቆማል" በሚለው ምላሼ ጸናሁ፤ ከብዙ ዓመት ልፋት በኋላ ያመጣሁት ሰው በዚህ መልክ እንዴት ይሂድብኝ? ኋላ ፈትለክ ብሎ ወደ በሩ እየሮጠ ሄደ። ከረጅም ዓመት ያላሰለሰ ጉትጎታ በኋላ፣ እሺ ብሎኝ ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጣ ሰው፣ በዚህ መንገድ ወደ ቤተ ክርስቲያን ዳግም ተመልሶ ሳይመጣ፣ በዚያው ዓመት በድንገተኛ ሕመም አሸለበ። ከክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐት የለሽነትና ሁከት የተባረረው ወንድሜ፣ ያለክርስቶስ ኢየሱስ በሞት ተጠናቀቀ። "በአምልኮ ችሁ ሥርዐት ይኑራችሁ"፣ "የማያምኑ ሰዎች በመካከላችሁ ቢመጡ አይታነጹበትም"፤ "ዐበዳችሁ ይላሉ"፤ "እግዚአብሔር የሥርዐት አምላክ ነው" የሚለው የሐዋርያው የጳውሎስ ምክር፣ ከማንም ይልቅ በእኔ መሰል ሕይወት ውስጥ ላለፉ ሰዎች ይገባናል፤ ምጡና ጣሩ ጉልቶ ይሰማናል። ዛሬ በየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚታየው ሁከት እንኪን ላላመነው፣ አማኝ ነኝ ለሚለው፣ ለረጅም ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ለተመላለሰውም ሰው፣ እጅግ ሲበዛ ግራ የሚያጋባ ነው። መንፈስን ያጣልቃል፤ ነፍስን ያውካል። ሐዋርያው ጳውሎስ ተርጓሚ ከሌለ፣ "ልሳን አትናገሩ" የሚለውን ግልጽ ምንባብ ጠቅሰን ሃይ ማለት አልቻልንም። "ሐዋርያት"፣ "ነቢያት"፣ "የእግዚአብሔር ሰው" የሚባሉ ሰዎች በግልጽ ስለሚያደርጉት፣ እኛ ምን ሆነን የሚሰማን ይገኛል? የሌላውን አላውቅም እኔ ግን አዳዲስ ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዞ መሄድ የማልችልበት ደረጃ ላይ ደርሻለሁ። እንኪን ሰው ይዘን ለመሄድ እኛም መሄድ በብዙ መልኩ ችግር ሆኖብናል። ስሜት ጣራ ያልነካበት ጉባኤ ፈልጎ ማግኘት አስቸጋሪ እየሆነ ነው። ከአንጡ ወይም ከመሰል ኑፋቄ ጋር ያልተቀላቀለ ንጹሕ ወንጌል የሚሰበክበት ዐውደ ምሕረት አለ ማለት በማይቻልበት ደረጃ ተደርሶአል። ለዚህ ነው የዘማሪ ዶክተር ደረጀ ከበደ መዝሙር፣ እጅግ ትልቅ ትርጉም ይዞ ከተፍ የሚለው—ሥርዐት የሌለበት፣ ገደብ የሌለበት...ሰው ተግተለተለ፣ እንክርዳዱ ስንዴ ተከኣው በግ መሰለ...አወይ ነ—ጻ—ነ—ት !



ክርስቲያን መታወክ ጀመረች፤ የአስተምህሮ መዋቅሮቿ ሁሉ ታዛ አልባ ሆኑ። ይኸው በዚህ ውጥንቅጥ እስከ ዛሬ አለን!

"የዐርነት" አገልግሎት የሚባለው፣ "የክርስቲያኖችን መርገም መስበር" እንዲሁም "አጋንንት ያለባቸውን ክርስቲያኖች በውስጣቸው ካለው አጋንንት ነጻ ማድረግ" ነው[4]። የዘመኑ አባይ ነባዮች በእኛው መካከል ዐድገው የጉለበቱ እንጂ፣ ከሌላ ምድር የመጡ ሰዎች አይደሉም። ባይሆን እነዚህን አስተምህሮዎች ሰብስበውና

---

[4] የእንቅስቃሴው መምህራን፣ "demon possessed" እና "demonized" የሚሉትን የእንግሊዝኛ ቃላት በሁለት የተለያዩ መንገዶች ይጠቀሙባቸዋል። "demonized" የሚባለው በአጋንንት በውስጡ አድሮ፣ ሙሉ ለሙሉ በቍጥጥራቸው ሥር ያደረጉትን ሰው የሚያመለክት ሲሆን፣ "demon possessed" ደግሞ አጋንንት በክርስቲያን የተወሰነ ወይም በመላ አካሉ ውስጥ ያድራል የሚለው ነው። አንዳንዶች ይህን አካሄድ አገላብጠው ይጠቀማሉ። ዞር ዞር ግን የእንቅስቃሴው አራማጆች፣ "ዳግም ልደት ያገኘ ክርስቲያን አጋንንት ሊያድርበት ይችላል፤ ስለዚም በክርስቲያን ውስጥ የሚያድረውን አጋንንት በዐርነት አገልግሎት ማስወጣት ያስፈልጋል ባይ ናቸው"። ግሪክ ሊክሲኮንም (lexicon) ሆኑ፣ የነገረ መለኮት መዝገበ ቃላት፣ "ዳይሞኒዞማይ" (δαιμονίζομαι) የሚለውን የግሪክ ቃል፣ በአጋንንት መያዝ ("to be possessed by a demon") ብለው ነው የተረጐሙት (δαιμονίζομαι; 1 aorist passive participle δαιμονισθείς; (δαίμων): to be under the power of a demon)። የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት "demon possession" የሚለውን ቃል የተረጐሙት፣ "to gain or exert influence or control over; dominate" (American Heritage Dictionary, 3rd ed.)። ከዚህ የተነሣ "demon possession" የሚለውን ቃል፣ በቍጥጥሩ ወይም በተጽእኖው ውስጥ መኖር ብለን ልንተረጕመው እንችላለን (ማቴ. 4÷24፤ 8÷16:28:33፤ 9÷32፤ 12÷22፤ 15÷22፤ ማር. 1÷32፤ 5÷15፤ ዮሐ. 10÷21)። የግሪኩን ቃል አጠቃቀም በተመለከተ የሚከተሉትን ሁለት መጻሕፍት ይመልከቱ:— Louw and Nilda, *Greek-English Lexicon of the NT Based on Semantic Domains* (New York: United Bible Society, n.d.), 1:147. Bauer, Ardnt, Gingrich, Danker, *A Greek-English Lexicon of the New Testament* (Chicago: University of Chicago Press, 1979), 169. የነገረ መለኮት መዝገበ ቃላት:— Gerhard Kittel, ed., *Theological Dictionary of the New Testament* (Grand Rapids, MI.: Eerdmans, 1964), 2:19. Colin Brown, ed., *New International Dictionary of New Testament Theology* (Grand Rapids, MI.: Zondervan, 1986), 1:453.

አቀናጅተው፣ በአለባበስና ባረማመድ አምረውና ደምቀው “ተገለጡልን” እንጂ።

ክርስቲያኖች በሰይጣንም ሆነ በአጋንንት፣ ጥቃት እንደሚደርስባቸው እሙን ነው። በዚህም አግባብ መጽሐፍ ቅዱስ ነቅተን እንድንኖር አበክሮ ያስገነዝባል (ነህ. 9÷6፤ ሉቃ. 2÷13-15፤ ኤፌ. 6÷12፤ ቈላ. 1÷15-16፤ 2ነገ. 6÷11-17፤ ዳን. 10÷7-17)። ከዚህ ባለፈ ግን፣ ዳግም የተወለደ ክርስቲያን፣ የመንፈስ ቅዱስ እንጂ፣ የአጋንንት ማደሪያ ሊሆን በጭራሽ አይችልም።

ከዚህ በመቀጠል፣ “ክርስቲያን አጋንንት ሊገቡበት ይችላሉ” ለሚለው አስተምህሮ ማስደገፊያ፣ ተዘውትረው የሚጠቀሱትን ዋና ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት እንዲሁም ሙግቶች ለማየት እንሞክራለን። ለሙግቶቹም አግባብነት አላቸው የምላቸውን ምላሾች አስከትላለሁ።

## ሙግት አንድ

አጋንንት በክርስቲያን ውስጥ ሊገባ ይችላል ለሚለው ትምህርት ተዘውትሮ የሚጠቀሰው ማስረጃ፣ ንጉሥ ሳኦል የተቀባ የአምላክ አገልጋይ ሆኖ ሳለ፣ አጋንንት ገብተውበታል (1ሳሙ. 18÷10-11፤ 19÷9-10)፤ በዚህ ትልቅ የአምላክ ባለሟል ውስጥ የሚገቡ ከሆነ፣ በእኛ የማይገቡበት አንዳችም ምክንያት የለም። የተጠቀሱትን ክፍሎች አንብበን ወደ ምላሹ እንዘልቃለን:—

> “10. በማግስቱም ከእግዚአብሔር የታዘዘ ክፉ መንፈስ በሳኦል ላይ በኀይል መጣበት፣ በዚህ ጊዜ ዳዊት ወትሮ እንደሚያደርገው ሁሉ በገና ሊደረድር፣ ሳኦል በቤቱ ሆኖ ትንቢት ይናገር ነበር። ሳኦል በእጁ ጦር ይዞ ነበር፤ 11. እርሱም፣ ‘ዳዊትን ከግድግዳው ጋር አጣብቀዋለሁ’ ብሎ በማሰብ ጦሩን ወረወረበት፤ ዳዊት ግን ሁለት ጊዜ ከፊቱ ዘወር አለ” (1ሳሙ. 18)።

> “9. ነገር ግን ሳኦል ጦሩን ይዞ በቤቱ ተቀምጦ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ መንፈስ መጣበት፤ ዳዊት በገናውን ይደረድር ነበር፣ 10. ሳኦልም ከግድግዳው ጋር ሊያጣብቀው ጦሩን ወረወረበት፤ ነገር ግን ዳዊት ዘወር በማለቱ ሳኦል የወረወረው ጦር በግድግዳው ላይ ተሰካ። በዚያች ሌሊት ዳዊት ሸሽቶ አመለጠ” (1ሳሙ. 19)።

*ይህ ሙግት አራት መሠረታውያን ችግሮች አሉበት:—*

***አንደኛው፣*** *ከትረካ መጻሕፍት ተነሥቶ አስተምህሮ ማዋቀር፣ እጅግ ሲበዛ ስሕተት እንደ ሆነ በዚህና በተለያዩ መጻሕፍት ላይ በስፋት ሞግቻለሁ። የትረካ ወይም የታሪክ መጻሕፍት ስለአንድ ክሥተት መናገራቸው፣ ያን ሁኔታ እኛም እንድንቀበለው ወይም በየዘመናቱ ለሚኖሩ ሰዎች መመሪያ እንዲሆን ተብሎ አይደለም። ሥነ ምግባራዊም ሆነ አስተምህሮአዊ መሠረቶችን የምናዋቅረው፣ ከታሪክ መጻሕፍት ሳይሆን፣ ምንጨታዊ (የትምህርት) ምንባባት ነው። ባይሆን ከምንጨታዊ ምንባባት የተማርናቸውን መርሖች፣ በታሪክ መጻሕፍት ውስጥ እንዴት ተግባራዊ ሆነው እንደ ቀረቡ በግልጽ እንመለከታለን። ስለዚህ በንጉሥ ሳኦል አንድ ነገር መከሠቱ፣ ስለተከሠተው ጉዳይ ዝርዝር (ማለትም ለምን፣ እንዴት፣ ወዘተ የሚል) መረጃ ስላልተሰጠን፣ ከዚያ ቊንጽል አሳብ ተነሥተን ወደ ድምዳሜ መድረስ ሲበዛ አስቸጋሪ ይሆናል።*

*ሁለተኛ፣* በእምላክ በተቀባ ጊዜ የእግዚአብሔር ሰው እንደ ነበር እንመለከታለን (1ሳሙ. 10÷1+)። የኋላ ኋላ የታየው ግን ሰውጡ እውነተኛ ሰውጥ እንዳልነበር የሚያሳይ ነው። "ወንድሞቼ ሆይ፤ አንድ ሰው እምነት አለኝ ቢል ሥራ ግን ባይኖረውምን ይጠቅመዋል? እንዲህ ያለው አምነት ሊያድነው ይችላልን?" (ያዕ. 2÷14) የሚለው አሳብ፣ በእምላከ መመረጡና አምላክ እርሱን መጠቀሙ፣ እውነተኛ አማኝ ነበር ወደሚለው ድምዳሜ አያደርሰንም። እግዚአብሔር አረማዊ የሆነውን ንጉሥ፣ ንጉሥ ቂሮስን የእግዚአብሔርን ዐላማ እንዲያስፈጽም አምላክ ቀብቶ እንዳለነሣው መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራልና (ኢሳ. 45÷1)።

*ሦስተኛ፣* በብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ የሚያድረው በጊዜያዊነት ሊሆን (መዝ 51÷11፤ መሳ. 13÷25፤ 1ሳሙ. 16÷14፤ ኢሳ. 63÷10-11)፣ በሐዲስ ኪዳን ግን በቋሚነት በአማኙ ሕይወት ውስጥ ይኖራል (1ቆሮ. 3÷16፤ 6÷19፤ 2ቆሮ. 6÷16፤ 2ጢሞ. 1÷14፤ ሐሥ. 6÷5፤ ኤፌ. 5÷18፤ ሮሜ 8÷9፡11፡15፤ ዮሐ. 16÷13፤ ገላ. 4÷6፤ 1ዮሐ. 2÷27)። በብሉይ ኪዳን በአማኙ ውስጥ በጊዜያዊነት ብቻ ስለሚኖር የእምላክ መንፈስ በተለየው ጊዜ፣ እርኩሳን መናፍስት ሊያድሩበት ይችላሉ። በሐዲስ ኪዳን ግን መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ በቋሚነት መኖሩ፣ እርኩሳን መናፍስት በአማኙ ሕይወት ውስጥ እንዲያድሩ ዕድል አይሰጥም። የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከእርኩሳን መናፍስት (ከቡዔልዜቡል) ጋር እንዳችም ኅብረት እንደሌለው፣ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል (የሚከተለውን ምንባብ ይመለከቷል ማቴዎስ 12÷24-35)።

*አራተኛ፣* የነገረ መለኮት ምሁራን፣ በሳኦል ላይ አጋንንት መምጣታቸውና መሄዳቸው፣ አጋንንት በእርሱ ውስጥ ማደራቸውን



በጭራሽ አያሳይም ባዮች ናቸው። ለምሳሌ ቶማስ አይስና ሮበርት ዲን፣ "የዕብራይስጡ ምንባብ፣ በሳኦል ላይ እርኩስ መንፈስ እንደ መጣበትና ኋላም ከእርሱ እንደ ሄደ ይገልጻሉ። ይህ ማለት ግን በሳኦል ላይ አጋንንት ገባበት ማለት በጭራሽ አይቻልም"[5] ባዮች ናቸው። ስለዚህ "መጣበት" ማለት "ገባበት" ወይም "ዐደረበት" የሚለውን አሳብ የሚያጸና አይደለም። ስለዚህ የንጉሥ ሳኦል ታሪክ፣ ክርስቲያን ላይ አጋንንት ይገባሉ ለሚለው አስተምህሮ፣ በጭራሽ ድጋፍ ሊሆን አይችልም።

## ሙግት ሁለት

በሉቃስ 13÷10-17 ባለው ክፍል፣ "የአብርሃም ልጅ" ተብላ ስለተጠራች ሴት እናነባለን። ነገር ግን "የድካም መንፈስ" እንደ ነበረባት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። እንዲያውም ሰይጣን ለ18 ዓመት እንዳሰራት ተገልጾአል (ቍጥር 16)[6]። የክፍሉን ሙሉ ዐውደ ካነበብን በኋላ ወደ ግምገማው እንሄዳለን:—

"10. ኢየሱስ በሰንበት ቀን በአንድ ምኵራብ ያስተምር ነበር። 11.
በዚያም የድካም መንፈስ ዐሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ አካለ
ስንኩል ያደረጋት አንዲት ሴት ነበረች፤ እርሷም ከመጕበጧ

---

[5] *Thomas Ice and Robert Dean, Jr., Overrun by Demons: The Church's New Preoccupation with the Demonic (Eugene, OR: Harvest House Publishers, 1990), 125.*

[6] አንዳንድ ጸሐፍያንም ይህቺ ሴት አማኝ ነበረች ብለው ጽፈዋል። ለዚህ ማስረጃ አድርገው የጠቀሱት *አንደኛ፣* በምኩራብ እግዚአብሔርን ማምለኳ፤ *ሁለተኛ፣* በፈውሷ ምክንያት እግዚአብሔርን ማመስገኗ፤ *ሦስተኛ፣* የአብርሃም ሴት ልጅ የሚለው ቃል ከዘኬዎስ ትረካ ጋር ሲነጻጸር ድነት ያገኘች ሴት እንደ ነበረች ያሳያል (ሉቃ. 19÷9)። C. *Fred Dickason, Demon Possession and the Christian: A New Perspective (Chicago: Moody Press, 1987),* 124-125. እነዚህ ሴቲቱ ክርስቲያን ነበረች ለማለት አሳማኝ ነጥቦች ላለመሆናቸው፣ በቀጣዮቹ ተከታታይ ገጾች ላይ የቀረበውን ምላሽ ይመልከቱ።

የተነሣ ፈጽሞ ቀና ማለት አትችልም ነበር። 12. ኢየሱስም ባያት ጊዜ ጠራትና፣ 'አንቺ ሴት፤ ከሕመምሽ ነጻ ወጥተሻል' አላት፤ 13. እጁንም በላይዋ ጫነ፤ እርሷም ወዲያው ቀጥ ብላ ቆመች፤ እግዚአብሔርንም አመሰገነች። 14. የምኵራቡ አለቃ ግን፣ ኢየሱስ በሰንበት ቀን ስለ ፈወሰ ተቈጥቶ ሕዝቡን፣ 'ሥራ ሊሠራባቸው የሚገባ ስድስት ቀኖች አሉ፤ ስለዚህ በእነዚያ ቀኖች እየመጣችሁ ተፈወሱ እንጂ በሰንበት ቀን አይደለም' አላቸው። 15. ጌታም መልሶ እንዲህ አለው፤ 'እናንት ግብዞች፤ ከእናንተ መካከል አንድ ሰው በሬውን ወይም አህያውን በሰንበት ቀን ከማደሪያው ፈትቶ ውሃ ሊያጠጣ ይወስደው የለምን? 16. ታዲያ፣ ይህች ሴት የአብርሃም ልጅ ሆና ሳለች ዐሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ በሰይጣን ታስራ ስትኖር፣ ከዚህ እስራት በሰንበት ቀን መፈታት አይገባትምን?' 17. ይህን በተናገረ ጊዜ ተቃዋሚዎቹ ሁሉ ዐፈሩ፤ ሕዝቡ ሁሉ ግን እርሱ ባደረገው ድንቅ ሥራ ሁሉ ደስ አላቸው" (ሉቃስ 13)።

ይህ ሙግት እያስሄድም። ***አንደኛ፣*** "የአብርሃም ልጅ" መባሏ፣ የይሁዲ ወገን መሆኗን እንጂ፣ ክርስቲያን መሆኗን የሚያሳይ አይደለም። ጌታ ዘኬዎስን፣ "የአብርሃም ልጅ" ማለቱ፣ እውነተኛ አይሁድና የአሮጌው ኪዳን አባል መሆኑን የሚያሳይ ነው። ይኸውም የሮማውያን ቀረጥ ሰብሳቢ ሆኖ ማገልገሉን በሚያነጻጽር መልኩ[7]።

***ሁለተኛ፣*** ግስስቧ በምኵራብ ማምስኳና ስፈውሷ እግዚአብሔርን ማመስገኗ፣ ክርስቲያን ነች ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስን አይደለም። ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን በምኵራብ ያመልኩሉ፣ አምላከን ያመስግናሉ፤ ነገር ግን እውነተኛ አማኞች ነበሩ ማለት አንችልም።

***ሦስተኛ፣*** "የድካም መንፈስ" ነበረባት ማለት፣ በሽታውን ያስከተለው መንፈስ ነው ማለት እንጂ፣ ራሱ የድካም መንፈስ አድሮባታል/ገብቶባታል ማለት ላይሆን ይችላል። እንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጕሞች፣ "በመንፈስ ምክንያት የመጣ በሽታ" ሲሉ ተርጕመውታል ለምሳሌ *(NAS—"Sickness caused a spirit" NIV* ደግሞ፣ *"Crippled by a spirit"* ብሎታል)። ነባሩ ትርጕም፣ "የድካም መንፈስ ***ያደረባት***" ብሎ ይተርጕመው እንጂ፣ አዲሱ መደበኛ ትርጕም፣ እንደ እንግሊዝኞቹ፣ "አካለ ስንኩል ***ያደረጋት***" ሲል ተርጕሞታል[8]።

***አራተኛ፣*** በዚህ ዐውደ ምንባብ ውስጥ ልናስተውለው የሚገባን ሌላው ነጥብ፣ ጌታ ከበሽታዋ እንደ ፈወሳት እንጂ፣ አጋንንት እንዳወጣላት ያለመነገሩ፣ እርኩስ መንፈስ የበሽታው ምክንያት እንደ ሆነ እንጂ፣ እርኩስ መንፈስ ያደረባት ሴት እንዳልሆነች ሊያሳይ ይችላል[9]።

---

[7] ይህ ሐሳብ የተወሰደው፣ ከሚከተለው የግሪክ ሌክሲከን ነው:— *Joseph H. Thayer, Thayer's Greek-English Lexicon of the New Testament (Grand Rapids, MI.: Baker Book House, 1977),* 292.

[8] በኮሪ ጽሑፉ፣ "καὶ ἰδοὺ γυνὴ πνεῦμα ἔχουσα ἀσθενείας" ይለዋል። የውይይቱ ማዕከል "ኤኮሜኖስ" (ἐχόμενος) የሚለው ቃል ነው። ቃሉ፣ "ኤኮ" (ἔχω) ከሚለው ግሥ እንቀጽ የተገኘ ሲሆን፣ ቃሉ በርካታ አማራጭ ትርጕሞች ሊወክል ይችላል። ይኸውም 1. አንድ ዕቃ/ንብረት ***ለማ*** ማለት (ማቴ 14÷17)፣ 2. አንድ ነገር በእጅ ***መጨበጥ*** (ራእ 6÷5)፣ 3. የተወሰነ አመለካከት ***መያዝ*** (ማቴ. 14÷5፤ ሉቃ. 14÷19) 4. ልብስ ***መልበስ*** (ማቴ. 3÷4)፣ 5. ችሎታ ***ማግኘት*** (ኤፌ. 4÷28፤ 2ጴጥ. 1÷15)፣ *James Swanson, Dictionary of Biblical Languages With Semantic Domains: Greek (New Testament), electronic ed. (Oak Harbor: Logos Research Systems, Inc., 1997).*

[9] ለዚህም ይመስላል ከላይ የጠቀስነው ጸሐፊ፣ "አፋችንን ሞልተን ሴትየዋ አጋንንት ነበረባት ማለት አንችልም" የሚለው። ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 127።

## ሙግት ሦስት

አጋንንት በክርስቲያኖች ውስጥ ያድራሉ የሚለው አስተምህሮ፣ አቋሙን እንዲያጸናለት ከሚያቀርበው ሙግት ውስጥ የሚከተለው ትልቅ ቦታ የሚይዝ ነው። በሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናቸው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ብዙ ክፍሎች እንዳሉት ማወቅ አለብን። በብሉይ ኪዳን የነበረው ቤተ መቅደስ የደጁ አደባባይ፣ ቅድስትና ቅድስተ ቅዱሳን ከሚባሉ ሦስት ዋነኛ ክፍሎች የተዋቀረ ነበር። ጽላቱ/ታቦቱ የሚቀመጠውም ሆነ፣ እግዚአብሔር የሚገለጸው በቅድስተ ቅዱሳን እንጂ በአደባባዩ አልነበረም። በተመሳሳይ መንገድ እኛ ክርስቲያኖች የአምላክ ቤተ መቅደስ ነን። ነገር ግን እኛም እንደ ብሉይ ኪዳኑ ቤተ መቅደስ ሦስት ክፍሎች አሉን፤ ይኸውም:— *ሥጋ*፣ ነፍስና መንፈስ። በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር መንፈስ፣ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ እንደሚያድር፣ በአዲሱ ኪዳን ደግሞ፣ በሰው መንፈስ ውስጥ ብቻ ነው የሚያድረው። በአደባባዩ ኀጢአታቸውን የሚያስተሰርዩ ሰዎች እንደሚሰበሰቡ ሁሉ፣ በሥጋችንም አጋንንት "ሊንጠላጠሉ"[10] ይችላሉ።

ይህ ሙግት በበርካታ ምክንያቶች ድምዳሜውን ማለትም ክርስቲያን አጋንንት ሊገባበት/ሊያድርበት ይችላል የሚለውን አቋም ሊደግፍ አይችልም። ***አንደኛ፣*** ክርስቲያኖች የሕያው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናቸው ሲል፣ መንፈስ ቅዱስ በመንፈሳቸው ብቻ ነው የሚያድረው በሚለው ሃሳብ አይደለም። በሁለመናቸው እንጂ፣ (በዋቢነት የሚከተሉትን ክፍሎች ያነቧል:— ሮሜ *8÷9*፤ *1*ቆሮ. *3÷16*፤ *2*ቆሮ. *6÷16*፤ *ያዕ. 4÷5)*።

[10] ከዚያው አካባቢ ያገኘሁት ቃል ነው።



***ሁለተኛ፣*** እንዲያውም በሚያስደንቅ መልኩ፣ መንፈስ ቅዱስ "በሥጋችን" (ግሪክ "ሶማ" σῶμα) ውስጥ እንደሚኖር መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል[11]። የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል:— "ቤተ መቅደስ ሲል ግን፣ ስለ ገዛ ሰውነቱ መናገሩ ነበር" (ዮሐ. *2÷21)*። በዚህ ዐውድ፣ ጌታ "አፍርሱት" ያለውና አነርሱም ያፈረሱት፣ ኋላ ግን እርሱ፣ "ከሦስት ቀን በኋላ" ስላስነሣው ቤተ "መቅደስ" ነው የሚናገረው። ይህ ደግሞ "ቤተ መቅደስ" የሚለው ቃል፣ ቍሳዊ አካሉን አመላካች እንደ ሆነ የሚያሻማ አይደለም። መንፈሱን ወይም ነፍሱን "አላፈረሱትምና" (አልሞተምና)። በዚህ ምንባብ ቤተ መቅደስ የተባለው የክርስቶስ ቍሳዊ አካል ነው።

"ስለመሆኑ፣ ሰውነታችሁ በውስጣችሁ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? ይህም መንፈስ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት ነው። እናንተም የራሳችሁ አይደላችሁም" *(1*ቆሮ. *6÷19)*። አዲሱ መደበኛ ትርጉም፣ "ሰውነታችሁ" ያለውን፣ ነባሩ ትርጉም፣ "ሥጋችሁ" ይለናል። በብዙ የሐዲስ ኪዳን ምንባባት "ሶማ" (σῶμα ማለትም "አካል") እና "ሳርክ" (σάρξ, ወይም "ሳርኮስ" σαρκός ማለትም "ሥጋ") የሚሉት ቃላት በተለዋዋጭነት ጥቅም ላይ ውለው አናገኛለን—እንዳችም የትርጉም ልዩነት ሳይኖራቸው። ለዚህ ነው፣ "ሶማ ሳርክ ነው፤ ሳርክም ሶማ ነው" የሚባለው[12]። ይህም እንደ ዮሐንስ 2÷21 ግሪኩ፣ "ሶማ"

[11] "ሶማ"(σῶμα) የሚለው የግሪክ ቃል የሚጨበጠውን፣ የሚዳሰሰውን ቍሳዊ አካል የሚያመለክት እንደ ሆነ ልብ ይሏል። *James Swanson, Dictionary of Biblical Languages With Semantic Domains: Greek (New Testament)*, electronic ed. (Oak *Harbor: Logos Research Systems, Inc., 1997)*.

[12] ለበለጠ መረጃ የሚከተሉትን ስመ ጥር መጻሕፍት ይመለከቷል:— *Louw and Nilda, Greek-English Lexicon of the NT Based on Semantic Domains (New York: United Bible Society, n.d.), 1:147. Bauer, Ardnt, Gingrich, Danker, A Greek-English*

(σῶμα) የሚለው ቃል ነው በዚህም ቦታ ግልጋሎት ላይ ውሎ የምናገኘው። ይህ ደግሞ ቤተ መቅደስ የተባለው ቊሳዊው አካል እንደ ሆነ ያሳያል።

"ደግሞም፣ 'ምግብ ለኾድ ነው፤ ኾድም ለምግብ ነው' እግዚአብሔር ግን ሁለቱንም ያጠፋቸዋል። ሰውነት ለጌታ ነው እንጂ፣ ለዝሙት አይደለም፤ ጌታም ለሰውነት ነው" *(1ቆሮ. 6÷13)*። ለዝሙት ግልጋሎት ላይ የሚውለው አካል (ግሪክ "ሶማ" σῶμα) "የጌታ ነው" ይለናል። ይህ ደግሞ ቊሳዊው አካል የጌታ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ በግልጽ የሚያሳይ ነው። በአጠቃላይ ሁለመናችን የጌታ መንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንጂ፣ የተወሰነ ክፍላችን አጋንንት የሚያድሩበት በተወሰነው ደግሞ ጌታ ከአጋንንት ጋር በደባል የሚኖርበት አካል የለንም።

***ሦስተኛ፣*** ጌታ ስለ ብርቱ ሰው በተናገረበት ምሳሌ ላይ፣ "'አንድ ሰው ወደ ኀይለኛ ሰው ቤት ገብቶ ንብረቱን ለመዝረፍ ቢፈልግ፣ አስቀድሞ ያንን ኀይለኛ ሰው ሳያስር እንዴት አድርጎ ይሳካለታል? ኋላም ቤቱን መበዝበዝ ይችላል" (ማቴ. 12÷29 እንዲሁም ሉቃስ 11÷2122 ይመለከቷል)። ለመበዝበዝ ማሰር ወሳኝ ነው ማለት ነው። በሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሆናቸው እሙን ከሆነ፣ እኛን ለመበዝበዝ በእኛ ውስጥ ያለውን ማሰር የግድ ነው ማለት ነው። እንግዲያው እኛን ለመበዝበዝ፣ በእኛ ውስጥ ያለውን ኀያሉን መንፈስ ቅዱስ የሚያስር ማን ነው?

---

*Lexicon of the New Testament* (Chicago: University of Chicago Press, 1979), 169. James Swanson, *Dictionary of Biblical Languages With Semantic Domains: Greek (New Testament)*, electronic ed. (Oak Harbor: Logos Research Systems, Inc., 1997).



***አራተኛ፣*** በብሉይ ኪዳን፣ በአደባባዩ ላይ ይሆናሉ የተባሉት የእግዚአብሔር ሕዝቦች፣ በሥጋ ላይ ይንጠላጠላሉ ከተባሉት አጋንንት ጋር የተመለሉበት አግባብ ምንድን ነው? ይህን ምስስል ለማበጀት ታሳቢ ያደረግነው ወይም ድጋፍ የሆነን ፅንሰ አሳብ ምን እንደ ሆነ በዝርዝር መጠቀስ ይኖርበታል።

***አምስተኛ፣*** የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና የሰይጣን ቤተ መቅደስ አንዳችም ግንኙነት እንደሌላቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል፣ "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖታት ጋር ምን ስምምነት አለው? እኛኮ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነን፤ እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል ተናግሮአል፤ 'ከእነርሱ ጋር እኖራለሁ፤ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፤ አምላካቸው እሆናለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ'" *(2ቆሮ. 6÷16)*። ታዲያ እግዚአብሔር በመንፈሳችን፣ አጋንንት ደግሞ በሥጋችን ውስጥ በደባልነት ሊኖሩ የሚችሉት አግባብ ምንድን ነው? በዚህ የደባል አስተምህሮ ውስጥስ የቤቱ የበላይ ተጠሪ ማን ይሆን?

## ሙግት አራት

ከፍተኛ የሆነ የመደባደብ፣ የዝሙት፣ የመጠጥ፣ የስርቆት፣ የቅናት፣ የቊጣ፣ ወዘተ ፍላጎት በአንድ ሰው ውስጥ መኖር፣ አጋንንት እንዳሉበት የሚያመለክት ነው የሚል አስተሳሰብ አለ። ለዚህ አስተሳሰብ ግን የሚጠቀስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ወይም ደግሞ የሚቀርብ ሙግት አላውቅም። በሰዎች ሕይወት ውስጥ ይህ ዐይነቱ ጽኑ ፍላጎት ሊከሠት እንደሚችል እሙን ነው። ነገር ግን ይህ ጉዳይ በግለሰቡ ውስጥ አጋንንት አድረዋል ወደሚለው ድምዳሜ እንዴት ሊያደርስ ይችላል? አንድን ነገር መናገርና ለተናገሩት ነገር አጥጋቢ የሆነ ማስረጃ ማቅረብ ደግሞ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ይህ

ዐዋጅ እንጂ ሙግት እንዳልሆነ ልብ ይሏል። እስካሁን መልስ የሰጠንው ለሙግት እንጂ፣ መረጃ ሳልቀረበስት አቋም አይደለም። ቢሆንም ነገሩ ክንቱ አሉባልታ መሆኑን በማስረጃ ልሞግት።

ጠንካራ የሆነ ኢ-ሥነ ምግባራዊ ፍሳጎት በሰዎች ውስጥ መኖሩ፣ የሰዎችን የኀጢአት ጥማት ሊያመለክት ይችላል። ምናልባትም ኢአማኒያን በሆኑ ሰዎች ሕይወት ውስጥ፣ አጋንንት የመኖራቸው ምልክት ነው ሊባል ይችል ይሆናል (ይህንንም ለማለት ማስረጃ ማቅረብ የግድ ያስፈልጋል፤ ነገር ግን የውይይታችን ርእስ ስላልሆነ በወዲህም ሆነ በወዲያ መሞገት አያስፈልገኝም)። ከዚህ ባለፈ ግን፣ ግለሰቡ ላይ የሚታየውን አዘንብሎት ምክንያት በማድረግ አጋንንት አድረውበት ነው ማለት ስሕተት ነው። ምናልባትም ነውር ነው!

*አንደኛ፣* መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ የሥነ ምግባር እክሎች የሥጋ ሥራ ሲል ይጠራቸዋል (ሮሜ *8÷13*፤ ቈላ. *2÷8*፤ ገላ. *5÷16*)። ይህ ደግሞ በክርስቲያኖችም ሊታይ ይችላል። በዚህ ረገድ “ሥጋውያን ናችሁ” የተባሉትን የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን በዋቢነት ማየት እንችላለን (ክርስቲያኖች ለመሆናቸው *1*ቆሮንቶስ *1÷2-9* መግለጫ ከቀረበ በኋላ፣ በመካከላቸው መለያየት፡— ከምዕራፍ *1-4*፤ ዝሙት፡—ከምዕራፍ *5-7*፤ መንፈሳዊ እንጭጭነት፡— ከምዕራፍ *8-14*፤ የአስተምህሮ ችግር፡—ምዕራፍ *15* እንደ ነበረ በዝርዝር ተነግሯል)።

እነዚህ ሥነ ምግባራዊ እክሎች፣ በብዙ ምክንያት የእኛ ጠባይ ሊሆኑ ይችላሉ (ከአስተዳደግ፣ ከቤተሰብና ከባልንጀራ ተጽእኖ፣ ካለፍንባቸው መጥፎ ታሪኮች ወዘተ)። ነገር ግን ክርስቶስን በመምሰልና እውነተኛ የደቀ መዝሙር ሕይወት በመኖር፣ ክርስቶስን ወደ መምሰል ዕለት በዕለት እያደግን እንሄዳለን። ሥነ ምግባራዊ ለውጦች በሂደት የሚመጡ እንጂ፣ አንድ ሰው ክርስቲያን በሆነበት



ማግሥት እንደ እንጉዳይ በአንድ ጀንበር የሚፈሉ አይደሉም። ስለዚህ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ የሥነ ምግባር ጉድለቶች መታየታቸው፣ ግለሰቡ አጋንንት እንዳለበት ማስረጃ ነው ማለት ስሕተት ነው።

*ሁለተኛ፣* ምናልባት በሰይጣንና በአጋንንት ተጽእኖ፣ ክርስቲያኖች አግባብ ያልሆነ ነገር ሊያደርጉ ይችላሉ። ለዚህም ነው ክርስቲያን በንቃት የአጋንንትን ሽንገላ መመከት እንደሚኖርበት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስገነዝበው (ኤፌ. *6÷10-18*)። ክርስቲያን በአጋንንት ተጽእኖ ሥር ሊወድቅ እንደሚችል አሙን ነው። ይህ ማለት ግን ክርስቲያን አጋንንት ይገቡበታል ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አይደለም።

*ሦስተኛ፣* ዓለም የራሷ የሆነ ሽንገላ እንዳላት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ዓለም እውነተኛ ደስታ፣ ዘላቂ ርካታ፣ ታላቅ የሆነ ሰላም ወዘተ እሰጣለሁ የሚል ስብከት አላት። በገንዘብ ብዛት፣ በዕውቀት ብዛት፣ በቍሳቍስ ብዛት ወዘተ ምድራዊ ሕይወት ፍጹም በሆነ ተድላና ፍሥሓ እንደሚሞላ ይታሰባል። በዚህ ሂደት ውስጥ ሰዎች በስሕተት ኢ-ሥነ ምግባራዊ በሆነ ሕይወት ውስጥ ሊወድቁ ይችላሉ (*1*ዮሐ *2÷15*፤ *5÷19*፤ ዮሐ. *2÷1517*፤ ያዕ. *4÷4*፤ ገላ. *5÷17*፤ ሮሜ *722*፤ *1*ጴጥ. *211*)።

ቅዱሳት መጻሕፍት የሰው ልጅ ሙሉ ለሙሉ በኀጢአት እንደ ተበላሸ በግልጽ ይናገራሉ። በክርስቶስ ኢየሱስ በተገኘውም አዲስ ሕይወት፣ ሰዎች በምድራዊ ሕይወታቸው ወደ ፍጽምና ይደርሳሉ ተብሎ አይታሰብም። ስለዚህ የሰዎችን ክንቱ ምግባር አይቶ ብቻ፣ አጋንንት አድሮብሃል ማለት ስሕተት ነው።

ተሞክሮ ነው። ይህንን ይመስላል:— “በመዘምራን ቡድን ውስጥ የምታገለግል ነባር ክርስቲያን፣ አጋንንት ጣላት”፣ “ለብዙዎቻችን ተምሳሌት የሆነ ወንድም አጋንንት ዐደረበት” ወይም “የቤተ ክርስቲያናችንን ነባር ዲያቆን አጋንንት ጣሰው” ወዘተ። ይህ ዐይነቱ ሙግት ከብዙ አንጻር ስሑት ነው። ዋና ዋና የምላቸውን እነሆ:—

*አንደኛ፣* ይህ አካሄድ መሠረታዊ ችግር አለበት። አስተምህሮ የምናዋቅረው ቅዱሳት መጽሐፍትን መነሻ አድርገን እንጂ፣ ተሞክሯችንን መሠረት አድርገን መሆን የለበትም። ተሞክሯችን ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ጋር ተመሳስለው ሲገኙ፣ የመጽሐፍ ቅዱሱን ትምህርት በተሞክሮ አዋዝቶ ማቅረብ አግባብ ነው። ነገር ግን ተሞክሮውን መሠረት አድርጐ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጻረር ትምህርት ማስተማር ስሕተት ነው። ምክንያቱም መመሪያችን መጽሐፍ ቅዱስ እንጂ፣ የሰዎች ተሞክሮ አይደለም። ሌላው እኛ ስለ ጉዳዩ ያለን ዕውቀት ውስን መሆኑ፣ ትምህርታችንን ያልተሟላ ያደርገዋል።

*ሁለተኛ፣* አንድ ሰው ስረጅም ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሏል ማለት፣ ክርስቲያን ነበር ማለት ላይሆን ይችላል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖር ስድነት ዋስትና አይደለምና። እግዚአብሔር ብቻ ነው ማን ድነት እንዳገኘ እንዲሁም ማን ድነት እንዳላገኘ የሚያውቀው። በሌላ አነጋገር የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነው ሰው ማን ነው የሚለውን ጉዳይ በግልጽ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው (2ጢሞ. 2፥19፤ 1ሳሙ 16፥7፤ ማቴ. 13፥24-30፡36-43)። እኛ ድነት ለማግኘታችን መንፈስ ቅዱስ ስመንፈሳችን እንደሚመሰክር ግን እሙን ነው (ሮሜ 8፥16)።

ጌታ ለመስቀል ሞት አሳልፎ ስለሚሰጠው ሰው ሲናገር፣ ደቀ መዛሙርቱ፣ “እኔ እሆንን” የሚለውን ጥያቄ ጠየቁ እንጂ፣



“እርሱማ ይሁዳ ነው” ሲሉ አንመለከትም። ምናልባትም ይሁዳን ገንዘብ ያዥ ያደረጉት፣ ጥሩ/ጨዋ ሰው ነው ብለው በማሰብ ነው። ስለዚህ አንድ ሰው ምግባሩን በማየት ድነት ያገኘ ነው ወይም ያላገኘ ነው የሚለው አስተያየት፣ የሰዎችን የዕውቀት ውስንነት ያላገናዘበ፣ ልኩን የጣለ አነጋገር ነው።

*ሦስተኛ፣* ሰዎችን የሚጥለው አጋንንት ብቻ ናቸው ብሎ ማሰብ ስሕተት ነው። ሰዎች በተለያየ ምክንያት ሊወድቁ ይችላሉ። በተለያዩ ዐይነት በሽታዎች፣ የምግብ መበከል፣ በቂ ምግብ ያለመብላት፣ በከፍተኛ ሐዘንና ድንጋጤ ውስጥ መውደቅ ወዘተ ሰዎችን ድንገት ሊጥላቸው ይችላል ሰዎችን ስለሚጥሉ የበሽታ ዐይነቶች ለራ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ የሕክምና ባለሙያዎችን ይጠይቁ። ስለዚህ የወደቀ ሁሉ አጋንንት ይዘውታል ማለት በእውነቱ የጉድ ነው! ቢያንስ በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሚኖር ዘመናዊ ሰው፣ እንደዚያ ማሰብ በፍጹም የለበትም።

*አራተኛ፣* የእኛ የኢትዮጵያውን ባህልና አስተዳደግ፣ ነገሮችን ከመንፈስ አንጻር ብቻ የማብራራት፣ በአንጻሩ አእምሮንና የአእምሮ ውጤቶችን የማጥላላት አዝምሞት አለው[14]። ይህ ደግሞ መውደቅን ሁል ጊዜ ከመንፈስ ጋር ብቻ እንድናያይዝ ምክንያት ሆኖናል። በተለያየ ምክንያት የወደቁትን ሰዎች አጋንንት እንዳደረባቸው በማሰብ ብዙዎችን ክፉኛ ጐድተናል። የወደቁበት ችግር ሳያንስ፣ ምን ይሉኛል በሚል ለቈቃ ውስጥ ከተናቸዋል። ስለዚህ በተለያዩ ምክንያቶች፣ መውደቅን ሁል ጊዜ ከክፉ መንፈስ ጋር ብቻ ማያያዝ

[14] ባህላችን ነገሮችን ከመንፈስ አንጻር መተንተን የሚወድ፣ ምስጠራ ክፉኛ የተጫነው ባህል እንደ ሆነ፣ “ቃለ እንክር—ዐይራ ይህን ያነበበ” በሚለው፣ በተለይ ከገጽ 5 እስከ ገጽ 24 ላይ በስፋት ምግተነበታል።

ትክክል አይደለም። በዚህ አንጻር ክርስቲያኖች ፍጹም ጠንቃቃ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

ክርስቲያን አጋንንት ይገቡበታል የሚሉ ሰዎች፣ ትምህርታችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ለማለት የሚጠቅሷቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትና የሙግት አካሄዶች ስሑት መሆናቸውን፣ በአስሳ መልክም እንኳ ቢሆን ለማየት ሞክረናል። ክርስቲያኖችም ምንም ዐይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ የሌለውን እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚያስተምረውን አስተምህሮ የሚቃረን ይህ ዐይነቱን ትምህርት ያለምንም ማቅማማት፣ ወግድ ሊሉ ይጠበቅባቸዋል። አጋንንት፣ ሰይጣን፣ ዲያብሎስ፣ እርኩሳን መናፍስት…ያለ ሁሉ፣ የእርኩሳን መናፍስት ባላንጣ እንዲሁም የአምላክ ባለሟል ነው ብሎ ማሰብ ትክክል አይደለም።

“የዘር ማንዘርሽን መርገም ልሰበርልሽ”፣ “የቍጣ መንፈስ ላስወጣልህ”፣ “ሰይጣን ስኬት እንዳታገኚ እየተዋጋሽ እንደ ሆነ መንፈስ ቅዱስ ይናገረኛል” ወዘተ የሚሉት ንግግሮች ሁሉ፣ አንዳችም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የላቸውም። ቢያንስ እስካሁን በሁለት ተከታታይ ምዕራፎች ያየናቸው ነጥቦች፣ ይህን አስተሳሰብ በፍጹም እንዳንቀበል እንዲያውም አስተምህሮውን በግልጽ እንድንቃወም የሚያስገነዝቡን ናቸው።



# ክፍል ዘጠኝ

## በአባይ ነባዮችና በመናፍቃን ተዘወትረው የሚታዩ ባሕርያት የትኞቹ ናቸው?



### ሀ. የአባይ ነባዮችና የመናፍቃን አስተምህሮአዊ ባሕርይ

በዚህ ክፍል ለማየት የምንሞክረው፣ በአብዛኞቹ አባይ ነባዮችና መናፍቃን ዘንድ ተዘወትረው የሚታዩትን አስተምህሮአዊ ባሕርያት ነው[1]።

[1] የዚህ ክፍል መሠረታዊ የሙግት ጭብጥ በአብዛኛው የተወሰደው፡— *Alan W. Gomes*, *Unmasking the Cults* (*Grand Rapids: Zondervan, 1955*) ላይ ነው።